# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ጥያቄ:- *ተከታዩ የጸሎቱ ክፍል:* "የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው: ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው: 'ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ' የሚለው: መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው: 'ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር' የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው: የዘለዓለም ማንተማችን እንደኾነ እናምናለን::" *የሚለው ነው::*

መልስ:- ይህ አንቀጽ: ራሱን ችሎ እየተሠራበት ስለኖረውና ከዚህ ቀደም ብዬ በጠቀስሁላችሁ ሰንደቅ ዓላማ መኻከል ላይ ሠፍሮ ስለሚታየው ብሔራዊ ማንተሙ ምንነት፡ ከማንና እንዴትስ እንዳገኘው: ኢትዮጵያዊዉን ያስታውሰዋል:: አዎን! ማንተሟ: ይህ ኾኖ: በሥጋውም፥ በነፍሱም፥ በመንፈሱም የተወለደባትና ያደገባት: የተማረባትና ያወቀባት፥ የሚመራባትና የሚተዳደርባት፡ ለዘለዓለምም የሚኖርባት መንግሥት: ከማን፡ ለማንና ለምን እንደተሰጠች: ይህ አንቀጽ: በግልጽ ይነግረዋል::

ይህች መንግሥት፥ ማንተሟ ጭምር: የፍጡራን ሳይኾኑ: የእግዚአብሔር መኾናቸውን: ለዘወትር ያስገነዝበዋል፤ በሥነ መንግሥት አስተሳሰቡም: ጥንት: በእባቡ ዲያብሎስ፡ ኋላም: በአዳምና ሔዋን፡ በመካከሉም: በእሥራኤል ሕዝብ የተደረገውን የመሰለ ክህደት፥ ዓመፅና ምንዝርና: በእርሱም ዘንድ ተፈጽሞ: እንደነዚያ: ለጥፋት እንዳይዳረግ፥ አገሩ ኢትዮጵያ፡ አባቶቹ ኢትዮጵያውያንና እናቶቹ ኢትዮጵያውያትም: ከመጀመሪያው አንሥተው: ይዘውት የኖሩትን: የእግዚአብሔርን ሥርዓተ መንግሥት ትቶ: ወደሌላ እንዳያዘነብል፡ ወይም: ከዚህ ውጭ የኾነ: ባዕድ ዓላማና አመራር ባለው የሥነ መንግሥት አንጃ ውስጥ አባል እንዳይኾን: ይኸው ጸሎት: ኢትዮጵያዊዉን: በጽኑ ያስጠነቅቀዋል::

ይህ የጸሎቱ ክፍል: የዚች የዘውድ መንግሥት: ንጉሥዋ: *"ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የተባለው: ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን፥ ንግሥቷም: *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"* የተባለችው: ድንግል ማርያም መኾኗን: ኢትዮጵያዊው: በፍጹም እውቀት ተቀብሎ: በሃይማኖት ያጸናው፥ በምግባርም የሚገልጸው መኾኑን: ለራሱና ለአምላኩ፥ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ: ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው::

ጥያቄ:- *ከዚህ በኋላ ያለው የጸሎቱ ክፍል:* "በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ: ከእግዚአብሔር በመንፈስ: የመወለድን ክብር ስላገኘን: በዚህ ልጅነታችን: የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን::" *የሚለው ነው::*

መልስ:- ይህ የጸሎቱ አንቀጽ: የኢትዮጵያዊነቱ ደረጃ: በመንፈሳዊው የጸጋ ኃይል: ከጠንቀኛው ሥጋዊ ፍትወትና ነፍሳዊ ምኞት ነጻ ከሚያደርገው ልዕልና የደረሰ መኾኑን፡ ማለትም: ዘለዓለማዊዉን የሕይወትና የክብር ዘውድ ለመቀዳጀት የበቃ መኾኑን: ለኢትዮጵያዊው: ዘወትር ያስታውሰዋል::

# ምዕራፍ ፪፤ ሃይማኖት።
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሓተታ።

---

ከዚህ የተነሣ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በልቦናው ውስጥ ያለማቋረጥ የሚፈነጥቀው የደስታ ብርሃን፡ ፀዳሉ፡ በፊቱ ላይ ሳይቀር ፈክቶ ይታያል። አዎን! ይህ ኹሉ የሚኾነው፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ፈጣሪው፡ በረቂቋ ነፍስና በግዙፉ ሥጋ አሟልቶና አሳምሮ፡ በመልኩ የፈጠረው ከመኾኑ ጋር፡ በቅዱስ መንፈሱ ወልዶ፡ የጸጋ ልጁ፥ የመንግሥቱ ወራሽና የአገልግሎቱ ተካፋይ ስላደረገው፡ ከዚህ የሚበልጥ፡ የክብር ደረጃና የደስታ ምንጭ አለመኖሩ ስለሚሰማው ነው።

በዚህ የእምነት መግለጫው መሠረትነት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ በተሰማራበት፡ በማናቸውም ሙያ፡ ወይም የሥራ መስክ፡ የሚያገለግለው፡ በልጅነት መብቱ፡ ወራሿ የኾነባትን የእግዚአብሔርን መንግሥት መኾኑን አውቆና ተገንዝቦ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ግዳጁን፡ በሙሉ ፈቃደኛነትና ታማኝነት፡ ቅንነትና ትጋት፥ ኃይልና ጽናት እያካኼደ ይፈጽማል። ግዳጁን የሚፈጽመውም፡ ገበሬም፥ ነጋዴም፡ ካህንም፡ ወታደርም፡ ዳኛም፡ ጭቃ ሹምም፡ እረኛም፥ ከብት አርቢም፡ ዘበኛም፡ አናጢም፡ ግንበኛም፡ ቀጥቃጭም፡ ሸክላ ሠሪም፥ ቀራጭም፥ ሸማኔም፡ ዘፋኝም፡ ባለገንዘብም፡ አምራችም፡ ሠራተኛም፥ ከያኒም፥ ጠቢብም፡ መሓንዲስም፥ ተዋናይም፡ መምህርም፥ ሠዓሊም፥ ጸሓፊም፥ ደራሲም፡ ባለቅኔም፥ ባለመድኃኒትም፡ ሓኪምም፥ ምሁርም፥ አማካሪም፡ አስተዳዳሪም፥ መሪም ቢኾን፡ በዚያ ሙያው፥ ወይም የሥራ መስኩ መኾኑን ተገንዝቦ ነው።

ይህ አንቀጽ፡ ኢትዮጵያዊው፡ "እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ ነኝ!" ብሎ፡ በውስጥ ልቡናው የሚያምንበትንና በአፍአ አንደበቱ የሚያስታውቀውን ማንነቱን፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ በሃይማኖት ያጸናው፥ በምግባርም የሚገልጸው መኾኑን፡ ለራሱና ለአምላኩ፥ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።

ጥያቄ፡- *መልካም! ከዚህ ተያይዞ ያለው የጸሎቱ ክፍል፡ "ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን።" የሚለው ነው።*

መልስ፡- ኢትዮጵያዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ማንነቱን እውነተኛነት የሚያረጋግጠውና የሚያጸድቀው፡ በዚህ ሃይማኖታዊ ምግባሩ ነው፤ ለማንነቱ ማረጋገጫና ማጽደቂያ፥ ከእግዚአብሔር ላገኛቸውም፡ የጸጋ ልጅነትና የመንግሥት ወራሽነት ዋስትና፥ ለአገልጋይነቱም ብቅዓት ማስተማመኛ ይኾነው ዘንድ፡ ከፈጣሪው የተሰጠው ማኅተም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ስለኾነ፡ በማያቋርጥ ንስሓ ላይ የተመሠረተውን፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር መፈጸም፡ ለኢትዮጵያዊው፡ እጅግ የሚያስፈልገው መኾኑን፡ ይህ የጸሎቱ ክፍል ያሳስበዋል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ አንቀጽ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ይህን ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ በሃይማኖት ያጸናው፡ በምግባርም የሚገልጸው መኾኑን፡ ለራሱና ለአምላኩ፣ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።

ጥያቄ:- *ከዚህ በመቀጠል ያለው የጸሎቱ ክፍል፡ "የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።" የሚለው ነው።*

መልስ:- ኢትዮጵያዊው፡ ኢትዮጵያዊነቱን፡ በሃይማኖታዊ ፍሬውም ኾነ፡ በምግባራዊ ግቡ፡ ለፍጹምነት የሚያበቃው፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በአንድነት በሚገኙበት ኹኔታና መልክ ብቻ ነው።

እንዲህ ካልኾነ በቀር፡ የኢትዮጵያዊነቱን ሃይማኖታዊ ፍሬም ኾነ፡ ምግባራዊ ግብ፡ እናቲቱንና ልጇን፡ በምንም መንገድ ለይቶ፡ ወይም፡ በተናጠል አድርጎ፡ ሊያስበውና ሊያውቀው፡ ሊቀበለውና ሊያምንበት፡ በንግግርና በጽሑፍ፡ በሥዕልና በሌላውም ጥበብ ቢኾን፡ ሊገልጸውና ሊያየው፡ ሊኖርበትም ከቶ አይቻለውም። ምክንያቱም፡ ኢትዮጵያዊነት፡ ጥንቱኑ፡ ተመሥርቶ የታነጸው፡ በመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ ሰብአዊና ምድራዊ ጋብቻ ላይ ሲኾን፣ ኋላም፡ በመለኮታዊውና ሰማያዊው ከብካብ ተደምድሞ፡ ዘለዓለማዊዉን የዘውድ ጉልላት የተቀዳጀው፥ በመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም በመኾኑ ነው።

ይህ እውነታ፡ እኒህ፡ የመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን የኾኑት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ተለያይተው፡ በተናጠል የተገኙበት ኹኔታና መልክ፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፡ በመንፈሳዊውም ህልውና፡ ፈጽሞ ባለመኖሩ ተረጋግጦ ይታወቃል፣ ይኸውም፡ ፍጥረተ-ዓለሙ፡ ከክፋቱና ከጥፋቱ የተነሣ፡ ሊደርስበት ከነበረው ጠቅላላ ድምሳሴ ድኖ፡ ሕያውነትን ሊያገኝ የቻለው፥ ደግሞም፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ በንጉሥነትና በንግሥትነት ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው፡ በሰማይና በምድር ያለውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍጥረተ-ዓለም የሚያስተዳድሩት፡ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም ሳይለያዩ፡ ኹለቱም በአንድነት በመኾኑ ነው።

እነሆ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ለዘለዓለም እየኖረባትና እያገለገለባት ባለችው፡ በዚችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያ፡ ሰፍነው ያሉት የዘውድ መሪዎቹና አስተዳዳሪዎቹ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ስለኾኑ፡ በዚህ እውነታ ላይ የተመሠረተውን ሃይማኖቱን፡ በምግባር የሚገልጸው፡ እናትና ልጇን፡ ኹለቱንም ባልተነጣጠለ ፍቅር፡ በአንድነት በመውደድ ሊኾን እንደሚገባ፡ ይህ የጸሎቱ ክፍል፡ ኢትዮጵያዊዉን ያሳስበዋል።

# ምዕራፍ ፬፤ ሃይማኖት::
## ስለኢትዮጵያውያኑ የቃል ኪዳን ጸሎት ሐተታ::

---

በተለይ: በአኹኑ: የመጨረሻው ዘመን: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ በተመሠረተበት: በማይነጣጠለው የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ፍቅሩ ላይ: ከባዱ የጠላት ጦር: ባልተቋረጠ ኀይል: እየተወረወረበት ያለ መኾኑን: እርሱም: ራሱን: ከዚያ ኀይል: በበለጠው የንቃትና የጽናት ትጥቅ ተከላክሎ: ጥቃቱን መመለስ ያለበት መኾኑን: ኢትዮጵያዊው: ጥሩ አድርጎ ያውቃል::

ስለዚሁ ጦር: በተለይም: የዲያብሎስን ኀይል ከታጠቀው የአምልኮ ባዕድና የፀረ ማርያም ወገን ስለሚሠነዘረው ጥቃት: *"ወዳጆች ሆይ! መንፈስን ኹሉ አትመኑ! ነገር ግን: መናፍስት: ከእግዚአብሔር ኾነው እንደ ኾኑ: መርምሩ! ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት: ወደዓለም ወጥተዋልና:: የእግዚአብሔርን መንፈስ: በዚህ ታውቃላችሁ:- ኢየሱስ ክርስቶስ: በሥጋ እንደመጣ: ማለትም: <u>ከድንግል ማርያም: ሰው ኾኖ እንደተወለደ:</u> የሚታመን መንፈስ ኹሉ: ከእግዚአብሔር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ: በሥጋ እንደመጣ: ማለትም: <u>ከድንግል ማርያም: ሰው ኾኖ እንደተወለደ:</u> የማይታመን መንፈስ ኹሉ: ከእግዚአብሔር አይደለም:: ይህም: የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፡ ይህም: እንዲመጣ ሰምታችኋል፡ አኹንም እንኳ: በዓለም አለ::"* ከሚለው የወንጌላዊው ቃል: ኢትዮጵያዊው: በሚበቃ ተምሮአል::

በእርግጥም: እኩሌቶቹ: በሌሊቱ ጨለማ: ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ አጋንንት እየሰገዱ: የቀሩትም: በቀኑ ብርሃን: "የሱስን እወድዳለሁ!" እያሉ: እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ግን በመጥላት: በክርስቲያንነት ስም: "እግዚአብሔርን እናመልካለን!" ማለት: የርኩስ መንፈስ እንጂ: የመንፈስ ቅዱስ ስላልኾነ: ኢትዮጵያዊው: ይህን የመሰለውን የባዕድ አምልኮና የፀረ-ማርያምነት ሰይጣናዊ ጥቃት: የመንፈስ ቅዱስ ጋሻ በኾነው: በፍቅረ-ማርያምና በክርስቶሳዊው ፍቅር ተከላክሎ በመመለስ: ድሉን መጐናጸፍ እንዳለበት: አዎን! ይኸው: የጸሎቱ ክፍል: ኢትዮጵያዊዉን አጥብቆ እያስጠነቀቀ ያስታውሰዋል::

ይህ አንቀጽ: ኢትዮጵያዊው: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱን በይፋ የሚገልጠውና ለይቶ የሚያሳውቀው: በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ላይ ተመሥርቶ በሚፈጽመው: የኢትዮጵያዊነት ምግባሩ የመኾኑን ነገር: በፍጹም እውቀት ተቀብሎ: በሃይማኖት ያጸናው: በምግባርም የሚገልጸው መኾኑን: ለራሱና ለአምላኩ፡ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ: ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው::

**ጥያቄ:-** *መልካም! በመጨረሻ ያለው የጸሎቱ ክፍል: "የቅዱሱ ኪዳን* <u>**ኢትዮጵያዊነታችንን: በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን: ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም: እንደቃል ኪዳኑ: እግዚአብሔር እንደ ኾነ እናምናለን:: ለዘለዓለሙ፡ አሜን::"**</u> *የሚለው ነው::*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

መልስ:- ኢትዮጵያዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን፡ አውቆት፡ አምኖበትና ሕይወት አድርጎት የኖረው፡ የሚኖረውም፡ ከሰው፡ ወይም፡ ከሌላ ፍጡር አግኝቶት፡ ወይም፡ ተምሮት ሳይኾን፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ አግኝቶትና በመንፈስ ቅዱስ ተምሮት መኾኑን፡ ሥርዖበት እንዲጠቀምበት የተሰጠውም፡ እንደመክሊቶቹ ባለቤት፡ ከራሱ ከፈጣሪው መኾኑን፡ ስለዚህም፡ አደራው ጥብቅ፡ ስጦታውም ምጡቅ በመኾኑ፡ ኀላፊነቱን አውቆ፡ የበኩሉን ግዳጅ፡ በአግባቡ መፈጸም እንዳለበት፡ ይህ የጸሎቱ ክፍል ያመለክተዋል።

ይህም፡ እግዚአብሔር፡ በነቢያት፡ *"ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፡ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። ...እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፡ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፡ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!"*፡ ደግሞም፡ *"ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ፡"* የሚለውን የነቢያትን ቃል በመጥቀስ፡ እውነተኛው መምህርና ምሁር ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"'ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!' ተብሎ፡ በነቢያት ተጽፏል፡ እንግዲህ፡ ከአብ የሰማ፡ የተማረም ኹሉ፡ ወደእኔ ይመጣል፡"* ሲል በተናገረው ቃሉ መሠረት ደርሶ የተፈጸመ ነው። ደግሞም፡ *"መምህራችሁ፡ አንድ፡ እርሱም፡ ክርስቶስ ነውና፡ እናንተም፡ ኹላችሁ፡ ወንድማማች ናችሁና፡ በምድር ላይ፡ 'መምህራን!' አትባሉ! ...እናንተ፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ እውነቱንም ፈልጉ! ሌላው ኹሉ ይጨመርላችኋል፡"* ያለው ቃሉ፡ ትምህርቱንና ዕውቀቱን የምናገኘውን ከእርሱ ብቻ መኾኑን ያመለክታል።

ከዚህ ቃሉ የተነሣ፡ ለሚፈልጉት ኹሉ ቅርብ የኾነውን እግዚአብሔርን፡ በእውነት መንፈስ ስለፈለገው፡ ይኸው አምላኩ፡ በልዩ ልዩ ረቂቃንና ግዙፋን የክፉትና የጥፋት ኀይላት፡ ተዳፍኖ ሊቀር ይችል የነበረውን፡ ያን መለኮታዊ ጸጋ፡ ገላልጦ ማሳወቁ ብቻ ሳይኾን፡ ከተጻራሪው ወገን የሚወረወረውን የፈተናና የመከራም ጦር ኹሉ ተቋቁሞና አሸንፎ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ያገኘውን የትንሣኤ ሕይወት እንዲቀጥል ያስቻለው መኾኑን፡ ይህ፡ የጸሎቱ ክፍል፡ ኢትዮጵያዊዉን ያስገነዝበዋል። በዘወትር ጸሎቱም፡ ከዚህ፡ የቃል ኪዳን ጸሎት ቀጥሎ፡ "ይህን ላደረገልን፡ ለእግዚአብሔር አብ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስጋናችንን እናቀርባለን።" የሚለውን ቃል የሚያሰማው፡ በዚህ ምክንያት ነው።

ይህ፡ የጸሎቱ፡ የመጨረሻ ማጠቃለያ አንቀጽ፡ ኢትዮጵያዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር የማግኘቱን ምሥጢር፡ በፍጹም እውቀት ተቀብሎ፡ የአምልኮ ታማኝነቱንም፡ በገሃድ ጭምር፡ ለቃል ኪዳን አምላኩ ብቻ አድርጎ፡ በሃይማኖቱና ያጸናው፡ በምግባሩም የሚገልጸው መኾኑን፡ ለራሱና ለፈጣሪው፡ ለሌላውም የተፈጥሮ ወገኑ፡ ዘወትር የሚያረጋግጥበት የምስክርነት ቃል ነው።

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት።

## የጋብቻ ሥርዓት፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተከብሮ ስለመኖሩ።

ጥያቄ፡- *የዚህን ጸሎት ማብራሪያ ከማብቃትህ በፊት፡ በዚሁ የቃል ኪዳን ጸሎት ውስጥ ተካትተው ከሚገኙት አርእስተ ነገሮች መካከል አንዳንድ ያመለቡንን ጥያቄዎች እንድናነሣቸው ብትፈቅድልን?*

መልስ፡- ማለፊያ! እንዲህ ስትበረቱልኝማ፡ ደስታዬ ነው፡ ስለዚህ፡ ጥያቄዎቹን አቅርቢቸውና እንወያይባቸው!

ጥያቄ፡- *እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን ስለመሠረተው፡ ኢትዮጵያውያንም፡ አክብረውና ጠብቀውት ስለኖሩት፡ ስለተቀደሰው ጋብቻ፡ ምሳሌ ሊኾኑን የሚችሉትን አባቶችና እናቶች ለይተህ ብታስታውቀን፡ የሚጠቅመን አይመስልህም?*

መልስ፡- በእርግጥ ይጠቅመናል፡ ለዚህ ጋብቻ፡ ምሳሌ ሊኾኑን ከሚችሉት፡ ከቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን መካከል፡ የታወቁትን፡ አዳምንና ሔዋንን፡ ኖኅንና ሐይከልን፡ ሴምንና ሚስቱን፡ ካምንና ሚስቱን፡ ያፌትንና ሚስቱን፡ ይስሐቅንና ርብቃን፡ ኢትዮጵያዊውን ካህን፡ ዮቶርንና ሚስቱን፡ እሥራኤላዊነቱን፡ ለኢትዮጵያዊነት ያበቃውን ሙሴንና ኢትዮጵያዊት ሚስቱን፡ ሲጳራን፡ ኢትዮጵያዊዉን እርዮንንና ሚስቱን ቤትሳባን፡ መጥምቁ ዮሐንስን የወለዱትን፡ ካህኑን ዘካርያስንና ኤልሣቤጥን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምን የወለዱትን፡ ኢያቄምንና ሐናን፡ ኢትዮጵያዊዉን ጻድቅ ተክለ ሃይማኖትን የወለዱትን፡ ጸጋ ዘአብንና እግዚእ ኃረያን በዋቢነትና በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል።

ጥያቄ፡- *ስለ ጋብቻ ቃል ኪዳን፡ በአርአያነታቸው፡ ደጋግ ምሳሌዎቻችን የኾኑትን፡ አዳምንና ሔዋንን፡ ከተከታታዮቹም ቃል ኪዳናት ተቀባዮች መካከል፡ ኖኅንና ሙሴን ስታነሣሣቸው፡ ምነው፡ የቀሩትን፡ መልከ ጼዴቅን፡ አብርሃምንና ዳዊትን ሳትጠቅሳቸው አለፍህ?*

መልስ፡- እኒህን ሦስቱን ስሞች፡ ሳልጠቅሳቸው ያለፍሁበት ምክንያት አለኝ፡ ይኸውም፡ መልከ ጼዴቅ፡ በኢትዮጵያዊነቱና በኢትዮጵያውያን አብነቱ፡ ለዘለዓለማዊው መልከ ጼዴቅ፡ ባለው ቀዳሚ ምሳሌነት፡ ሕይወቱን፡ በተለየ ብቅዓት የመራ ቅዱስ ሰው በመኾኑ ነው፤ እሥራኤላውያኑ፡ አብርሃምና ልጁ ያዕቆብ፡ እንዲሁም፡ ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን ግንምር፡ በጋብቻቸው ረገድ፡ በአንድ ሚስት እንዲጸኑ የሚጠይቀውን የእግዚአብሔርን ሥርዓት ጠብቀው ባለመኖራቸው ነው።

ይኹን እንጂ፡ እኒህ እሥራኤላውያን፡ የኋላ ኋላ፡ እሥራኤላዊነታቸውን፡ ለኢትዮጵያዊነት ያበቁበት በረከት ስለተሰጣቸው፡ በዚያ በረከት ምክንያት፡ ይኸንኑ የጋብቻ ቃል ኪዳን እንደፈጸሙ ሊቆጠሩ በቅተዋል።

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህም፡ ከዚህ በሚከተለው ኹኔታዎች ተረጋግጦ ይታወቃል፡

፩ኛ፡ መልከ ጼዴቅ፡ በኹለንተናው፡ ፈጽሞ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አርአያ ኾኖ የተገለጸ ሰው ስለነበረ፡ ጋብቻ ሳያስፈልገው፡ በብሕትውና ይኖር እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ የምታስተውሏቸው ኹለት ቍም ነገሮች አሉ፡ እነዚህም፡ አንዱ፡ ግብፃውያን፡ በቅርቡ፡ ወደኢትዮጵያ ካመጡት፡ ከምንኵስና ይልቅ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ እውነተኛው የንጽሕናና የብቅዓት ሕይወት ተደርጎ፡ ሲሠራበት የኖረው፡ ሥርዓት፡ እንደምንኵስናው፡ አስኬማ፡ ጥቁር ቆብና ጥቁር ልብስ የማያስፈልገው፡ በኢትዮጵያውያኑ፡ በመጥምቁ ዮሓንስና በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአኗኗርና የአለባበስ ባህል፡ በገሃድ ተከሥቶ የነበረው፡ "ብሕትውና" መኾኑ፡ ኹለተኛውም፡ የመልከ ጼዴቅ ዘርና ልደት፡ ለኢትዮጵያውያን የተላለፈው፡ ሰብአዊው፡ በወንድሞቹና በእኅቶቹ በኩል ሲኾን፡ መልአካዊው ደግሞ፡ በመንፈስ ቅዱስ መኾኑ ነው፡፡

፪ኛ፡ አብርሃም፡ የግርዛትን ቃል ኪዳን፡ ከፈጣሪው የተቀበለው፡ እንደቃል ኪዳኑም የተገረዘው፡ ይስሓቅንም፡ ከመካን ሚስቱ ከሣራ እንደሚወልድ፡ ከሥላሴ፡ የተስፋ ቃል የተሰጠው፡ የተስፋ ቃሉም ተፈጽሞ የወለደውና እርሱንም፡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው፡ አስቀድሞ፡ ስለአምልኮተ እግዚአብሔርና ስለግርዛት ምሥጢር፡ የልዑል እግዚአብሔር ወገን፡ የእውነት ካህንና የሰላም ንጉሥ ከኾነው፡ ከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ አውቆና ተምሮ ካመነ፡ በእርሱም ከተባረከ በኋላ መኾኑ ይታመናል፤ እንዲያ ከኾነ፡ በዚያን ዘመን፡ ለኢትዮጵያዊነት የሚያበቃው ጸጋ፡ ያ ቡራኬ ስለነበር፡ በዚያ ጸጋ፡ አብርሃም፡ "ለኢትዮጵያዊነት በቅቶ ተገኘ!" ያሰኛል፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ሥላሴ የሰጡት የተስፋ ቃል ተፈጽሞለት፡ ገና በአረማዊነቱ ሣለ ካገባት፡ ከመካኒቱ ከሣራ፡ በተገረዘና በግርዛት ቃል ኪዳን በከበረ ሰውነቱ፡ ይስሓቅን የወለደው፡ በዚያ ኢትዮጵያዊነቱ መኾኑ፡ ሊጠረጠር ከቶ አይቻልም፡፡ ስለዚህ፡ ሣራ ስትሞት፡ በኢትዮጵያዊቷ ኬጡራ ብቻ ተወስኖ እንዲኖር የተጠራው አብርሃምና ይህችው ኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተከብሮና ተጠብቆ የኖረውን፡ የእግዚአብሔርን የጋብቻ ሕግ ለመፈጸም በቅተዋል፡፡

፫ኛ፡ በእውነተኛ ንስሓው፡ ለኢትዮጵያዊነት የበቃው ዳዊትና በኢትዮጵያዊው የጋብቻ ሕግ ጸንታ፡ ከኢትዮጵያዊው ኦርዮ ጋር፡ በቅድስና የኖረችው፡ ኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በትሳባ (ቤርሳቤህ)፡ ሰሎሞንን ለመውለድ የበቁት፡ ጋብቻቸውን፡ ኢትዮጵያውያን አክብረውትና ጠብቀውት በኖሩት የእግዚአብሔር ሕግ መሠረት በመፈጸማቸው መኾኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

፬ኛ፡ ከተነሣሒው ዳዊትና ከሕጋዊዋ ቤትሳባ የተወለደው፡ ሰሎሞን፡ የቃል ኪዳን ዘርነቱና የማክዳ ድንግልና፡ ንስሓ ኾኖት፡ ለኢትዮጵያዊነት መብቃቱ እርግጥ ነው፡፡ ስለዚህ፡ ድንግሊቱ ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማክዳ፡ ከእርሱ፡ ከሰሎሞን፡ ምኒልክን፡ በንጽሕና የወለደችው፡ ኢትዮጵያውያን አክብረውትና ጠብቀውት በኖሩት፡ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ከተፈጸመ ጋብቻ መኾኑ ተረጋግጦ ተመዝግቧል፡፡

# ምዕራፍ ፪፣ ሃይማኖት።

---

## ስለኢትዮጵያና ስለእሥራኤል የበኵር ልጅነት ትርጓሜ።

ጥያቄ፡- የጋብቻና የግርዛት ነገር ከተነሣ ዘንድ: ሙሴንና ኢትዮጵያዊት ሚስቱን: ሲጳራን: አኹን ከምንወያይበት ርእስ ጋር አያይዘህ: በበለጠ እንድታስረዳን የምንፈልገው ምሥጢር አለ።

ይኸውም: ሙሴ: የእሥራኤልን ልጆች: ከባርነት: ነጻ ያወጣቸው ዘንድ: ወደግብፅ እንዲኼድ: እግዚአብሔር አዝዞት: ኢትዮጵያዊት ሚስቱን: ሲጳራንና ከእርሷ የወለዳቸውን ኹለቱን ልጆቹን ይዞ: በመንገድ ላይ እየተጓዘ ሣለ: እግዚአብሔር እንዳነጋገረው: ከዚያ ንግግር በኋላም: አንድ አስደንጋጭና አስፈሪ ኹኔታ ድንገት ደርሶ እንደነበረ የሚናገረው: እንዲህ የሚለው ዜና ነው።

- እግዚአብሔር: በዚያ ንግግሩ: ለሙሴ: ፈርዖን: ከብዙ መቅሠፍቶች በኋላ: ልቡን በማደንደን: የእሥራኤልን ልጆች ለመልቀቅ: ፈቃደኛ ስለማይኾን: "ፈርዖንን: እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- 'እሥራኤል: የበኵር ልጄ ነው፥ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ: አንተም: ትለቅቀው ዘንድ እምቢ አልህ፤ እነሆ: እኔ: የበኵር ልጅህን እገድላለሁ! ይላል፤' በለው።" እንዳለው፥

- ወዲያውም: ሙሴ: ከነቤተሰቡ ባደረበት ሥፍራ: እግዚአብሔር: እንደገና ተገለጠለት: ሊገድለው እንደፈለገ:

- ሚስቱ ሲጳራም: ባልጩት ወስዳ: የልጇን ሸለፈት እንደገረዘች፡ ወደእግሩም እየጣለችው: ስለግርዛቱ: "አንተ: ለእኔ: የደም ሙሽራ ነህ!" እንዳለችው፥

- በዚህም ጊዜ: ሙሴን ሊገድለው የታዘዘው መልአክ ሞት: [፴፫] ከእርሱ: ፈቀቅ እንዳለ: በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንነበናል።

ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን መልእክት የያዙትን: የአንተን መጻሕፍት: እንዲህ ለማንበብ መቻላችን: የዚህ ውይይታችን ፍሬ ነውና: "ዕድሜ ለአንተ!" እንላለን።

አኹንም: ይህ ነገር: ምሥጢር ኾኖብናል፤ በተለይም: ሙሴ: "በመንገድ ላይ ባደረበት ሥፍራ: እግዚአብሔር ተገናኘው፤ ሊገድለውም ፈለገ፤" የሚለው ቃል: እግዚአብሔር: ሙሴን በሚያህል: ለታላቅ ተልእኮ በጠራው ባለሟሉ ላይ: እንዴት: ይህን የመሰለው የመጨረሻ ፍርድ: ሊፈጸምበት ይገባል!" ብሎ አሰበ? ደግሞስ: እግዚአብሔር: የአብርሃምን ልጆች: እሥራኤልን: የበኵር ልጄ ካላቸው: እኛ: ቀዳሚዎቹ: የመልከ ጼዴቅ ልጆች የኾንነው ኢትዮጵያውያን ምን ልንኾን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች: በየሕሊናችን ተፈጥረውብናል፤ ስለእነዚህ: ምሥጢር ስለኾኑብን ጥያቄዎች: አያይዘህ የምትገልጽልን እውነታ ቢኖር: ያን ለመስማት እንጓጓለን።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

መልስ:- በዚህ ጥያቄያችሁ አቀራረብ: እግዚአብሔርን: እንደገና አመሰግነዋለሁ: የማመሰግነውም: በዚያ: ለሰዎች: የአጋጣሚ በሚመስለው: በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ታቅዶ በተፈጸመው: ግንኙነታችን የጀመርነው ውይይታችን: እናንተን: ለዚህ: ቅን ፍላጎትና የእውቀት ደረጃ አድርሶ: ይህን የመሰለ ጥልቅነት ያለውን ጥያቄ ለማቅረብ በመቻላችሁ ነው፡ ስለእናት አገራችሁ ኢትዮጵያና ስለራሳችሁ ኢትዮጵያዊነት: እውነቱን ለማወቅ: የቱን ያህል እንደተጨነቃችሁበት: ይህ ምግባራችሁ: ራሱ በቂ ማስረጃ ኾኖ ይመሰክራል:: ይህን ካልሁ በኋላ: ወደጥያቄያችሁ መልስ አመራለሁ::

ሙሴ: ምንም እንኳ በትውልዱ: የአብርሃም ዘር: እሥራኤላዊ ቢኾንም: የተወለደውና እስከአርባ ዓመት ዕድሜው ድረስ የኖረው: የተማረውና የሠለጠነውም: በግብፅ ምድር: በዚያው አገር አምልኮና ባህል ስለነበረ: ያ: የግብፃውያን ልማድ አይሎበት ይኹን: ወይም: ለዕብራውያን: በአብርሃም ምክንያት እንዲጸና የተደረገውን የግርዛትን ቃል ኪዳን: በማቃለል ቸል ብሎት ይኹን: ወይም: የልጁን ጤንነት የጠበቀ መስሎት ይኹን: ወይም: ሌላ ምክንያት ኖሮት እንደኾነ ባይገለጽም: ከልጆቹ: በኩር የኾነውን ሳያስገርዝ ቀርቶ እንደነበረ ይታወቃል:: "የግርዛት ቃል ኪዳንህን አክብረህ ባለመፈጸምህ: ከፈርዖን የበኩር ልጅ በፊት: የሚሞተው: የአንተ የበኩር ልጅ ነው!" ብሎ: እግዚአብሔር አምላክ: ሙሴን ሊያስደነግጠውና መለኮታዊ ቃል ኪዳንን ማፍረስ: ምን ዓይነት ጠንቅን እንደሚያስከትል ሊያሳየው: በጥፋቱም ተጠያቂነቱ: የእርሱ መኾኑን ሊያሳውቀው: የሞቱ ፍርድ የታዘዘው: በእርሱ : በራሱ: በሙሴ ላይ በመኾኑ ይረጋገጣል::

ኢትዮጵያዊት ሚስቱ: ሲጳራ ግን: ከእግዚአብሔር ታዝዞ: በባሏ: በሙሴ ላይ: ቅጣቱን ሊፈጽም የቀረበው መልአከ ሞት: በምን ምክንያትና ለምን ተልእኮ እንደመጣ: ወዲያው ስላወቀች: በኢትዮጵያዊትነቷ: ጥንት: ከአብርሃም በፊት ሳይቀር: እስከአባቷ: እስከካህኑ ዮቶር ድረስ: በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ ተከብሮና ተጠብቆ የቆየውን: የግርዛት ቃል ኪዳን: ሥርዓቱን: በለመደችው ዘዴና መሣሪያ: ፈጥና: በራሷ እጅ ፈጸመች:: በዚህ የቃል ኪዳን ታማኝነት ምግባርዋም: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጸመች፣ የባሏንም ሕይወት አዳነች፣ ለወገኖቿ ኢትዮጵያውያንም: አብነትና መኩሪያ ኾነች: ኢትዮጵያውያን: ከእሥራኤላውያን በፊት: የእግዚአብሔር የበኩር ልጆች መኾናቸውንም አስመሰከረች::

*"እሥራኤል: የበኩር ልጄ ነው!"* የሚለው የእግዚአብሔር ቃል: "ጣዖት ከሚያመልኩት: ከአረማውያኑ አሕዛብ መካከል: ሰማይንና ምድርን: የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም በፈጠረው: በአንድ: በእግዚአብሔር አምላክ በማመን: የጣዖት አምላኪው: የታራ ልጅ: አብርሃም: የመጀመሪያው አማኝ ኾነ!" ማለት መኾኑን: አስተውሉት! "በእግዚአብሔር ማመን" ደግሞ: በቃል ኪዳን: ወይም: በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ "የእግዚአብሔር ልጅ መኾን" ማለት ስለኾነ: በአብርሃምና በልጁ: በይስሐቅ፡ በልጅ ልጁና "እሥራኤል" በተባለውም: በያዕቆብ ቃል ኪዳን ምክንያት: የእሥራኤል ሕዝብ: "የበኩር ልጄ" የሚለውን ክብር ለማግኘት ዕድሉ ተሰጥቷቸው እንደነበረ ይታመናል።

# ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት፡፡
## ስለኢትዮጵያና ስለእሥራኤል የበኵር ልጅነት ትርጓሜ፡፡

ይህም፡ እግዚአብሔር፡ በሙሴ መሪነት፡ የእሥራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ ካወጣቸው በኋላ፡ ገና በሲና ምድረ በዳ ሳሉ፡ ሙሴን፡ በተራራው ጠርቶ፡ "ለእሥራኤል ልጆች፡ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡- ቃሌን፡ በእውነት ብትሰሙ፡ ኪዳኔንም፡ ብትጠብቁ፡ ምድር ኹሉ፡ የእኔ ናትና፡ ከአሕዛብ ኹሉ፡ የተመረጠ ርስት ትኾኑልኛላችሁ!" በሚለው የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅስ፡ "ወተወክፎ ለእሥራኤል ቍልዔሁ፡" ማለትም፡ "ብላቴናውን እሥራኤልን ተቀበለ!" ስትል፡ "ኢትዮጵያ" የኾነችው፡ ድንግል ማርያም፡ መንፈስ ቅዱስን ተመልታ፡ በተናገረችውም ቃል ይታወቃል፡፡[፴፱]

እነርሱ ግን፡ "እሥራኤል፡ የበኵር ልጄ ነው!" የሚለውን፡ ይህን፡ የትንቢት ቃል፡ አክብረው በመቀበል፡ ሊጠቀሙበት ባለመፈለጋቸው፡ መለኮታዊውን የልግሥና በረከት ሲያጡት፡ የሰማያዊ አባቱ፡ የእግዚአብሔር አብና የኢትዮጵያዊት እናቱ፡ የድንግል ማርያም፡ የበኵር ልጅ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ተፈጻሚነትን ሊያገኝ በቅቷል፡፡ ይህንም፡ "እነሆ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ በሕልም፡ ለዮሴፍ ታይቶ፡ "ሄሮድስ፡ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና፡ ተነሣ! ሕፃኑን፡ [ኢየሱስ ክርስቶስን] እና እናቱን፡ [ድንግል ማርያምን] ይዘህ፡ ወደ ግብፅ ሽሽ! እስክነግርህም ድረስ፡ በዚያ ተቀመጥ!" አለው፡ እርሱም፡ ተነሥቶ፡ ሕፃኑንና እናቱን፡ በሌሊት ያዘና፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ በነቢይ፡ "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት!" የተባለው እንዲፈጸም፡ ወደ ግብፅ ኼደ፡ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ፡ በዚያ ኖረ፡፡" ሲል፡ ወንጌላዊው በጻፈው ሕያው ቃል አረጋግጦታል፡፡[፵]

ሕፃኑና እናቱ፡ ከዮሴፍና ሰሎሜ ጋር፡ በግብፅ ምድር የቆዩባት፡ "ደብረ ቍስቋም" የተባለችው፡ የተቀደሰችው ቦታ፡ ኢትዮጵያውያን፡ በገዳማዊነት ይኖሩባት የነበረች፡ የኢትዮጵያውያን ንብረት ስለነበረች፡ ትንቢቱን ለመፈጸም፡ እናትና ልጁ፡ በግብፅ ምድር ሳይቀር፡ መርጠው፡ ስደታቸውን ያሳለፉት፡ በወገኖቻቸው፡ በኢትዮጵያውያን መካከልና የኢትዮጵያውያን ንብረት በኾነችው ገዳም ውስጥ በመኾኑ፡ በኢትዮጵያ ምድር እንደተገኙ ማስቆጠሩ አያከራክርም፡፡[፵፩]

በእሥራኤል አንጻር፡ ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ ደግሞም፡ የልዑል እግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ የነበረው፡ በዚህ መብትና ሥልጣኑም፡ አብርሃምን ባርኮ፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የመልከ ጼዴቅ ልጆች በመኾናቸው፡ ከእግዚአብሔር ያገኙት የበኵር ልጅነት ቀዳሚነታቸው አያጠያይቅም፡፡ እግዚአብሔርም፡ በነቢያቱ አንደበት ያናገረው ቃል፡ ይህን የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ማንነት፡ ማለትም፡ ከእሥራኤል በፊት የነበራቸውን ቀዳሚነት ለማረጋገጥ መኾኑ፡ አይታበልም፡፡

በዚህ ረገድ፡ በዘመን ብሉይ የተነገረው፡ የነቢያቱ ቃል፡ "እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም!"፡ "ወወሀብከሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ!"፡ "ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ!" ማለትም፡ "በንጉሥነቱ ለምነው፡ በአምልኮ ለሚሰግዱለትና በእውነት ለሚገዙለት፡ እርሱም፡ ምግባቸውን አትረፍርፎ ለሚሰጣቸው፡ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ፡ እግዚአብሔር፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አንሥቶ፡ ምንጊዜም ንጉሣቸው ነው!"

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ደግሞም፡ "የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ፡ ለእኔ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር።" የሚለው ሲኾን፡ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኹለት ልጆች ያሉትን፡ ቸር፡ ርኅሩኅና መሓሪ አባት፡ በምሳሌነት አቅርቦ፡ ያስተማረው ትምህርት፡ በአባትዬው፡ እግዚአብሔርን፡ በታላቁ ታማኝ ልጁ፡ ኢትዮጵያውያንን፡ በታናሹ አጥፊ ልጁም፡ እሥራኤላውያንን ማመልከቱ መኾኑን፡ እናንተም፡ ይህን ቁም ነገር፡ ልታስተውሉት እንደሚገባችሁ ላሳስባችሁ እወድዳለሁ።

ከአዳምና ሔዋን የዘር ግንድ ሥርያ፡ በኹለት ዋና ዋና ዘርፎች ከተከፈለውና በቃየል በኩል ከወረደው፡ ከአንደኛው የትውልድ ሐረግ የተገኙት ወገኖች፡ "የሰው ልጆች" ተብለው፡ እስከኖኅ ዘመን ድረስ ከኖሩ በኋላ፡ በፈጣሪያቸው ላይ በፈጸሙት ክህደት፡ ዓመፅና ምንዝርና ምክንያት፡ በዚያው በኖኅ ጊዜ፡ በጥፋት ውኃ መደምሰሳቸው ይታወቃል። በአቤል ቦታ በተተካው፡ በእሴትና በእግዚአብሔር ስም የመጠራትን ሥርዓት በጀመረው፡ በልጁ፡ በሄኖስ፡ በልጁ፡ በቃይናን፡ በልጁ፡ በመላልኤል፡ በልጁ፡ በያሬድ፡ አካኼዱን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ፡ ሞትን ሳያይ፡ እግዚአብሔር በወሰደው፡ በልጁ፡ በኄኖክ፡ ከሰው ልጆች ዕድሜ፡ የመጨረሻውን ከፍተኛ ዘመን ባገኘው፡ በልጁ፡ በማቱሳላ፡ በልጁ፡ በላሜሕ፡ በልጁ፡ በኖኅና በሚስቱ፡ በሃይከል በኩል ከወረደው፡ ከመደበኛው የትውልድ ሐረግ የተገኙት፡ ሦስቱ ልጆቹ፡ ሴም፡ ካምና ያፌት፡ ከሦስቱ ሚስቶቻቸው ጋር፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለው፡ በእግዚአብሔር ላይ በነበረው ሃይማኖታቸው ጸንተው፡ በጽድቅ ምግባራቸውም ጠንክረው በሥሩት መርከባቸው፡ ከጥፋቱ ውኃ መትረፋቸውም፡ እነሆ፡ ሲነገር ይኖራል።

ከኖኅ በኋላ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የመኾኑ ውርስ፡ ዓፅመ አበውንና ቅዱሳት ቅርሶችን፡ ከኖኅ በተረከበው፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ማለትም፡ ከሴም፡ ከካምና ከያፌት ዘሮች የጋብቻ ውሕደት በተገኘው፡ በመልከ ጼዴቅና በልጆቹ፡ በኢትዮጵያውያን በኩል ሲቀጥል፡ "የሰው ልጆች" የሚያሰኘው፡ የአሕዛብነት ውርስ ደግሞ፡ በዔቦር፡ "ዕብራውያን" በተባሉት፡ ወገኖች በኩል፡ ጣዖት ያመልክ እስከነበረው፡ እስከአብራም አባት፡ እስከታራ ድረስ የወረደው መኾኑን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ ያሳያል።

ለዚያውም ቢኾን፡ እውነተኛ የአብርሃም ልጅነቱን፡ እውነተኛ እሥራኤላዊነቱንና እውነተኛ ይሁዲነቱንም ቢኾን፡ ኢትዮጵያውያን፡ እንደንግሥት እናታቸው ድንግል ማርያምና እንደንጉሡ አባታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገና፡ ከኪዳነ ኦሪቱ ጀምሮ፡ ከነቃል ኪዳኑ ተረክበውት ይኖሩበታል።

ከሚጠፋው ሥጋዊ መብልና ፍትወት ይልቅ፡ የማይጠፋውን የእግዚአብሔርን የሕይወት ቃልና ፈቃድ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ስለመረጡ፡ ኢትዮጵያውያን፡ "እሥራኤል" የተባለው፡ የያዕቆብ፡ እውነተኞች ልጆች ናቸው እንጂ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘውን፡ ብኩርና፡ በመብል አሳልፎ የሰጠው የዔሳው ልጆች አለመኾናቸውን ሊታውቁ ይገባችኋል።

## እሥራኤል፡ ከኢትዮጵያውያን ስለተማሩት ሥርዓተ መንግሥት።

ጥያቄ፡- *ከዚህ ቀደም ብለህ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መታወቂያ ስለኾኑት፡"ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" እና "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" በሚሉት ቅዱሳት ቃላት መነሻነት፡ ኢትዮጵያዊው፡ "በሥነ መንግሥት አስተሳሰቡ፡ ጥንት፡ በእባቡ ዲያብሎስ፡ ኋላም፡ በአዳምና ሔዋን፡ በመካከሉም፡ በእሥራኤል ሕዝብ የተደረገውን የመሰለ ክህደት፡ ዓመፅና ምንዝርና፡ በእርሱም ዘንድ ተፈጽሞ፡ እንደነዚያ በደለኞች፡ ለጥፋት እንዳይዳረግ፡ የቃል ኪዳን ጸሎቱ ያስታውሰዋል" ያልኸውን መግለጫ፡ እዚህ ላይ ብታብራራልን?*

መልስ፡- በቀድሞ ስሙ፡ "ሳጥናኤል" ይባል የነበረው ዲያብሎስ፡ በፍጡርነቱ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የነበረውን፡ የመልአክነት ደረጃና ክብር ያጣው፡ ሌላ የራሱን መንግሥት ለመመሥረት በማሰቡ እንደነበረ፡ ከእርሱ ውድቀት በኋላም፡ አዳምና ሔዋን፡ የእርሱን ፈለግና ምክር በመከተል፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በመልካም ሕይወት መኖርን ትተው፡ የራሳቸውን መንግሥት ለማቋቋም በመፈለጋቸው መኾኑን፡ ካለፉት ውይይቶቻችን ተረድታችኋል። የእሥራኤል ልጆችም፡ እግዚአብሔር፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን አስታጥቆ በላከው፡ በአገልጋዩ፡ በሙሴ እጅ፡ በምድረ ግብፅ ከነበሩበት የባርነት አገዛዝ ነጻ ካወጣቸው በኋላ፡ ወዲያው የቀይ ባሕርን እንደተሻገሩ፡ የሙሴ አማት ዮቶር፡ ራሱ፡ ሙሴ ጭምር ባለበት፡ ለእሥራኤል ሽማግሌዎች፡ ኢትዮጵያውያን ይመሩበትና ይተዳደሩበት ስለነበረው፡ ስለእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት አስተምሮአቸው እንደነበረ የሚያረጋግጠውን የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት፡ አንሥተን የተነጋገርን መኾናችንንም ታስታውሱታላችሁ።

የእሥራኤል ልጆች ግን፡ በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ቸርነትና የምሕረት ኃይል፡ በሙሴ መሪነትና በኢያሱም አስፈጻሚነት፡ "ምድረ ርስት" የተባለችውን፡ የከነዓንን አገር ከወረሱ በኋላ፡ ያን፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር የተማሩትን፡ በእርሱና በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራም ምክንያት፡ ኢትዮጵያዊነትን ከተቀበለው፡ ከሙሴ ያገኙትን፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ መንግሥት፡ በማቃለል ትተው፡ ከአምላካቸው ጋር የተጋቡትንም ቃል ኪዳን አፍርሰው፡ በነቢዩ ሳሙኤል ዘመን፡ የሰውን አገዛዝ ስለመረጡ፡ ለመቼውም ጊዜ ሊድኑ ካልቻሉበት የጥፋት አዘቅት ውስጥ ወድቀው፡ ይኸው እስከዛሬ፡ የሰላም መፍትሔን ባጣ፡ የጣር ህልውና እየተሠቃዩ የመኖር ዕጣቸውን በመቀበል መቀጠላቸውን፡ እነሆ፡ የዛሬው ትውልድ ይመለከታል።

ለዚህም ዕድል የዳረጋቸው፡ የራሳቸው ፍላጎት፥ ምርጫና ውሳኔ መኾኑን፡ ከዚህ የሚከተለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እያረጋገጠ ይነግረናል፡-

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"የእስራኤል ሽማግሌዎች ኹሉ ተሰብስበው፡ ወደሳሙኤል መጡና፡ "እነሆ፡ አንተ ሸምግለሃል፡ ልጆችህም፡ በመንገድህ አይኼዱም፡ አኹንም፡ እንደአሕዛብ ኹሉ፡ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን!" አሉት።

"'የሚፈርድልን ንጉሥ ስጠን!' ባሉት ጊዜ፡ ነገሩ፡ ሳሙኤልን አስከፋው፡ ሳሙኤልም፡ ወደእግዚአብሔር ጸለየ።

"እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፡- "በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ፡ እኔን እንጂ፡ አንተን አልናቁምና፡ በሚሉህ ነገር ኹሉ፡ የሕዝቡን ቃል ስማ! ከግብፅ ካወጣኋቸው ቀን ጀምሮ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ እኔን ትተው፡ እንግዶች አማልክትን በማምለካቸው፡ እንደሠሩት ሥራ ኹሉ፡ እንዲሁ በአንተ ደግሞ ያደርጉብሃል። አኹንም፡ ቃላቸውን ስማ! ነገር ግን፡ ጽኑ ምስክርን መስክርባቸው! በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን የንጉሡን ወግ ንገራቸው!""

"ሳሙኤልም፡ የእግዚአብሔርን ቃል ኹሉ፡ ንጉሥን ለፈለጉት ሕዝብ ነገራቸው፡ እንዲህም አለ፡- "በእናንተ ላይ የሚነግሠው፡ የንጉሡ ወግ ይህ ነው፡- "ወንዶች ልጆቻችሁን ወስዶ፡ ሠረገለኞችና ፈረሰኞች ያደርጋቸዋል፡ በሠረገሉቹም ፊት ይሮጣሉ፡ ለራሱም፡ የሻለቆችና የመቶ አለቆች ያደርጋቸዋል፡ እርሻውንም፡ የሚያርሱ፡ እህሉንም፡ የሚያጭዱ፡ የጦር መሣሪያውንና የሠረገሉቹንም ዕቃ የሚሠሩ ይኾናሉ። ሴቶች ልጆቻችሁንም ወስዶ፡ ሽቶ ቀማሚዎችና ወጥ ቤቶች፡ አበዛዎችም [እንጀራ ጋጋሪዎች] ያደርጋቸዋል።

"'ከእርሻችሁና ከወይናችሁም፡ መልካም መልካሙን ወስዶ፡ ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል። ከዘራችሁና ከወይናችሁም፡ አሥራት ወስዶ፡ ለጃንደረቦቹና ለሎሌዎቹ ይሰጣቸዋል።

"'ሎሌዎቻችሁንና ገረዶቻችሁን፡ ከከብቶቻችሁና ከአህዮቻችሁም፡ መልካም መልካሞቹን ወስዶ ያሠራቸዋል። ከበጎቻችሁና ከፍየሎቻችሁ፡ አሥራት ይወስዳል። እናንተም፡ ባሪያዎች ትኾኑታላችሁ።'

"'በዚያም ቀን፡ ለእናንተ ከመረጣችሁት ከንጉሣችሁ የተነሣ፡ ትጮኻላችሁ፤ በዚያም ቀን፡ እግዚአብሔር አይሰማችሁም።'"

"ሕዝቡ ግን፡ የሳሙኤልን ነገር ይሰማ ዘንድ፡ "እምቢ!" አለ፡ "እንዲህ አይኹን! ነገር ግን፡ ንጉሥ ይኹንልን፡ እኛም ደግሞ፡ እንደአሕዛብ እንኾናለን፤ ንጉሣችንም፡ ይፈርድልናል፤ በፊታችንም ወጥቶ፡ ስለእኛ ይዋጋል።" አሉት።

"ሳሙኤልም፡ የሕዝቡን ቃል ኹሉ ሰማ፡ ለእግዚአብሔርም ተናገረ።

"እግዚአብሔርም፡ ሳሙኤልን፡- "ቃላቸውን ስማ! ንጉሥም አንግሥላቸው!" አለው።

"ሳሙኤልም፡ የእስራኤልን ሰዎች፡- "እያንዳንዳችሁ፡ ወደከተማችሁ ኺዱ!" አላቸው።"

## ምዕራፍ ፪፡ ሃይማኖት።
## እሥራኤል፡ ከኢትዮጵያውያን ስለተማሩት ሥርዓተ መንግሥት።

የእስራኤል ልጆች፡ ያን፡ በሙሴ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉትን ቃል ኪዳን፡ እንዲያ፡ ንቀውና ተጻፍረው በመተላለፋቸው፡ የቅጣቱን ጽዋ፡ ይኸው፡ ያለማቋረጥ እየተጎነጩት እንደሚገኙ ትመለከታላችሁ፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የዚህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ዕድል ፋንታው፡ ይኸው ዓይነት ኾኖ ይታያል፡ አዎን! ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ኢትዮጵያውያን አባቶቹና እናቶቹ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት፡ አገርነትና ሕዝብነት፡ ጸንተው ለመኖር፡ ራሳቸው ፈልገውና መርጠው፡ ፈቅደውና ተስማምተው፡ ከቃል ኪዳን ፈጣሪያቸው ጋር ያደረጉትን፡ ለዘንተ ዓለምም፡ አክብረው፡ ጠብቀውና አቆይተው ያስረከቡትን ቅዱሱን ኪዳን ክዶና በዚያ ላይ ዓምፆ፡ ከእግዚአብሔር ካገኘውና የራሱ ከኾነው ሥርዓተ መንግሥት ይልቅ፡ "የባዕዳኑ ይሻለኛል!" ብሎ፡ ያን በመሻት፡ በዚያውም ላይ ሲያመነዝር በመገኘቱ፡ ለዚህ ድርጊቱ፡ እነሆ፡ በእስራኤል ላይ እየደረሰ ያለውን የመሰለውን ዋጋ እየከፈለ መኾኑን፡ ራሳችሁም ምስክሮች ናችሁ።

## ጠላት፡ በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ስላደረሰው ጠንቀኛ ጥቃት።

ጥያቄ፡- [ኹለቱም ወጣቶች፡ የያዙትን አንድ መጽሓፍ ገልጠው እየተመለከቱ፡] *ሰንደቅ ዓላማችንን በሚመለከት፡ ቢቃል ኪዳን ጸሎታችን ሓተታ ውስጥ፡ ከሰጠኸን ማብራሪያና ከቀደሙት መጻሕፍትህ መካከል፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፍረጃ!" በሚለው ውስጥ፡ እንዲህ ሲል ከሚነበበው ጥቅስ ጋር የተያያዘ፡ ተጨማሪ ጥያቄን እንድናቀርብልህ ፍቀድልን! ይህም፡-* "ጉልተው የሚታዩት የቀስተ ደመናው ሦስቱ ዓበይት ቀለማት፡ ማለትም፡ አረንጓዴ፡ ብጫና ቀይ ሲኾኑ፡ የውዳሴ ማርያሙ፡ የአንድምታ ትርጓሚ ግን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሌለውን፡ 'ደመና በዞረ ጊዜ፡ ዐራት ኅብር አድርጌ፡ ቀርፀዬ አሳይሃለሁ፡ ይኸውም፡ ነጭ፡ ቀይ፡ ብጫ፡ ጥቁር ነው።' የሚለውን ትርጉምና ሓተታ ሰጥቶ ሲያብራራ እናገኘዋለን።" *የሚለውን ሓረግ፡ መነሻ የሚያደርገው ዓቢይ ዐረፍተ ነገር ነው።*

*ከዚያ አያይዞም፡* "ዓለሙ ጭምር በተቀበለው፡ በራሷ የኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቦ ለሚገኘው፡ ለእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል፡ ፈጽሞ የሌለና የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት፡ ደግሞም፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ አረንጓዴ፡ ብጫና ቀይ ኾኖ፡ በጉልህና በገሃድ የሚያየውን የቀስተ ደመናውን ኅብረ ቀለማት፡ በጥቁርና በነጭ በመለወጥ፡ እስከዚህ ድረስ ዓይን ያወጣ፡ የሓሰት ድርጊት፡ በድፍረት የተፈጸመው ለምንድር ነው? እንደዛሬው ኹሉ፡ ባዕዳን የኢትዮጵያ ፀሮች፡ ካገር ተወላጆች ከሃዲዎች ጋር በመመሣጠርና በመተባበር፡ ያው፡ ኢትዮጵያና እውነተኞች ልጆቿ ኢትዮጵያውያን፡ ከፈጣሪያቸው ጋር፡ በቅዱሱ ኪዳን የተሣሠሩበትን፡ ከሰባቱ ኪዳናት፡ አንዱ ምልክታቸውና የማንተማቸው አንዱ ክፍል የኾነውን፡ ሰንደቅ ዓላማቸውን፡ የሃይማኖት ደብዛው ሳይቀር ፈጽሞ ለማጥፋት መኾኑ ሊታበል አይቻልም።"

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

"ለመኾኑ፡ ይህ ቅዱሱና ዘለዓለማዊው ቅርሳችን፡ ታሪኩ ተዘርዝሮ፡ ምሥጢሩም ተፍታትቶ ሊነገር የሚገባው፡ መቼና የት፡ በማንስ ነበር? በዚሁ፡ የውዳሴ ማርያሙን በመሰለው ትርጓሜ ላይ፡ የሃይማኖታችን ቅርስ ጠባቂ በኾነችው በቤተ ክህነትና በካህናት አልነበረምን? ነገር ግን በሃይማኖት አንድነት ሰበብ፡ ሠርገው የገቡብን፡ የወዳጅ ጠላቶቻችንና ባላንጣዎቻችን ግብፃውያን፡ እንዴት አድርገው፡ ሲገዘግዙን እንደኖሩ፡ እኛም፡ ጥቃት የማይሰማን፡ ሃይማኖታዊ ቅንዓት የጐደለንና ሐሞተ ቢሶች ኾነን፡ ዝም ብለን አጎብድደን፡ ግፋን ስንቀበል እንደኖርን፡ ይህ ኹኔታ፡ በሚበቃ እየስረዳ ይመሰክርብናል።" የሚለው ትችት ይነበባል።

*ይህን በመሰለ ቃል፡ የተሠነዘረውን ትችት፡ በቀላል ማለፍ፡ ለእውነተኛ ኢትዮጵያዊ ይከብደዋል፡ ለእኛም፡ የሕሊና ሁከትን ፈጥሮብን፡ ይኸው፡ የመንፈስ ዕረፍትን ነሥቶን እንገኛለን፡ ታዲያ! በዚህ ረገድ ያለንን ኢትዮጵያዊ አቋምና የሚሰማንን ኢትዮጵያዊ ቅንዓት፡ እንዴት አድርገህ ነው፡ በበለጠ እውቀትና ማስረጃ አጠናክረህልን፡ በውስጣችን ሰላምና ፀጥታን ልታስገኝልን የምትችለው?*

መልስ፡- ስለሰንደቅ ዓላማችን ነገር፡ በእናንተ በኩል ልትፈጽሙት የሚገባችሁን የግዳጅ ድርሻ አታጓድሉ እንጂ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ እውነቱን አውቃችሁ፡ የውስጥ ሰላማችሁንና ፀጥታችሁን መልሳችሁ ለማግኘት፡ የያዛችሁትንም፡ ኢትዮጵያዊ አቋምና የሚሰማችሁን ኢትዮጵያዊ ቅንዓት፡ በበለጠ የሚያጠናክርላችሁን በቂ ማስረጃ ለመስጠት፡ በእኔ በኩል፡ አያዳግተኝም። በግብፃውያን ላይ፡ ይህን የመሰለው ክስና ውቅስ ሊቀርብ የተገባው ያለምክንያት አይምሰላችሁ! በቂ የኾነ ምክንያት አለ፡ ያንንም ምክንያት፡ እንደሚከተለው ልግለጽላችሁ!

በመሠረቱ፡ የቤተ ክህነታችን ሊቃውንት፡ የሚያሰሙት የአንድምታ ትርጓሜ፡ በየዘመኑ የሚነሣው ትውልድ የሚጠይቀውን የቋንቋና የንግግር፡ የአስተሳሰብና የእውቀት ደረጃን ተከትሎ፡ የመሻሻል ጥራትን የሚያሳይ አይደለም፡ እንዲያው ዝም ብሎ፡ እንደዘመኑ መቅረጸ ድምፅ፡ ያንኑ መደበኛውን ድርሰት፡ በቃል ትምህርት ብቻ ይዞ የሚተላለፍበት በመኾኑ፡ በምሁሩ ተናጋሪና በአድማጩ ጉባኤ መካከል፡ የአለመግባባቱ ችግር፡ በማናቸውም አግጣጫ እየጸና ከመኼድ በቀር፡ የሃይማኖቱም መልእክት፡ በጊዜው በሚኖረው ትውልድ ዘንድ፡ ግልጽነትንና ተቀባይነትን ሳያገኝ ከመቅረቱ በቀር፡ ለችግሩ ማሻሻያ፡ ወይም፡ ከተቻለ፡ ማስወገጃ የሚኾን መፍትሔ ሳይፈለግለት፡ እነሆ፡ ዛሬ ካለንበት ዘመን ደርሰናል።

ስለዚሁ ጠንቅና ስለመፍትሔው፡ ወደፊት የምንወያይበት ኾኖ፡ እርሱን፡ ለጊዜው በዚሁ ደረጃ እናቆመውና፡ ስለሰንደቅ ዓላማችሁ፡ ያላችሁን ኢትዮጵያዊ አቋምና የሚሰማችሁን ኢትዮጵያዊ ቅንዓት እንዲያጠናክርላችሁ፡ የማቀርብላችሁ ማስረጃ፡ ለኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ እስካኹን ምሥጢር ተደርጎበት የኖረውንና በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ ላይ የተፈጸመውን የክህደት አበሳ የሚያረጋግጠውን ይኾናል።

# ምዕራፍ ፪: ሃይማኖት::
## ጠላት: በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ስላደረሰው ጠንቀኛ ጥቃት::

ይኸውም: እኛ ኢትዮጵያውያን: በክርስትና ጥምቀታችን ጊዜ: አንገታችን ላይ በሚታሠርልን: የአረንጓዴ: ብጫና ቀይ ቀለማት ሦስት ፈትሎች ማተብነት: በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ: ከእግዚአብሔር ልናገኘው የሚገባንን የልጅነት ክብር: በረቂቁ ሰይማናዊው ዘዴ እንድንገፈፍ: ደግሞም: በኖኅ አማካይነት: ከእግዚአብሔር የተቀበልነውንና በቀስተ ደመና ምልክትነት: አረንጓዴ: ብጫ: ቀይ የኾነውን: ሰንደቅ ዓላማችንን: በባዕዱ የአምልኮ ምልክት እንድንተካ ተደርጎ ያሳለፍነው የአያሌ ምዕት ዓመታት የባርነት ቀምበር ነው::

ጥያቄ:- እንዴት!? (አሉ: ኹሉቱም ወጣቶች በቍጣ::)

መልስ:- ቆዩ እኮ! Coptic (ኮፕቲክ) እና Orthodox (ኦርቶዶክስ) የሚባሉት ባዕዳን የስያሜ ቃላት: በኢትዮጵያዊነታችንና በሃይማኖታችን ላይ ያመጡብን ጣጣና ጥለውብን ያለፉት ጠንቅ ሳያንሰን: አኹን ደግሞ: በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ በኩል: የተፈጸመብንን ሥውር በደል: እስኪ: በእርጋታ መንፈስ ኾናችሁ አዳምጡኝ!? ይህን በደል: ብዛቱን አሳንሼ: በ፪ ልክፈለው:-

፩ኛ. እኛ ኢትዮጵያውያን: በኖኅ ቀስተ ደመና አማካይነት: ከፈጣሪያችን ያገኘናቸው: የሰንደቅ ዓላማችን ቀለማት የኾኑት: አረንጓዴ: ብጫና ቀይ ቀርተው: በእነርሱ ፋንታ: እስከዛሬዪቱ ቀን ድረስ ጸንቶ እየተሠራበት ያለው: የግብፃውያን ሰንደቅ ዓላማ ምልክት የኾኑትን: "ነጭ: ቀይ: ጥቁር እና ብጫ" ቀለማት እንድንቀበል መገደዳችን ነው:

፪ኛ. ኢትዮጵያውያን ሕፃናት: ትልልቆችም ጭምር: እስካኹን: ክርስትና በሚነሡበት ጊዜ: ጸሎት ተደርጎበት: ከጥምቀቱ በኋላ: በአንገታቸው ላይ ሲታሠርላቸው የቆየውና አኹንም: የሚታሠርላቸው ማተብ: የራሳቸው የቃል ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት የኾኑት: አረንጓዴ: ብጫና ቀይ ሳይኾኑ: የግብፃውያንን ሦስት የሰንደቅ ዓላማ ቀለማትን የያዘው: ቀይ: ነጭና ጥቁር ፈትል መኾኑ ነው::

• በውዳሴ ማርያም የቀለማት ድልድል ትርጓሜ የተሟላው: ይኸው: የግብፃውያን ሰንደቅ ዓላማ: ከዓናት ያለው: የአንዱ የአግድም ጥለት ቀለም: ***ቀይ*** ሲኾን: በግርጌ ያለው ደግሞ: ***ጥቁር***: የመኻሉም: ***ነጭ*** ኾኖ: ዕምብርቱ ላይ: ኹለንተናው ***ብጫ*** (ወርቃማ) የኾነው: "የሳላዲን ንሥር" ንስ የተባለውን ምሥል የያዘው ብሔራዊ ማንተማቸው ሠፍሮበት ይገኛል::

በግብፃውያን ጳጳሳት ሥር እንድትመራ የተደረገችው የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሊቃውንት: ይህን ደባ: በአንድምታ ትርጓሜ አስታክከው: በየዓመቱ: በጾመ ፍልሰታ ሱባዔ: በሚካኼደው የምእመናን ጉባኤ ላይ፥ በይፋ በሚያሰሙት ቃል ሲፈጽሙት መኖራቸው: "መቸም: ይኼ: የዋህና ያልተማረ ሕዝብ: እኛ የምንለውን ኹሉ: ከመቀበል በቀር: ለማወቅና ለመረዳትም እንኳ ቢኾን: 'እስኪ ልጠይቅ!' የሚል ልማድ ስለሌለው: እኛ: የፈቀድነውን ማድረግ እንችላለን!" በሚለው፥ ተቀባይነትም ባገኘው ሥልጣናቸው በመተማመን: ከባዕዳኑ ባላጋራዎቻችን ጋር ተባብረው መኾኑ ይታወቃል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይኹን እንጂ፡ ኢትዮጵያና የቃል ኪዳን ሕዝቧ፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከፈጣሪያቸው በቀስተ ደመና የተቀበሉትን፡ የአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ባለሦስት ደማቅ ቀለማት ሰንደቅ ዓላማቸውን፡ እንኳንስ ወደሌላ መለወጥ፡ በነቍጥ እንኳ ሳያስነኩ፡ እነሆ፡ እስከዛሬ ጠብቀውት ይገኛሉ።

እግዚአብሔር ወልድ፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ በሰውነቱ በተቀበለው ፈተናና መከራ፡ የከፋትን ኃይል፥ በመስቀል ላይ በቆረሰው ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙም፡ የኃጢአትን ጠንቅ፥ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ፡ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱም፡ የሞትን ፍዳና ሙስና መቃብርን ደምስሶና አጥፍቶ፡ በታላቅ ድል አድራጊነት የዋጀውን፡ ለእርሱ የቃል ኪዳን ዜጋው፥ ለቅድስት እናቱም፡ በስሟ ተጠርቶ፡ ርስቷ፥ ጕልቷ የኾነውን፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ፡ ዲያብሎስ፡ በዚህ መልክ፡ እንዴት አድርጎ፡ በረቂቅ ስልት ገብቶ፡ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷን ኢትዮጵያዊት፡ በነፍስ ወከፍ፡ ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ፡ ነጥቆ ሊወስድ እንደሞከረ ተመልከቱት!

ነገር ግን፡ አልተቻለውም፤ አይቻለውምም። ነቢዩ፡ *“ይትዓየን መልአከ እግዚአብሔር ዐውደሙ፤ ለእለ ይፈርህዎ ወያድኅኖሙ፤ ጥዕሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብሔር።”* ማለትም፡ *“የእግዚአብሔር መልአክ፡ በፈጣሪያቸው ታምነው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚያመልኩትን ኹሉ፡ ከሠራዊቱ ጋር፡ ዙሪያቸውን ከብቦ ይጠብቃቸዋል፤ ያድናቸዋልም። ስለዚህ፡ እንዲህ የሚያደርግ እግዚአብሔር፡ እንዴት ቸር እንደኾነ እወቁ! አስተውሉም!”* እንዳለው፡ የእርሱ የኾኑትን ኹሉ፡ ቀን፡ በደመና ዓምድ፥ ሌትም፡ በእሳት ዓምድ ሠውሮ የሚጠብቀው ቅዱሱ ኪዳን፡ እነሆ፡ ኢትዮጵያውያንን፡ እስከዛሬ ጠብቋቸው፡ በኢትዮጵያዊነት ህልውናቸው ሊቀጥሉ ችለዋል።[፵፪]

<u>ዛሬ፡ “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” የሚለው፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፥ ወንድ ኾነ ሴት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ታማኝ መኾኑን ለማረጋገጥ፡ የቃል ኪዳን ምስክርነቱን በይፋ ከሰጠ በኋላ፡ የኢትዮጵያዊው ሰንደቅ ዓላማ ሦስት ቀለማት የኾኑት፡ የአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ኅብር ያላቸው ሦስት ፈትሎች የተዋሐዱበትን ማተብ፡ በአንገቱ ላይ እንዲያሥር የሚደረገው፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑን ልታውቁት ይገባል።</u>

*ጥያቄ፡- ይህን የመሰለውን ጉዳችንን፡ ሌላው ቢቀር፡ ኃላፊነቱና አደራው፡ ከፈጣሪዋ የተሰጣት ቤተ ክህነታችን፡ እንዴት እስከዛሬ ሳታውቀው፥ ካወቀችውም፡ እንደምን ሸፍናውና ደብቃው ለመቆየት ቻለች? ለዚህስ ታላቅ በደል፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ጭምር ተጠያቂው ማነው? እንደድፍረት አይቆጠርብንና፥ ለዚህም፡ እንደገና ይቅርታን ታደርግልን ዘንድ እንድንጠይቅህ ፍቀድልንና፡ አንተስ፡ በነበረህ ኃላፊነት፡ እንዴት ይህን ግዳጅህን ለመወጣት ሳትችል ቀረህ?*

## ምዕራፍ ፱፡ ሃይማኖት።
## ጠላት፡ በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ስላደረሰው ጠንቀኛ ጥቃት።

---

መልስ፡- በመጀመሪያ ነገር፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ በግልጽ መወያየቱንና መጠያየቁን፡ ቀደም አድርገን ጀምረነውና ተለማምደነው ቢኾን ኖሮ፡ በሥጋዊዉም፡ በነፍሳዊዉም፡ በመንፈሳዊዉም ህልውናችን፡ ዛሬ ተዳርገን ከምንገኝበት ሙስናና ጉሥቍልና ከመዘፈቅ ድነን፡ በመልካም ሕይወት ለመኖር በቻልን ነበር፡ ነገር ግን፡ ይህ ሳይኾን ቀርቷል፤ ዕድሉም፡ አንዴ አምልጦናል። በትንሣኤ የምናምን ስለኾን፡ በክህደት፡ በዓመፅና በአመንዝራነት የተጎዳ ሃይማኖታችንንና ምግባራችንን፡ በእውነተኛ ንሥሓ ካስተካከልነውና ካደስነው፡ በግልጽ ውይይታችንም፡ እንዲህ ከቀጠልን፡ እንደገና አንሠራርተንና ተጠናክረን፡ ከወደቅንበት ልንነሣ፡ በኹለቱም እግራችን ልንቆምና በጤናማው የዕድገት ጎዳና ላይ ወደፊት ልንራመድ ይቻለናል።

በበደሉና በጥፋቱ፡ የዚህ ትውልድ አባሎች የኾንነው ኹሉ፡ በኃላፊነቱ ተጠያቂዎች ነን፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ በነፍስ ወከፍ፡ እንደየዓቅሙ፡ በኃላፊነት ከመጠየቅ ሊያመልጥ የሚችል አይኖርም። በእኔም በኩል፡ የተጠያቂነት ድርሻ አለኝ ማለት ነው። በዚህ፡ በአኹኑ ተልእኮዬ፡ ይኸው፡ ያለብኝን የግዴታ ድርሻዬን እየተወጣሁ ይመስለኛል። በዚህ መልክ፡ በግልጽ እየተወያየን፡ በየግላችን ሳናውቃቸው የቆዩት ጥፋቶቻችን፡ ጉድለቶቻችንና ስሕተቶቻችን፡ እንዲህ ከተደበቁበት እንዲወጡ ለማድረግ የተቻለው እኮ፡ ይህ፡ እንደደራሽ የውኃ ማዕበል ያጥለቀለቀን፡ እንደ ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስ ያናወጸን፡ እንደእሳተ ገሞራም ፈንድቶ የነደደብን የጥፋት መከራ ሳናስበው በድንገተኛ ስለደረሰብን ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ከውጭ ግዙፍ ወራሪ ሳይመጣብን፡ እነሆ፡ እርስ በርሳችን፡ በጠላትነት ተነሣሥተን፡ በራሳችን ጦር ኃይል፥ ሠራዊትና መሣሪያ፡ የብዙ ወገኖቻችን ደም ፈሰሰ፤ ብዙዎች፡ ታሠሩ፤ በግፍ ተገደሉ፤ ተሠቃዩ፤ ተራቡ፥ ተጠሙ፡ ታመሙ፡ ደኸዩ፡ ተራቆቱ፤ ቤትአልባ ኾኑ፡ ተሰደዱ፤ በአራዊት ተፈጁ፡ በእርስ በርስ ጦርነት ተላለቁ። በአጠቃላይ፡ እጅግ ከፍ ያለ መሥዋዕትነት ተከፈለ።

በዚህ ጊዜ፡ ይህ ኹሉ የጥፋት መከራ ለምን እንደደረሰብን፡ እያንዳንዳችን፡ ሳንወድድ፡ በግድ እንጠይቅ፥ እንፈልግና እንመረምር፥ እናጠናና እንመራመር ዘንድ፡ በጽኑ የሚያስፈልገን ኾነ! አለዚያማ፡ በሽታውን እንደምን አውቀን ልንደርስበት፥ መድኃኒቱንም ልናገኝለት ይቻለናል? ይህ ኹሉ የመቅሠፍት መዓት የወረደብን፡ ያለምክንያት አለመኾኑንና ያም ምክንያት፡ ከራሳችን ክፉ አሳብ መንጭቶ፡ ራሳችን፡ በግብር ላይ ያዋልነው፡ ያው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ በሥውርም ኾነ በገሃድ የፈጸምነው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት በደላችን መኾኑን፡ እኔም በበኩሌ፡ ለማወቅና ለመገንዘብ ቻልሁ፥ ለዚህም ያበቃኝ፡ በሃይማኖታዊ ጽሙናና በመንፈሳዊ ተመስጦ ካካኼድሁት፡ ከዚሁ ጥናቴና ምርምሬ ኾነ! ከዚህ የበደል መዝገባችን ውስጥ፡ ለዚህ ጥናትና ምርምር የቀረበው፡ አንዱ ጠንቅ፡ ይህ፡ በቃል ኪዳን ሰንደቅ ዓላማችን ላይ የተፈጸመው ታላቅ ኃጢአት መኾኑ አያጠራጥርም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህን ኹሉ መከራ ያስከተለብን በደላችን፡ ምን እንደኾነ፡ ተመራምረን እንድናውቀውና ይህንኑም በንስሓ እንድናስተካክለው ያደረገን፥ እያደረገን ያለውም፡ ራሱ፡ ይኸው መከራ እንደኾነ፡ ቀደም ብዬ፡ ባጭሩ ገልጫለሁ፤ ይኹን እንጂ፡ ከዚህ ውድቀታችን ለመዳን እንችል ዘንድ፡ ከኣኹኑ የጥፋት ለውጥ በፊት፡ ልንከተለው ይገባን ስለነበረው መሠረታዊ አመራር፡ በእግዚአብሔር ረድኤት፡ በዓቅሜ፡ የተቻለኝን የበኩሌን የግዳጅ አስተዋጽዖ ያበረከትሁ መኾኔን፡ ባለፉት መጻሕፍቴ ውስጥ፡ አልፎ አልፎ ያመለከትሁትን ታስታውሱታላችሁ፣ ለምሳሌ፡ ሰብአዊው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥታዊ አቋም በፈራረሰ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በኢትዮጵያ ለመሠረታት፡ ለእርሱ መንግሥት መቀጠል፡ "ያስፈልጋል!" ብሎ፡ በቤተ ክህነቱ በኩል ያዘጋጀውን የሰበካ ጉባኤን፡ በመላ ኢትዮጵያ ለማቋቋም፡ በጊዜው፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የነበርሁትን፡ እኔን፡ ታናሹን ልጅ፡ ለዚያ አገልግሎት፡ መሣሪያው እንድኾን የፈቀደበትን ጥሪ፡ እዚህ ላይ፡ እንደአንድ ተጨባጭ ማስረጃ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል።

*ጥያቄ፡- ግብፃውያን፡ ይህን የመሰለ ረቂቅ ጥቃትን፡ እንዲህ ሲፈጽሙብን የኖሩ ከኾነ፡ ሌላም፡ ሊኖር ስለሚችል፡ ይህን ርእስ ከመዝጋትህ በፊት፡ ያን፡ የቀረ በደል፡ ጨርሰህ ብትገልጽልን?*

መልስ፡- በእነርሱ፡ በግብፃውያኑም ኾነ፡ በሌሎቹ ባዕዳን፡ ሲካኼድብንና ሲፈጸምብን የኖረ፡ እጅግ የበዛና የተለያየ ጥቃት መኖሩ አያጠያይቅም፤ ይኹን እንጂ፡ ያን ኹሉ፡ እንግዲህ ወዲህ፡ ፈልጋችሁና ተከታትላችሁ፥ ተመራምራችሁና አጥንታችሁ፡ ገሃድ ልታወጡት የሚገባችሁ፡ እናንተ ናችሁ! ይህንም ለማድረግ ደግሞ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ቅንዓትና ንቃት፥ ቆራጥነትና ጥረት፡ በውስጣችሁ ሊንበለበሉ ግድ ነው፤ አኹንም፡ ይኸው መቀጣጠል መጀመራቸውን፡ እነሆ፡ በይዞታችሁ እመለከታለሁ።

በእኔ በኩል፡ ግብፃውያንን በሚመለከት፡ እዚህ ላይ፡ ላክለው የምፈልገው፡ አንዱን፡ የቅርብ ጊዜ ድርጊታቸውን ብቻ ይኾናል፤ እርሱም፡ ከአጼ ምኒልክ ዘመን አንሥተው፡ እስከንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የቆዩት፡ አቡን ማቴዎስ የሚባሉት ግብፃዊው ጳጳስ፡ የፈጸሙት ድርጊት ነው። ይኸም፡

፩ኛ፡ የኢትዮጵያ ገዳም ርስት በኾነው፥ የሚካኤልና የ፬ቱ እንስሳ ታቦቶች በሚገኙበት በዴር ሡልጣን ይዞታ ላይ ጥያቄ ተነሥቶ ሣለ፡ እኚሁ ጳጳስ፡ ከኢትዮጵያ ወደኢየሩሳሌም ኼደው፡ የዚሁ ይዞታ ንብረትነት፡ የግብፅ እንጂ፡ የኢትዮጵያ እንዳልኾነ በማስመልከት፡ የበሩ ቁልፍ፡ ወደግብፃውያን መነኮሳት እንዲዛወር ሲሉ፡ በጽሑፍ የሰጡት ማስታወሻ፥

፪ኛ፡ ልጅ ኢያሱ፡ ወደእስልምና ሃይማኖት በማዘንበሉ፡ ከሥልጣን እንዲወገድ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው በተወሰነ ጊዜ፡ ውሳኔውን መቀበል ግድ ኾነባቸው እንጂ፡ "እርሱን የከዳውን ሰው፡ ...እንኳን ቃሌ፡ አጥንቴ፡ በመቃብር አይፍታው!" ካሉበት ውግዘታቸው ጋር ስለወንጀሉ፡ በገሃድ የቀረበውን ማስረጃ ባለመቀበል፡ "መስለሙን አላምንም!" ብለው ያስቸገሩበት የእስልምና ደጋፊነታቸው ነው።

\+ + +

# ምዕራፍ ፫፤

## አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

*ጥያቄ፡-* *ስለሃይማኖት ባሕርይና መሠረታዊ ምንነት፡ ይህን ያህል ካስረዳኸን፡ በነፍሳዊው ልባችን ላይ የተጻፈችውና በመንፈሳዊው ልቦናችን ውስጥ ያደረችው፡ ይህችው ሃይማኖት፡ በሥጋዊው አእምሮአችንም ዘንድ፡ እውን ኾናና በሥርዓት ተገልጣ ልትታወቅ የምትችልበት መንገድ እንዳለ፡ ብታሳየን?*

መልስ፡- ይህች፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ተመሥርታ የቆመችባቸውና የምትታወቅባቸው፥ ኅልታም የምትገለጥባቸው፡ አምስት ምሥጢራት አሉ፤ እነርሱም፡ አዕማደ ሃይማኖት ተብለው፡ እንደሚከተለው፡ የተዘረዘሩት ናቸው፡-

፩ኛ፡ ምሥጢረ ሥላሴ፤
፪ኛ፡ ምሥጢረ ሥጋዌ፤
፫ኛ፡ ምሥጢረ ጥምቀት፤
፬ኛ፡ ምሥጢረ ቊርባን፤
፭ኛ፡ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

*ጥያቄ፡-* *እንግዲያማ፡ እነዚህን ምሥጢራት እናውቃቸው ዘንድ፡ ስለእያንዳንዳቸው ልታብራራልን ያስፈልጋል፤ እኛም፡ ልንሰማህ ተዘጋጅተናል። ከዚያ በፊት ግን፡ ትምህርቱና እውቀቱ፡ "ምሥጢር" የተባለበትን ምክንያት ብትገልጽልን ደስ ይለናል።*

መልስ፡- እግዚአብሔር፡ መንፈስ በመኾኑ፡ በመንፈሳዊው አእምሮና ዓይን፥ ጆሮና እጅ ካልኾነ በቀር፡ በነፍሳዊውና በሥጋዊው አእምሮና ዓይን፥ ጆሮና እጅ ብቻ ሊታሰብና ሊታይ፥ ሊሰማና ሊዳሰስ ስለማይቻል፡ ትምህርቱና እውቀቱ፡ "ምሥጢር" ተባለ። "ምሥጢር" የተባለበትን ምክንያት፡ በሦስት ቊም ነገሮች አጠቃልዬ ላስረዳችሁ!

፩ኛ. የእግዚአብሔርን፡ የአንድነትና የሦስትነት ነገር፥ ቀጥሎ፡ ከሦስቱ አካላት አንዱ፡ ሰው የመኾኑን ነገር፥ እንዲሁም፡ ሰው፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የመወለዱን ነገር፥ ደግሞም፡ ሰው የኾነውን አምላክ፡ ሥጋውን በመብላትና ደሙን በመጠጣት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ የመኖርን ነገርና በመጨረሻ፡ ሰው፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወት ወይም ሞት፡ በማይበሰብስ አዲስ አካል፡ እንደገና የመነሣቱን ነገር የሚያስረዳ ጥልቅ የኾነ፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት በመኾኑ ነው፤

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

፪ኛ. ትምህርቱና እውቀቱ፡ እንደሥጋዊ ትምህርትና እውቀት፡ ተጽፎ የሚቀርብና ተነብቦ የሚጠና፥ በሥጋዊው ቊሳቊስ ግዙፍ ማስረጃነት እየተደገፈ የሚሰጥ ሳይኾን፡ በአንድ ወገን፡ ከሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ልቦና፡ በእውነተኛ አምልኮ ፈልቆ የሚናገሩትና የሚያስተምሩት፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በእውነተኛ ፍላጎት ላይ በተመሠረተ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ልቦና ኾነው የሚሰሙትና የሚማሩት፡ ረቂቅ፡ የእግዚአብሔር ነገር ስለኾነ ነው፤

፫ኛ. ለማያምኑ፡ የማይገለጥና የተቈለፈ የብረት ሣጥን፥ ለሚያምኑ ግን፡ በእውነተኛው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ የእውቀት ቊልፍ ከፍተው፡ በዚያው በፍጹሙ ብርሃን ካዩት በኋላ፡ አክብረው የሚጠብቁት፡ "የማይጠፋ ዕንቊ" በመኾኑ ነው::

## ምሥጢረ ሥላሴ::

**ጥያቄ:-** *መልካም! ምሥጢርነቱ፡ እንዲህ ከኾነ፡ ስለእያንዳንዱ ምሥጢር፡ የምትሰጠንን የማብራሪያ ሐተታ፡ በነፍሳዊውና በሥጋዊው አእምሮና ጆሮ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በመንፈሳዊው ጆሮአችን ሰምተን ለማጤን፥ በመንፈሳዊው አእምሮአችንም አስተውለን ለመቀበል እነሆ፡ እንደተለመደው ተዘጋጅተን እንጠብቃለን::*

**መልስ:-** ምሥጢረ ሥላሴ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጠው፡ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያስረዳ ጥልቅ የኾነ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ትምህርት ነው:: መንፈሳዊና እውነተኛ፥ ዘለዓለማዊና ሕያው በኾነው ህላዌውና ባሕርዩ፡ ረቅቆ የሚኖረው፥ የሚሠራውና በፍጥረቱ ገዝፎ የሚታየው፡ እግዚአብሔር፡ ፍጡሩ ሊያውቀውና ሊደርስበት በማይቻለው፡ በማንነቱና በአሳቡ፥ በመለኮትነቱና በጌትነቱ፥ በፈቃዱና በምክሩ፥ በፈጣሪነቱና በባለቤትነቱ፥ በአምላክነቱና በመንግሥቱ፥ በሥልጣኑና በኃይሉ፥ በክብሩና በምስጋናው፡ አንድ ሲኾን፡ "እግዚአብሔር አብ፤ እግዚአብሔር ወልድ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤" ተብሎ፡ በሦስት ስም ይጠራል፤ በሦስት አካል ይገለጣል፤ በሦስት ግብር ተግባሩን ይፈጽማል::

**ጥያቄ:-** *እግዚአብሔር፡ አንድ አምላክ ሲኾን፡ ለምንድር ነው፡ በሦስት ስም መጠራት፥ በሦስት አካል መገለጥና በሦስት ግብር ሥራውን መፈጸም የፈለገውና ያስፈለገው?*

**መልስ:-** እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ አምላክ ሲኾን፡ በሦስት ስም መጠራት፥ በሦስት አካል መገለጥና በሦስት ግብር ሥራውን መፈጸም የፈለገውና ያስፈለገው፡ በዚህ መጽሐፍ፡ ቀዳማዊ ክፍል እንደተገለጸው፡ የህልውናውና የሕይወቱ፥ የእውቀቱና የጌትነቱ፥ የመንግሥቱና የሥልጣኑ፥ የክብሩና የምስጋናው፡ ተካፋይ እንድንኾን፥ እንድናመልከውም፡ በመልኩ፡ በአርአያው ለፈጠረን፡ ለአንተ፥ ለአንቺና ለእኔ፥ በጠቅላላ ለፍጥረቱ ኹሉ፥ በተለይም፡ ለሰው፡ ዘለዓለማዊ ደኅንነትና መልካም ሕይወት ሲል ነው::

# ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥላሴ።

ፈጣሪ፡ በአንድ በእግዚአብሔርነቱ ባሕርይና ህላዌ፡ "አብ" ወይም "አባት" ብቻ ተብሎና ኾኖ መኖር፥ መታወቅም ይችል ነበር፤ ነገር ግን፡ በመጀመሪያ፡ የማይታየውን ረቂቁንና የሚታየውን ግዙፉን ፍጥረቱን፡ በቃሉ ለማስገኘት፥ ለማስተዳደርና ለመጠበቅ፥ በመካከሉም፡ ይኸው ፍጥረቱ፡ በተቃራኒው የክፋት ኃይል አበጋዝነትና በራሱ የስሕተት ምርጫ በጠፋ ጊዜ፡ ሊያድነው፡ በአርአያው በፈጠረው ፍጡሩ መልክ፡ "ወልድ" ወይም "ልጅ" ተብሎና ኾኖ፡ በሥጋ ለመገለጽ፥ በመጨረሻም፡ ቦታ፥ ጊዜና ኹኔታ ሳይወስነው፡ እርሱ፡ ፍጡሩን፥ ፍጡሩም፡ እርሱን፡ በቀጥታ ሊያገኝና በቀላሉ ሊገናኝ እንዲቻለው፡ "መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ ዘንድ፡ መንፈስ ኾኖ ለመስፈን ፈቃዱ ኾነ! ይህንም ፈቃዱን ፈጽሞ፡ እውን አደረገው። በዚህ ረገድ፡ እስካሁን በተነገረውና በተጻፈው፥ ወደፊትም በሚነገረውና በሚጻፈው ዝርዝር ሐተታ፡ በበለጠ ተብራርቶ ታገኙታላችሁ፤ ታውቁታላችሁ፣ ትገነዘቡታላችሁም።

### ስለቅድስት ሥላሴ።

**ጥያቄ:-** *ስለዚህ ምሥጢር፡ ወደሚቀጥለው ዝርዝር ሐተታ፡ ተሻግረህ ሳትኼድ፡ "ቅድስት ሥላሴ" ስለሚባለው አጠራር ብትገልጽልን?*

**መልስ:-** ጥሩ ጥያቄ አነሣችሁ! "ቅድስት ሥላሴ" የሚለው ስያሜ፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር መገለጫ ነው። ይኸውም፡ "ቅድስት"፡ የእግዚአብሔር፡ አንድነቱን፥ "ሥላሴ"፡ ሦስትነቱን ያመለክታል፤ ያረጋግጣል። "ቅድስት"፡ ለአንዲት ሴት፡ በነጠላ ቍጥር የሚሰጥ፥ "ቅዱስ" ደግሞ፡ ለአንድ ወንድ፡ በነጠላ ቍጥር የሚሰጥ፡ ተነጻጻሪ አንቀጹ ነው። መውለድ፡ ለሴት ነውና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ባገኘነው ጸጋ፡ እግዚአብሔር አብ፡ እኛን ሰዎችን፡ በምሥጢረ ጥምቀት፡ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ወልዶን፡ የዘለዓለም ልጆቹ ስላደረገን፡ "ቅድስት" የሚለው ቅጽል ተሰጥቶታል።

**ጥያቄ:-** *እንዲህ ከኾነ፡ የምሥጢረ ሥላሴ ነገር የታወቀው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ መኾኑ ነውን?*

**መልስ:-** እርግጥ፡ የቅድስት ሥላሴ ምሥጢር፡ በነገረ መለኮት፡ በግልጽ ታውቆ፡ በሥርዓተ ሃይማኖት፡ የተወሰነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ነው። ይኹን እንጂ፡ ከዚያ በፊት፡ ጥንት ከመሠረት ጀምሮ፡ በዘመነ ብሉይ፡ ሲነገርና ሲጻፍ የኖረ፥ ከዚያም፡ ሲያያዝ መጥቶ፡ እስከዘመነ ሐዲስ የደረሰ ምሥጢር አለ፤ ምሥጢርነቱ፡ እንግዳ ደራሽ አይደለም። ይህን፡ የፈጣሪን፡ አንድነትና ሦስትነት የሚጠቁም ፍንጭ፡ ቀደም ብሎ ተገኝቷል፤ ይኸውም፡ ከዚህ በሚከተሉት፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ተረጋግጦ ይታወቃል:-

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፩. "እግዚአብሔር፡ 'ሰውን፡ በመልካችን፡ እንደምሳሌአችን እንፍጠር!' አለ። ...ሰውንም በመልኩ ፈጠረ!" በሚለው ቃል፡ "እግዚአብሔር አለ፡ በመልኩ ፈጠረ" ማለቱ፡ "አንድነቱን"[፺፪]፡ "በመልካችን እንፍጠር!" ማለቱ ደግሞ፡ "ሦስትነቱን" ያመለክታል፡

፪. "እግዚአብሔርም አለ፡ 'ኑ፡ እንውረድ! አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው፡ ቋንቋቸውን፡ በዚያ እንደባልቀው!'" በሚለው ቃል፡ "እግዚአብሔር አለ፡" ማለቱ፡ "አንድነቱን"[፺፫]፡ "ኑ፡ እንውረድ!" ማለቱ ደግሞ፡ "ሦስትነቱን" ያሳያል፡

፫. "የእግዚአብሔር ቸርነት፡ ምድርን ሞላች፡ በእግዚአብሔር ቃልም፡ ሰማዮች ጸኑ፡ ሠራዊታቸውም ኹሉ፡ በአፉ እስትንፋስ፤" በሚለው ቃል፡ "እግዚአብሔር" ብሎ ስሙን ደጋግሞ ማንሣቱ፡ "አንድነቱን"፡ "የእግዚአብሔር ቸርነት፡ ምድርን ሞላች፡" ያለው፡ እግዚአብሔር አብን፡ "በእግዚአብሔር ቃልም፡ ሰማዮች ጸኑ፡" ያለው፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ "ሠራዊታቸውም ኹሉ፡ በአፉ እስትንፋስ፡"[፺፬] ያለው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ስለኾነ፡ "ሦስትነቱን" ያስረዳል፡

፬. ኢሳይያስ በትንቢቱ፡ "ሱራፌልም፡ ...አንዱም ለአንዱ፡ 'ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡ የክብሩ ምስጋና በሰማይና በምድር ፈጽሞ የመላ ነው!' እያለ፡ ይጮህ ነበር።" ሲል በተናገረው ቃል መሠረት፡ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" ማለቱ፡ "አንድነቱን"፡ ሦስት[፺፭] ጊዜ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ!" ማለቱ ደግሞ፡ "ሦስትነቱን" ያጠይቃል።

### የእግዚአብሔር አንድነትና በስም ሦስትነት።

ጥያቄ:- እግዚአብሔር፡ በአምላክነቱ፡ አንድ ሲኾን፡ በስም፡ ሦስትነቱ እንደምን ነው?

መልስ:- ፍጥረትን ያስገኘው አምላክ፡ በአንድነት ስሙ፡ "እግዚአብሔር" ይባላል፡ የዚህ የአንድነት ስሙ ትርጉም፡ በመጀመሪያው ውይይታችን ላይ ስለተብራራላችሁ፡ አውቃችሁታል። በሦስትነት ስሙም፡ "እግዚአብሔር አብ፤ እግዚአብሔር ወልድ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤" ይባላል። ይህ የግእዙ ቃል ሲተረጐም፡ "አብ = አባት[፺፮]፤ ወልድ = ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ = ቅዱሱ የእውነት መንፈስ" ማለት ነው።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ሥላሴ። ስለቅድስት ሥላሴ።

### የእግዚአብሔር አንድነትና በስም ሦስትነት።

---

እግዚአብሔር አብ፡ "አባት" እና "አሥራፂ" ማለት ነው፤ እርሱም፡ የእግዚአብሔር ወልድ አባት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አሥራፂ ነው። እግዚአብሔር ወልድ፡ "ልጅ" ማለት ነው፡ እርሱም፡ እግዚአብሔር አብን መስሎ፡ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ፡ የእግዚአብሔር አብ፡ የባሕርይ ልጅ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ "ሠራፂ" ማለት ነው። እርሱም፡ እግዚአብሔር አብን መስሎ፡ እግዚአብሔር ወልድን አህሎ፡ ከእግዚአብሔር አብ የሠረፀ (የወጣ)፡ የእውነት መንፈስ ነው።

**ጥያቄ፡-** *እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ በአምላክነቱ፡ አንድ የኾነው እግዚአብሔር፡ በዚህ፡ የአባትነት፡ የልጅነትና የሠራፂነት ሦስትነቱ፡ እንዴት እኩል ሊኾን ይችላል?*

**መልስ፡-** እግዚአብሔር፡ ራሱን፡ "አባት፡ ልጅ፡ ሠራፂ" ብሎ፡ በሦስት ስም መጥራቱ፡ እኛ፡ ፍጡራኑ ሰዎች፡ በለመድነውና በምናውቀው፡ የሥጋዊ ሥነ ፍጥረት አካኼድ፡ የእርሱን፡ የአንዱን አምላክ፡ የእግዚአብሔርን፡ የሦስትነቱን መንፈሳዊ ምሥጢር፡ በቀላሉ ለመገንዘብ እንችል ዘንድ፡ ሊረዳንና ሊያስረዳን፥ ሊያሳምነንም፡ እንጂ፡ በሰዎች ሥርዓት፡ አባት፡ ልጁን፡ ወይም፥ ከእርሱ የሚወጣውን መሰሉን፡ እንደሚበልጠውና እንደሚቀድመው ዓይነት፡ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ፡ መቅደም፡ መቀዳደም፡ መከተል፡ መከታተል፥ መብለጥ፡ መበላለጥ ኖሮ አይደለም። በአንዱ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ እያንዳንዱ ኵነት (ኹኔታ)፡ ማለትም፡ አባትነቱም፥ ልጅነቱም፥ ሠራፂነቱም፡ በአንድነቱ ህልውና ውስጥ፡ በአንድነት ታስቦና ከአንድነቱ ፈልቆ፡ ታውቆና ተፈቅዶ፡ በስምምነት የኾነ ነው።

ይህም፡ እንደሰዎች የተፈጥሮ ሥርዓት ሳይኾን፡ በመለኮታዊው ምሥጢር ብቻ የተከናወነ ስለኾነ፡ በመንፈሳዊው የሃይማኖት አእምሮ ካልኾነ በቀር፡ ሰብአዊው ቀርቶ፡ መልአካዊው አእምሮ እንኳ ሊደርስበት አይቻለውም። ከዚህ የተነሣ፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱ ፍጹምነት፡ "አባት፡ ልጅ፥ ሠራፂ" በሚለው፡ በሦስትነቱ ስም ምክንያት፡ የትርጓሜ ሕፀፅ (ጕድለት) እንኳ እንዳያገኘው በመጠንቀቅ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በሃይማኖት ጸሎታችን ላይ፡ የአንዱን የእግዚአብሔርን፡ የሦስትነት ስም፡ "እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" ብለን በመጥራት፡ የቅድስት ሥላሴን ምሥጢር ጠብቀን ለመኖር በቅተናል።

### የእግዚአብሔር አንድነትና በግብር ሦስትነት።

**ጥያቄ፡-** *የአንዱ እግዚአብሔር፡ በግብር ሦስትነቱ፡ እንደምን ነው?*

**መልስ፡-** የእግዚአብሔር አብ፡ ግብሩ፡ "እግዚአብሔር ወልድን፡ መውለድ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ማሥረፅ" ነው። የእግዚአብሔር ወልድ፡ ግብሩ፡ "ከእግዚአብሔር አብ መወለድ" ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ግብሩ፡ "ከእግዚአብሔር አብ መሥረፅ" ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር: ማነው?

ይህም ማለት: እግዚአብሔር አብ: እግዚአብሔር ወልድን: ቢወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም ቢያሠርፅ እንጂ: እንደእግዚአብሔር ወልድ: አይወለድም፤ እንደእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ: አይሠርፅም:: እግዚአብሔር ወልድም: ከእግዚአብሔር አብ ቢወለድ እንጂ: እንደእግዚአብሔር አብ አይወልድም፥ አያሠርፅም፤ እንደእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አይሠርፅም:: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም: ከእግዚአብሔር አብ ቢሠርፅ እንጂ: እንደእግዚአብሔር አብ አይወልድም፥ አያሠርፅም፤ እንደእግዚአብሔር ወልድም: አይወለድም::

ጥያቄ:- *የእግዚአብሔር አብ: እግዚአብሔር ወልድን: መውለድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም ማሥረፅ፤ የእግዚአብሔር ወልድ: ከእግዚአብሔር አብ መወለድ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም: ከእግዚአብሔር አብ መሥረፅ እንደምን ነው?*

መልስ:- ቀደም ብሎ እንደተገለጸው: እኛ: ፍጡራት ሰዎች: በለመድነውና በምናውቀው: በሥጋዊው ሥነ ፍጥረት አካኼድ: የአንዱን አምላክ: የእግዚአብሔርን: የሦስትነቱን መንፈሳዊ ምሥጢር: በቀላሉ ለመገንዘብ እንችል ዘንድ፥ ሊያስረዳን እንጂ: በሰዎችና በዕፀዋቱ ሥርዓት ሲፈጸም እንደሚታየው: በእግዚአብሔር ዘንድ: መውለድ: መዋለድ፥ መሥረፅ: ማሥረፅ ኖሮ አይደለም:: ይህ መለኮታዊ ምሥጢር: እንዲያው በሃይማኖታዊውና በመንፈሳዊው ኅሊና: "ድንቅ" ብለው: በግሩምነቱ ይዘከሩታል፥ "ዕፁብ"ም ተብሎ በጭንቅ ያስቡታል እንጂ: በሰብአዊው ቀርቶ: በመልአካዊው እንደበት እንኳ ሊነገር፥ በአእምሮም ሊደረስበት አይቻልም::

ጥያቄ:- *እግዚአብሔር አብ: ከወለደ፥ እግዚአብሔር ወልድ: ከተወለደ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ከሠረፀ: አይበላለጡምን?*

መልስ:- አይበላለጡም::

ጥያቄ:- *እንዴት አይበላለጡም? እስቲ: እባክህ: በበለጠ አብራራልን!*

መልስ:- መልሱን: በቀላሉ: ከየራሳችሁ ሰውነትና የተፈጥሮ ግብር ታገኙታላችሁ፤ ይኸውም: ከየልቡናችሁ፥ ከየቃላችሁና ከየእስትንፋሳችሁ ባሕርይና አሠራር ማለት ነው፤ እነዚህ: በአንተና በአንቺ፥ በእኔም: በአንዱ አካላችን ውስጥ ያሉት፥ የሚዳስሱትና ከእኛ ወጥተው የሚደመጡት: ልቡናችን፥ ቃላችንና እስትንፋሳችን: ሦስት ነገሮች ሲኾኑ: እንደማይለያዩና እንደማይበላለጡ ኹሉ: እንደዚሁ: በልቡና የሚመሰለው: እግዚአብሔር አብ፥ በቃል የሚመሰለው: እግዚአብሔር ወልድና በእስትንፋስ የሚመሰለው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም: "ቅድስት ሥላሴ" ተብለው: አንድ አምላክ ሲኾኑ: አይበላለጡም::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥላሴ። ስለቅድስት ሥላሴ።
### የእግዚአብሔር አንድነትና በግብር ሦስትነት።

ሰው የኾነውና በዚህ ሰውነቱ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ የተጠራው፡ እግዚአብሔር ወልድም፡ *"እኔና አብ፡ አንድ ነን! ...አብ፡ በስሜ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ፡ እርሱ፡ ኹሉን ያስተምራችኋል፤"* ብሎ ነግሮናል።

አለመበላለጣቸው ብቻ ሳይኾን፡ አንዱ፡ ሌላውን ሊኾን እንደማይችል፡ የሥነ ፍጥረትን ሥርዓት እንኳ፡ በማስተዋል ተመልከቱት! እኛ፡ የምንናገረው ቃል፡ ከልቡናችን መንጭቶ፡ በእስትንፋሳችን ተሸኝነት፡ ከጆሮአችን ይደርሳል። ቃልና እስትንፋስ፡ ከአንድ ልቡና ስለወጡ፡ ወይም፡ ልቡና ስላስገኛቸውና ስላገናኛቸው፡ ያንኑ የማንነታቸውን አካልና ባሕርይ፡ ስምና ግብር እንደያዙ፡ በዚያው ህልውናቸው ተገልጸው ይሠራሉ እንጂ፡ አይለወጡም፡ አይለዋወጡም። ይህም እንዲህ ነው፦ ቃል፡ "ቃል" ኾኖና ተብሎ፡ ቢነገርና ቢደመጥ እንጂ፡ "ልቡና" ወይም "እስትንፋስ" አይባልም፡ እስትንፋስም፡ "እስትንፋስ" ኾኖና ተብሎ፡ ቢተነፈስና ቢሸተት እንጂ፡ "ልቡና" ወይም "ቃል" አይባልም፡ ልቡናም፡ "ልቡና" ኾኖና ተብሎ፡ ቢታሰብበትና ቢታወቅ እንጂ፡ "ቃል" ወይም "እስትንፋስ" አይባልም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ ልቡናነት ወጥተው ስለተገኙ፡ ወይም፡ የእግዚአብሔር አብ፡ ልቡናነት ስላገናኛቸው፡ ያንኑ የማንነታቸውን አካልና ባሕርይ፡ ስምና ግብር እንደያዙ ይኖራሉ እንጂ፡ አይለወጡም፡ አይለውጡም፡ አይለዋወጡም። እንዲህም ማለት፡ እግዚአብሔር አብ፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፥ እግዚአብሔር ወልድ፡ በእግዚአብሔር ወልድነቱ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነቱ ባሕርይ፥ ስምና ግብር፡ ጸንተው፡ በአንድነትና በሦስትነት እንደኖሩ፡ ለዘለዓለምም ይኖራሉ። ማለት ነው።

### የእግዚአብሔር አንድነትና በአካል ሦስትነት።

**ጥያቄ:-** *የአንድ እግዚአብሔር፡ የአካል ሦስትነት፡ እንደምን ነው?*

**መልስ:-** ለእግዚአብሔር አብ፡ ፍጹም አካል፥ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም ገጽ አለው፡ ለእግዚአብሔር ወልድም፡ ፍጹም አካል፡ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም ገጽ አለው፡ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ ፍጹም አካል፥ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም ገጽ አለው።

**ጥያቄ:-** የአካል፥ የመልክና የገጽ ልዩነት ምንድር ነው?

**መልስ:-** ከራስ ፀጉር ጀምሮ፡ እስከእግር ጥፍር ድረስ ያለው ቅርጽና ገዘፍ፡ "አካል" ይባላል፤ የአካሉ ሙሉነት፥ ቀለሙና ዓይነቱ፡ "መልክ" ይባላል። የዚያ አካል ፊት፡ "ገጽ" ይባላል። ከአካሉ፡ አንድ አባል፡ ወይም ብልት፡ ወይም ሕዋስ ቢጐድል፡ ያ አካል፡ "ጎደሎ" ይባላል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር ማነው?

የቅድስት ሥላሴ አካል፡ መልክና ገጽ፡ እንደሰው አካል፥ መልክና ገጽ ነው። ይህም፡ *"እግዚአብሔርም አለ፡ "ሰውን፡ በመልካችን፡ እንደምሳሌአችን፡ እንፍጠር!"* በሚለው አምላካዊ ቃል፡ ተረጋግጦ ይታወቃል። ዳዊትም፡ በመዝሙራቱ፡ *"እግዚአብሔር፡ ዙፋኑ፡ በሰማይ ነው፡ ዓይኖቹ፡ ወደ ደሀ ይመለከታሉ፡ ቅንድቦቹም፡ የሰው ልጆችን ይመረምራሉ። ...የእግዚአብሔር ዓይኖች፡ እውነተኞችን ይመለከታሉ፡ ጆሮቹም፡ ልመናቸውን ይሰማሉ። መታሰቢያቸውን፡ ከምድር ያጠፋ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር ፊት፡ ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነው። ...የእግዚአብሔር ፊቱ፡ ክፉ ወደሚያደርጉ ነው። ...እጅህ ሥራችን፡ አበጃጀችኝም። ... ከንድህን፡ ከአርያም ላክ!"* ብሏል። ራሱ እግዚአብሔርም፡ በነቢያት አንደበት፡ *"ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፡ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት!"* ሲል ተናግሯል።

ነገር ግን፡ የሰው አካሉ፡ በሥጋው ምክንያት፡ ግዙፍ፡ ውሱን፡ ጠባብ፡ ፈራሽና በስባሽ ሲኾን፡ የሥላሴ አካል ግን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሰውነት ከተገለጸበት ጊዜ በቀር፡ ይህ ኹሉ የሌለበት፡ በሰማይና በምድር፡ በአየርና በጥልቁ የመላ፡ ስፉሕ፡ ረቂቅና ሕያወ ባሕርይ ነው።

### የእግዚአብሔር አንድነት፡ በሦስትነት፥ ሦስትነት በአንድነት ምሥጢር።

*ጥያቄ:- እስኪ፡ የእግዚአብሔርን አንድነት፡ በሦስትነቱ ምሥጢር፡ ሦስትነቱንም፡ በአንድነቱ ምሥጢር አስፋፍተህ አብራራልን?*

**መልስ:- ይህ፡ የሃይማኖታዊው ትምህርትና የመንፈሳዊው እውቀት አሰጣጥና አቀባበል የሚካኼደው፡ በሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ልቦናና አእምሮ አማካይነት ነው፤ ይኹን እንጂ፡ የእግዚአብሔርን፡ የማይነጣጠል አንድነትና ሦስትነት፡ በቀላሉ ለማስረዳት የምንጠቀምባቸው ምሳሌዎች፡ ምድራውያን፡ ሥጋውያን የኾኑትን፡ የእግዚአብሔርን ግዙፋን ፍጥረቶች መኾኑን፡ አስቀድሜ ላሳውቃችሁ እፈልጋለሁ።**

**ሦስትነቱ፡ በአንድነቱ ውስጥ እንዴት ህልዋን ኾነው፥ አንድነቱም፡ በሦስትነቱ፡ እንዴት ህልው ኾኖ እንደሚኖር፡ ማለትም፡ ይህን፡ የሥላሴን የአኗኗር ምሥጢራዊ ነገር፡ በበለጠ ለማብራራት፡ በመጀመሪያ፡ ቀደም ብለን ያወሳናቸውን፡ እነዚሁኑ፡ "ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ" የተባሉትን የሕያዋን ፍጡራን የህልውና መሣሪያዎች፡ እንደሚከተለው፡ በምሳሌነት እንጠቀምባቸዋለን።**

**"ህልው፥ ህልዋን" የሚለው የግእዝ ቃል፡ "ህለወ"፡ "ኖረ" ከሚለው ግሥ የተገኘ መኾኑን ልታስተውሉት ያስፈልጋል።**

## ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

### ምሥጢረ ሥላሴ፡ የእግዚአብሔር አንድነትና በአካል ሦስትነት::
### የእግዚአብሔር አንድነት፡ በሦስትነት፡ ሦስትነት በአንድነት ምሥጢር::

---

እግዚአብሔር አብ፡ እርሱ ራሱ፡ የአንድነቱ ልብ ሲኾን፡ ከእርሱ ጋር፡ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ አብረው፡ ህልዋን ኾነው፡ በእርሱ ልቡናነት ያስቡበታል:: እግዚአብሔር ወልድ፡ እርሱ ራሱ፡ የአንድነቱ ቃል ሲኾን፡ ከእርሱ ጋር፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ አብረው፡ ህልዋን ኾነው፡ በእርሱ ቃልነት ይናገሩበታል:: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እርሱ ራሱ፡ የአንድነቱ እስትንፋስ ሲኾን፡ ከእርሱ ጋር፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ፡ አብረው፡ ህልዋን ኾነው፡ በእርሱ እስትንፋስነት ይተነፍሱበታል::

ይህ፡ እውነታ፡ በእኛም፡ በሰዎች ዘንድ፡ ህልውናችንና ሕይወታችን ኾኖ፡ አብሮን የሚገኝ፡ ከየራሳችንም ላይ፡ ለቅጽበት እንኳ ሳይቋረጥ እየተከኼደ ያለ ስለኾነ፡ በቀላሉ ልንረዳው ይቻለናል:: ለዚህም:-

በመጀመሪያ፡ በምሳሌነት የምጠቅስላችሁ፡ ከመለኮት ባሕርይ የተገኘችውንና መንፈሳዊት የኾነችውን፡ የእያንዳንዳችንን ነፍስ ነው፡ ለዚች ነፍሳችን፡ ሦስት ባሕርያት እንዳሏት አውቃችኋል፡ እነዚህም፡ "ለባዊነት"፡ "ማለትም"፡ ክፉና ደጉን ለይቶ የማወቁ ሥልጣን፡ "ነባቢነት"፡ ማለትም፡ ስሜትን፡ በንግግርና በተለያየ ድርጊት የመግለጽ ችሎታ እና "ሕያውነት"፡ "ማለትም"፡ ሳትሞት፡ ለዘለዓለም የመኖሩ ብቅዓት ናቸው:: በነፍስ ለባዊነት፡ እግዚአብሔር አብ ይመሰላል፤ በነባቢነቷ፡ እግዚአብሔር ወልድ ይመሰላል፤ በሕያውነቷ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ይህች ነፍስ፡ በሦስቱ ባሕርያቷ እየተከሠተች ብትሠራም፡ "አንዲት ነፍስ" ብትባል እንጂ፡ "ሦስት ነፍሳት" እንደማትባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፤" ብለን አናምንም::

ኹለተኛ የምጠቅሰው፡ እያንዳንዳችን፡ በነፍሳዊ ተፈጥሮአችንና ሥጋዊ በኾነው ደመ ነፍሳችን የተቀዳጀናቸውን፡ "ልብ፥ ቃልና እስትንፋስ" የተባሉትን ረቂቃን መሣሪያዎች ነው:: በልቡናችን፡ እግዚአብሔር አብ፥ በቃላችን፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ በእስትንፋሳችን፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ:: እኛ፡ በአንድ ልቡናችን እንደምናስብ፡ እነርሱም፡ በእግዚአብሔር አብ ልቡናነት፡ በአንድነት ያስባሉ:: እኛ፡ በአንድ ቃላችን እንደምንነጋገር፡ እነርሱም፡ በእግዚአብሔር ወልድ ቃልነት፡ በአንድነት ይናገራሉ:: እኛ፡ በአንድ እስትንፋሳችን እንደምንተነፍስ፡ እነርሱም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ:: በእነዚህ፡ የህልውናችን መገለጫዎች በኾኑት፡ በሦስቱ የሕይወት መሣሪያዎች ምክንያት፡ እነዚህኑ የያዘው ሰውነታችን፡ ማለትም፡ የእያንዳንዳችን እኔነት፡ "አንድ" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት" እንደማይባል፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔርም፡ ምንም፡ ለፍጥረቱ መልካም ሕይወትና የዘለዓለም ደኅንነት ሲል፡ የቸርነቱን ሥራ ሲሠራ፡ በሦስት ስም ቢጠራ፥ በሦስት አካል ቢገለጥና በሦስት ግብር ቢሠራ፡ አንድ አምላክ እንጂ፡ ሦስት አማልክት ስላልኾነ፡ እርሱን፡ "አንድ አምላክ ነው" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ያሉበት አምላክ ነው፤" ብለን አናምንም::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ሦስተኛ፡ ለቅጽበት የማይለየንንና ሕይወታችን የኾነውን አየርን፡ እስኪ፡ ለአንዲት አፍታ እናስተውለው! ለአየር፡ ሦስት ነገሮች አሉት፥ እነርሱም፡ "አካሉ፥ ርቅቀቱና ኃይሉ" ናቸው:: በአካሉ፡ እግዚአብሔር አብ፥ በርቅቀቱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በኃይሉ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ይህም፡ "አንድ አየር" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት አየሮች" እንደማይባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፡" ብለን አናምንም::

አራተኛ፡ ስለምንጭ ውኃ ደግሞ፡ እናስብ! ምንጭ፡ ሦስት ነገሮች አሉት፥ እነርሱም፡ "ነቅዑ (መፍለቂያው)፥ ኾረቱና ማርካቱ" ናቸው:: በነቅዑ፡ እግዚአብሔር አብ፡ በኾረቱ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በማርካቱ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ያ የምንጭ ውኃ፡ እንዲህ በመኾኑ፡ "አንድ ውኃ" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት ውኆች" እንደማይባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፡" ብለን አናምንም::

አምስተኛ፡ ፀሓይን፡ በምሳሌነት ተመልከቷት! ለፀሓይ፡ ሦስት ነገሮች አሏት፥ እነርሱም፡ "ክበቧ፥ ብርሃኗና ሙቀቷ" ናቸው:: በክበቧ፡ እግዚአብሔር አብ፡ በብርሃኗ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በሙቀቷ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ፀሓይ፡ እንዲህ በመኾኗ፡ "አንዲት ፀሓይ" ብትባል እንጂ፡ "ሦስት ፀሓዮች" እንደማትባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፤" ብለን አናምንም::

ስድስተኛ፡ ከፍሬ ዛፎች መካከል ደግሞ፡ የወይን ተክልን፡ ምሳሌ እናድርግ! ለወይን፡ ሦስት ነገሮች አሉት፤ እነርሱም፡ "ግንዱ፥ ፍሬውና ልምላሜው" ናቸው:: በግንዱ፡ እግዚአብሔር አብ፥ በፍሬው፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ በልምላሜው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ይህም፡ "አንድ ወይን" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት ወይኖች" እንደማይባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፤" ብለን አናምንም::

ሰባተኛ፡ በቅርብ ያለውን፡ ሰው የሚያነደውን እሳት እዩት! ለእሳት፡ ሦስት ነገሮች አሉት፤ እነርሱም፡ "ፍሕሙ፥ ነበልባሉ (የሚያበራው ላንቃው) እና ዋዕዩ (ማቃጠሉ)" ናቸው:: በፍሕሙ፡ እግዚአብሔር አብ፥ በነበልባሉ፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ በዋዕዩ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ይህም፡ "አንድ እሳት" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት እሳቶች" እንደማይባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፤" ብለን አናምንም::

የምንኖርበትን ቤት፡ በምሳሌነቱ፡ እስኪ እንጠቀምበት! ቤትን፡ ቤት የሚያሰኙ፡ ሦስት ነገሮች አሉ፤ እነርሱም፡ በግድ አንድ ኾነው መገኘት የሚኖርባቸው፡ "መሠረቱ፥ ግድግዳውና ጣሪያው" ናቸው:: በመሠረቱ፡ እግዚአብሔር አብ፥ በግድግዳው፡ እግዚአብሔር ወልድ፥ በጣሪያው፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ይህም፡ "አንድ ቤት" ቢባል እንጂ፡ "ሦስት ቤቶች" እንደማይባል፡ እግዚአብሔርንም፡ "አንድ አምላክ ነው፤" ብለን እናምናለን እንጂ፡ "ሦስት አማልክት ነው፤" ብለን አናምንም::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥላሴ፤ የእግዚአብሔር አንድነትና በአካል ሦስትነት።
## የእግዚአብሔር አንድነት፡ በሦስትነት፥ ሦስትነት በአንድነት ምሥጢር።

---

እንግዴህ፡ "እግዚአብሔር፡ እንዲህ አንድ ሲኾን፡ 'እግዚአብሔር አብ'፥ 'እግዚአብሔር ወልድ'፥ 'እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ' ተብሎ፡ በሦስትነት ስም ሊጠራ፥ በሦስትነት አካል ሊገለጥና በሦስትነት ግብር ሊሠራ፡ ስለምን ፈለገ?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ግልጽና ቊርጥ፥ አጭር፡ም ነው። ያም፡ "ለፍጥረቱ፥ በተለይም፡ በመልኩ ለፈጠረው ሰው ሲል ነው፡- ማለትም፡ ለዚህ ፍጡሩ ካለው፡ ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ ነው!" በሚለው፡ የሃይማኖት እውነታ ላይ በተመሠረተው ቃል ይጠቃለላል፤ ይህንም ታላቅ ቊም ነገር፡ እስከሁን ከተረዳችሁት በላይ፡ ወደፊት ተከታትለው በሚቀርቡት ምሥጢራት፡ በበለጠ ተብራርቶ ታገኙታላችሁ።

### ስለምሥጢረ ሥላሴ ማጠቃለያ።

ጥያቄ፡- *ወደሚቀጥሉት ምሥጢራት ከመኼድህ በፊት፡ የዚህን ዋና ምሥጢር፡ ፍሬ ነገሮች፡ በየአእምሮአችን ቀርጸን ልናስተውላቸው ይቻለን ዘንድ፡ በተጠቃለለ መልክ ብትነግረን!*

መልስ፡- የምሥጢረ ሥላሴን ነገር፡ እኔ፡ ትሑቱ አገልጋይ፡ በውሱኑ የመግለጥ ዓቅሜ፡ ለእናንተ ለእውቀት ወጣኒዎቼ፡ የምሥጢሩን ፍንጭ አስጨብጣችሁ ዘንድ፡ እንዲህ በሚል ቃል፡ ላጠቃልለው እሞክራለሁ፡-

ያው፡ አንዱ እግዚአብሔር፡ "እግዚአብሔር አብ" በሚል ስም፡ ማለትም፡ "አባት የኾነው እግዚአብሔር"፡ እንደሰብአዊት ነፍስ ለባዊነት፥ እንደሰው ልብ፥ እንደአየሩ አካል፥ እንደውኃ ምንጭ፥ እንደፀሓይ ክበብ፥ እንደእሳት ፍሕም፥ እንደተክል ግንድ እና/ወይም በተጨማሪ፡ እንደቤት መሠረት፡ ለኹሉ፡ አንድ መነሻ ነው።

ያው፡ አንዱ እግዚአብሔር፡ "እግዚአብሔር ወልድ" በሚል ስም፡ ማለትም፡ "የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ የኾነው እግዚአብሔር"፡ ከሰብአዊዋ ነፍስ "ለባዊነት" ወጥቶ እንደሚገዝፈው ነባቢነት፥ ከ"ፍጡር ልቡና" መንጭቶ እንደሚሰማ ቃል፥ ከ"አየር አካል" ተገኝቶ እንደሚዳሰሰው ርቅቀት፥ ከ"ምንጭ" ፈልቆ እንደሚፈስስ የውኃ ጅረት፥ ከ"ፀሓይ ክበብ" ተፈንጥቆ፡ እንደሚያበራ ብርሃን፥ ከ"ፍሕም" ተነሥቶ እንደሚታይ የእሳት ነበልባል እና ከ"ግንድ" ላይ በቅሎ፡ የተክሉን ምንነት እንደሚያስታውቀው ፍሬ፥ እንዲሁም፡ ከ"ቤት መሠረት" ላይ ታንጾ እንደሚቆም ግድግዳ፡ ጥንት፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ ያለሰብአዊት እናት ተወልዶና "የእግዚአብሔር ልጅ" ተብሎ፡ የፈጣሪነት ሥራውን ሲያካኺድ ኖረ፤ በመጨረሻውም ዘመን፡ "የሰው ልጅ" ተብሎ፡ ከድንግል ማርያም፡ ያለሰብአዊ አባት ተወለደ። እንዲህ፡ በሰውነት ተገልጦ፡ የእግዚአብሔርን ማንነት ያስታወቀውና የቤዛነት ጸጋውን፡ ለፍጥረቱ ኹሉ ያስገኘው፡ እርሱ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተባለ።

ያው፡ አንዱ እግዚአብሔር፡ "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" በሚል ስም፡ ማለትም፡ "ቅዱሱ የእውነት መንፈስ የኾነው እግዚአብሔር"፡ ከሰብአዊዋ ነፍስ "ለባዊነት" ወጥቶ እንደሚያስገኘው ሕያውነት፡ ከ"ፍጡር ልቡና" የመነጨውን ቃል ተሸክሞ እንደሚያስተላልፈው እስትንፋስ፡ ከ"አየር አካል" ተገኝቶ፡ የጸጋ ተልእኮውን በርቅቀት እንደሚፈጽመው ኃይል፡ ከ"ምንጭ" ፈልቆና ፈስሶ እንደሚሰጠው የውኃ እርካታ፡ ከ"ፀሓይ ክበብ" ተፈንጥቆ፡ የሚያበራው ብርሃን እንደሚሰጠው ሙቀት፡ ከ"ፍሕም" እንደሚወጣው ግለት እና ከ"ግንድ" ላይ በቅሎ፡ የተክሉን ኹለንተና እንዳላበሰውና መልካም መዓዛን እንደሚሰጠው ልምላሜ፡ እንዲሁም፡ ከ"ቤት መሠረት" ላይ ታንጾ በቆመው ግድግዳ ላይ እንዳረፈው ጣሪያ፡ ጥንት፡ ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእግዚአብሔር አብ ሠርፆ፡ በሕይወት የማኖር ሥራውን ያካኺድ ነበር፡፡ በመጨረሻው ዘመን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ የሰው ዘር ጠላቶች የኾኑትን፡ ዲያብሎስን፡ ኃጢአትንና ሞትን ድል አድርጎ፡ ወደሰማይ ካረገና በዘለዓለማዊው ዙፋኑ ከተቀመጠ በኋላ፡ እርሱ፡ በቤዛነቱ፡ በከፈተው ጎዳናና ባስገኘው ጸጋ፡ ይህን ዓለም፡ በምልዓትና በስፋት ያጥለቀልቀው ዘንድ፡ የማይታይ ረቂቅ መንፈስ ኾኖ፡ ወደሰውና ወደቀረው ፍጥረቱ፡ እንደገና መጣ፤ በእውነት በሚፈልገው ሰብአዊ ፍጡሩም ላይ ኹሉ፡ በጸጋነት የሚያድር ኾነ!

ይህን ሃይማኖታዊ ትምህርት መሠረት በማድረግ፡ ቀደም ብለው በምሳሌነት ከቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፡ ለዓይነት ያህል፡ "ፀሓይ"ን ብንወስድ፡ በክበቧ፥ በብርሃኗና በሙቀቷ ሦስትነት ያላት፡ ይህችው፡ አንዲቷ ፀሓይ፡ እነዚሁ፡ የአካል፥ የመልክና የጠባይ ኹነታዎቿ፡ ከራሷ፡ ከምንጯቸው፡ ከፀሓይ ጀምረው፡ በባሕርይ ሳይለያዩ፡ በአንድነት እንደሚሠሩ፥ ከተለያዩ ግን፡ ህልውና ሊኖራቸውና ሊገለጡ፥ ሊሠሩም እንደማይችሉ ለማስረዳትና ለመረዳት፡ ግልጽና ቀላል ይኾናል፡፡ ደግሞ፡ 'የፀሓይ ክበብ'፥ 'የፀሓይ ብርሃን' እና 'የፀሓይ ሙቀት' ተብለው፡ እንዲህ፡ በሦስት ስም በመጠራታቸው፥ ወይም 'በክበብነት'፥ 'በብርሃንነት' እና 'በሙቀትነት'፡ በእነዚህ፡ ሦስት አካላት በመገለጣቸው፥ ወይም፡ 'ፀሓይ ወጣች!'፥ 'ውጭው፡ ፀሓይ ነው፤' 'ፀሓዩ ያቃጥላል፤' በሚል፡ በሦስት ዓይነት ግብር ሲሠሩ በመገኘታቸው፡ ያው፡ አንዲት ፀሓይ እንጂ፡ ሦስት ፀሓዮች እንደማይባሉ የታወቀ ነው፡፡

እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ አንድ አምላክ ስለኾነ፡ የአንድነቱ ማረጋገጫ በኾነው ስሙ፡ "እግዚአብሔር" ይባላል፡፡ ይኸው እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ በአንድ የእግዚአብሔርነት ባሕርይና ህልውና፡ ሳይለያይ፡ አንድ አምላክ ኾኖ ሣለ፡ በሦስት ስሞች ይጠራል፤ በሦስት አካላት ተገልጦ፡ ሦስት ግብራትን ይፈጽማል እንጂ፡ ሦስት እግዚአብሔር፥ ወይም፡ ሦስት አማልክት፥ ወይም፡ ሦስት መለኮት አይባልም፡፡

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡
### ስለምሥጢረ ሥላሴ ማጠቃለያ፡፡

---

በሦስት ስም መጠራት ማለትም: 'እግዚአብሔር አብ÷ እግዚአብሔር ወልድ÷ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ' መባል ነው፤ በሦስት አካላት መገለጥ ማለትም: 'በእግዚአብሔር አባትነት÷ በእግዚአብሔር ልጅነት÷ በእግዚአብሔር ጸጋነት' መታወቅ ነው፤ ሦስት ግብራትን መፈጸም ማለትም: 'አብ: ልጁን ወልዶ÷ መንፈሱንም አሥርፆ መላክ÷ ወልድም: ከአብ: ያለእናት ተወልዶ: ሰው ከመኾኑ በፊትና ከድንግል ማርያም: ያለአባት ተወልዶ: ሰው ከኾነ በኋላ: በልጅነቱ: የእግዚአብሔርነቱን ፈቃድ መፈጸም÷ መንፈስ ቅዱስም: ከአብ ሠርፆ -ወጥቶ- የእግዚአብሔር የኾነውን ተግባር: በርቅቀትና በምልዓት ማካኼድ ነው፡፡

እስካሁን: በምሳሌነት የቀረቡት: የአንድ ሰው: ነፍሳዊውና ሥጋዊው ተፈጥሮ: የአየሩ አካል÷ የእሳቱ ነድ: የውኃው ምንጭ: የወይኑ ተክልና የቤቱ ሕንፃ: በየፊናቸው የአላቸው: የአንድነት ህላዌና የሦስትነት ባሕርይ: ልክ እንደዚሁ: እንደፀሓይዋ ነው፡፡ ከእነዚህ ምሳሌዎች መካከል: ኹለቱን ያህል በድጋሚ ማስረጃነት ወስደን: የአንድነትና የሦስትነት ህልውናቸውንና ባሕርያቸውን ምሥጢር: እንደገና አካትተን ብንመለከተው: ለጥያቄያችሁ: እስካኹን ካገኛችሁት መልስ በላይ: በበለጠ የምትረኩበትን ግንዛቤ ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ይኸውም: ቀደም ብዬ እንዳተትሁላችሁ: ሰው: በአንድ አካል ገዘፎ የሚታይ ሲኾን: የተለያየ ስያሜ: ኹነትና አገልግሎት ባላቸው: 'በልቡ÷ በቃሉና በትንፋሹ ሦስትነት' ምክንያት: 'ሦስት ነው!" የማይባል መኾኑ ነው፡፡

ከዚህ ያተነሣ: በአንድ ግለሰብ ሰውነት ውስጥ: በተፈጥሮ የሚገኙና ለየራሳቸው: የተለያየ 'ሦስት ስም': 'ሦስት አካል' እና 'ሦስት ግብር' የአላቸው: እነዚህ ግዙፉን መግለያዎች: ፩ኛ: 'ልብ'÷ 'ቃል'÷ 'ትንፋሽ' ተብለው: በየራሳቸው ስም የሚጠሩ በመኾናቸው: ፪ኛ: ለየራሳቸው: የህልውና ገጽታ የአላቸው በመኾናቸው: ፫ኛ: 'ልብ': አሳብን በማመንጨት÷ 'ቃል': ያን አሳብ: በቃላት ወይም በንግግር: አከናውኖና በድምፅ አጉልቶ በማሰማት÷ 'ትንፋሽ' ደግሞ: በቃል ንግግር ወይም ድምፅ: የኅላውን: ያን: ከልብ የመነጨውን አሳብ: ወደሌላ ሰሚ ጆሮ: በምሕዋርነት በማስተላለፍ: ሦስቱም: የየራሳቸውን የተለያየ አገልግሎት: የሚሰጡ በመኾናቸው: 'ሦስት' ሲኾኑ: ሰውዬው ግን: ያው: 'አንድ' ሰው እንጂ: 'ሦስት' ሰዎች አይባልም፡፡ "እከሌ: በልቡ: አንድ አሳብ ነበረው: ያንንም: እንዲህ ብሎ: በቃሉ አስረዳ: ያም: በየቦታው ተናኝቶ: ተሰማ!" ሲባል: በ'ሦስት' መልክ የተገለጸው: የሰውዬው ተግባር: ሰውዬውን: ያው: 'አንድ' ሰው እንጂ: 'ሦስት' ሰዎች አያደርገውም፡፡

እንዲህ: "'በሦስትነት' የሚጠራ÷ የሚታይና የሚሠራ 'አንድነት'" ያላቸው: እኒህ: 'ልብ'÷ 'ቃል'÷ 'ትንፋሽ' የተባሉት ባሕርያት: 'ሦስት' ሲኾኑ: 'አንድ' መኾናቸው ተረጋግጦ የሚታወቅበት ልዩ እውነታ አላቸው፤ ይህም: ከሦስቱ: አንደኛቸው: ከመካከላቸው ከተለየ: ወይም ከሌለ: ኹሉም: ወይም አንዳቸው: ለየብቻቸው: ወይም ተነጣጥለው ሊኖሩ አለመቻላቸው ነው፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህን እውነታ፡ እስኪ፡ በበለጠ ግልጽ ላድርግላችሁ! ሰውዬውን፡ ፍጹም ሰው ለማሰኘት፡ 'ልብ'፥ 'ቃል'፥ 'ትንፋሽ' የተባሉት፡ የሰውነቱ የህልውና ክፍሎች፡ 'ሦስቱም'፡ 'በአንድነት' መኖር አለባቸው፤ ይኸውም፡ 'ቃል' እና 'ትንፋሽ'፡ ያለ'ልብ' ሊገኙ፡ ወይም ሊኖሩ አይችሉም፡ ኹለቱም፡ ከ'ልብ' ይመነጫሉ፡ 'ልብ'ም፡ 'ቃል'ን እና 'ትንፋሽ'ን የሚያስገኝ ካልኾነ፡ የዚያ ግለሰብ ፍጹም ሰውነት "አለ!" ሊባል አይቻልም። 'ትንፋሽ'፡ 'ቃል'ን ለማስተላለፍ፡ መኖር አለበት፥ 'ቃል'ም፡ ያለ'ልብ' እና ያለ'ትንፋሽ' ህልውና የለውም። "በዚያ ሰው 'ልብ'፡ 'እግዚአብሔር አብ'፥ በዚያ ሰው 'ቃል'፡ 'እግዚአብሔር ወልድ'፥ በዚያ ሰው 'ትንፋሽ'፡ 'እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ' ይመሰላል፡" የተባለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ ምሥጢሩን፡ በትክክል በመረዳት፡ እውነቱን፡ አረጋግጦ መገንዘብ ይቻላል።

ምሥጢረ ሥላሴ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የቱን ያህል በሰውነታቸው ሠርፆና ጠልቆ፡ ሥር ሰድዶና ተወድዶ፡ በሕያውነት ህልውና ተዋሕዷቸው የሚኖር መኾኑን፡ በዓለ ቅድስት ሥላሴን፡ በየወሩ በ፯ኛው ቀን፡ በተለይም፡ በየዓመቱ፡ በጥር ፯ እና በሐምሌ ፯ ቀን፡ በታላቅ የደስታ ስሜትና ድምቀት ማክበራቸው፡ በሚበቃ ያስረዳል።

"ምሥጢረ ሥላሴ" የሚባለው፡ የእግዚአብሔር፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ነገር፡ እንግዲህ፡ ይህ፡ ከዚህ በላይ በዝርዝር የተብራራላችሁ ነው።

ከዚህ የሚቀጥሉት አራቱ ምሥጢራት፡ በዚሁ፡ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ውስጥ በተከሠቱት መሠረታውያን የሃይማኖት እውነቶች ላይ ታንፀው የቆሙ፡ ከእነርሱም የሚመነጩ በመኾናቸው፡ በዚህ ምሥጢር ላይ፡ ይህን የመሰለውን ዝርዝር ሓተታ ማግኘታችሁ፡ ስለቀሩት፡ አራት ምሥጢራት፡ ለማወቅና ለመረዳት፥ ጥያቄዎችም ቢኖሩ፡ ለእነዚያ፡ ተገቢውን መልስ ለመስጠት፡ የቱን ያህል ቀና ሊኾንላችሁ እንደቻለ፡ በቀላሉ ትረዱታላችሁ።

## ምሥጢረ ሥጋዌ።

*ጥያቄ፦ ቀደም ብለህ በሰጠኸን ዝርዝር መሠረት፡ ቀጥለህ የምታብራራልን፡ ኹለተኛው ምሥጢር፡ ምሥጢረ ሥጋዌ መኾኑ አይደለምን?*

መልስ፦ አዎን! እግዚአብሔር፡ ሰው ኾኖ፡ ዓለሙን የማዳኑን ሥራ የሚያስረዳው፡ ይህ፡ ኹለተኛው ትምህርት፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ይባላል። አምላክ፡ ሰው የመኾኑ ምሥጢር የተገለጸበት፡ ይኸውም፡ መለኮትና ትስብእት ማለትም፡ አምላክነትና ሰውነት፡ በተዋሕዶ አንድ የኾኑበት ነገረ ሃይማኖት የሚነገርበት ትምህርት ስለኾነ፡ "ምሥጢር" ተብሏል።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥጋዌ።

---

### እግዚአብሔር፡ ለምን ሰው መኾን ፈለገ?

*ጥያቄ፦ በመሠረቱ፡ በዚህ አካሉና ባሕርዩ፡ ይኖርና ይሠራ የነበረው እግዚአብሔር፡ ለምን ሰው መኾን እንዳስፈለገው፡ ምክንያቱን ብትገልጽልን?*

መልስ፦ እስካኹን በየቦታው እንደተገለጸው፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በምሥጢረ ሥላሴ ያወቅነው፡ አንድ ባሕርይ የኾነው ፈጣሪያችንና አምላካችን እግዚአብሔር፡ ከሦስቱ አካላቱ፡ "ወልድ" በተባለው፡ የተለየ አካሉ፡ ሰው እንዲኾን ያስፈለገው፡ ፍጥረቱን፡ በተለይም፡ ሰብአዊ ፍጡሩን ለማዳን መኾኑ፡ ይህን እውቀት፡ በበለጠ አጉልቶ የሚያብራራልንም ትምህርት፡ *ምሥጢረ ሥጋዌ* የሚባለው መኾኑ ተነግሯዋል። እግዚአብሔር ወልድ፡ በመለኮታዊ ፍቅሩና ቸርነቱ፡ ሰው የኾነበት ምክንያት፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪው የተሰጠውን የሕይወት መመሪያ፡ በራሱ ምርጫ አፍርሶ፡ በራሱ ላይ ታላቅ ጉዳትን ያስከተለበትን የዲያብሎስን አገዛዝ፡ በገዛ ፈቃዱ በመቀበሉ፡ ከሚማቅቅበት፡ ከክፋው የባርነት ኑሮው ነጻ ሊያወጣው፡ ከዚህ የተነሣም፡ እየተጫነው የኼደውን የኃጢአት ቀንበር ሊሠብርለትና በዚህ ምክንያት ከተፈረደበት የሞት ፍዳ ሊያተርፈው መኾኑን፡ ይህ ምሥጢር ያብራራልናል።

በመሠረቱ፡ ሰው፡ የእግዚአብሔርን መልክ ተቀዳጅቶ፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ፡ በሥጋ የተፈጠረው፡ የፈጣሪውን ስም፡ በምስጋና እየቀደሰ፡ የክብሩ ወራሽ ኾኖ፡ በፍጹም ተድላ ደስታ፡ ለዘለዓለም፡ በሕይወት ለመኖር መኾኑ፡ ቀደም ብሎ፡ በየቦታው የተነገረውን ሰምታችሁታል። እግዚአብሔር፡ እንዲህ አድርጎ፡ ለዚህ ዓላማ፡ ሰውን ሲፈጥረው፡ ይኸው፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ለዚህ መለኮታዊ መልካም ዓላማ፡ ብቁ መኾኑ ቀርቶ፡ ተቃራኒና አፍራሽ እንደሚኾን፡ እርሱ፡ ፈጣሪው አስቀድሞ አያውቅም ማለት አይደለም። በእርግጥ ያውቅ ነበር። ይህንም እውነታ፡ *"እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ 'የምንፈጥረው ሰው፡ በተፈጥሮው፡ በተለይም፡ በሚለብሰው ሥጋ ምክንያት፡ ስሑት፡* (ማለትም፡ ስሕተተኛ) *መኾኑ አይቀርምና፡ አንፍጠረው!' ቢሉ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ 'እኔ ዋስ እኾነዋለሁና፡ ግድ የለም! ይፈጠር!' ስላለ፡ ተፈጠረ፡"* የሚለው፡ የሃይማኖታችን ምሁራን፡ ስለዚህ ምሥጢር፡ የሚሰጡት የትርጓሜ ሐተታ ያመለክታል።

**በዚህ መሠረት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ የፈጠረው ሰው፡ ወደፊት ከተዘጋጀለት መልካም ሕይወት ውጪ ኾኖ፡ የሚጠፋበትን ክፉ ሥራ እንደሚያደርግ፥ ነገር ግን፡ የኋላ ኋላ፡ የኃጢአቱ ጽዋ ሲሞላ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ደርሶ፡ ከጥፋት ስለምታተርፈው፡ ይህ የክፋት ሥራው፡ በመጨረሻ፡ ለዘሩ ሳይቀር እንደሚበጀው፥ ራሱም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በመለኮታዊ ፈቃዱ፡ ይህንኑ፡ ሰብአዊ ፍጡሩን፡ ገና ሲፈጥረው፡ የሰጠውን ዋስትና አስቦ፡ የመቤዠት (ቤዛ ኾኖ የማዳን) ግዴታውን ለመፈጸም፡ ሰው መኾኑና መሞቱ እንደማይቀርለት፡ ፈጣሪ፡ አስቀድሞ እንደሚያውቅ፡ በግልጽ ይታመናል።**

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እግዚአብሔር ወልድ፡ በዚህ መልክ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያት፡ በበርካታ ቁም ነገሮች ሊጠቃለል ይቻላል፤ ከእነዚህ መካከል፡ የሚከተሉትን ልጥቀስላችሁ:-

፩ኛ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ በብሉዩ ዘመን ኪዳናት አጽንቶ ያቆያትን፡ በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተችውን መንግሥቱን፡ በአዲሱ ኪዳን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ አድሶ፡ ለዘለዓለማዊነት ህልውና ሊያበቃት ነው፤

፪ኛ፡ የመልካሙ ነገር ተቃዋሚና የሰው ጠላት የኾነውን፡ የዲያብሎስን ኃይል፡ ከኃጢአትና ከሞት ጠንቆቹ ጋር፡ ፈጽሞ አስወግዶ፡ ፍጡሩ ሰው፡ በዚች መለኮታዊት መንግሥቱ ውስጥ፡ ዛሬ፡ በመንፈስ ቅዱስ በታደሰው ሥጋዊ አካሉ፡ በሚታየው ዓለም ላይ፥ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚጐናጸፈው የትንሣኤ አካል፡ በማይታየው ዓለም፡ የዘለዓለምን ሕይወት ወርሶ ለመኖር የሚያበቁትን ጸጋዎች ሊያስገኝለት ነው፤

፫ኛ፡ እነዚህ ጸጋዎች፡ ወደእማኙ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉባቸውን ምሥጢራትና ሥርዓታት ሊመሠርት ነው፤

፬ኛ፡ እኛ፡ የእግዚአብሔር ወገኖች የኾንነው ሰዎች፡ ሥጋዊዉንም ኾነ መንፈሳዊዉን ሕይወት፡ በዚህ ዓለም፡ በሥጋ፡ እንዴት መኖር እንደሚገባን፡ ማለትም፡ ዐሥሩ ን የእግዚአብሔር የሕይወት ቃላት (ትእዛዛት)፡ ልንፈጽማቸው የሚገባን፡ እንዴት እንደኾነ፥ ደግሞም፡ ልንጸልይ፥ ልንጸምና ልንመጸውት፥ በጠቅላላም፡ ሃይማኖታችንን፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኳችን አጽንተንና በንስሓ አንጽተን፡ በበጎ ምግባር ልንገልጸው የሚገባን፡ እንዴት እንደኾነ፡ በአርአያነቱ ጭምር፡ ሊያስተምረን ነው፤

፭ኛ፡ "እግዚአብሔር፡ ማነው? ምንድር ነው? መልኩስ፥ ግብሩስ ምንን ይመስላል? እውነት፡ ምንድር ናት?" ለሚሉት፡ የሰብአዊው ፍጡር የማያቋርጡ፡ ረቂቃን ጥያቄዎች፡ ራሱ፡ በገዛ ድና በእውን ተገልጦ፡ ግዙፍ የኾነውን አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ነው::

ይህም እውነታ፡ የእግዚአብሔር ባለሟሉ አገልጋይ የኾነው ሙሴ፡ የሰው ዘር ኹሉ፡ ፍላጎትና ምኞት የኾነውን፡ *"እባክህ፡ ክብርህን አሳየኝ!"* ሲል፡ ለፈጣሪው ባቀረበው ጥያቄ ታውቋል፤ ፍጡሩ ሰው፡ ይህን ጥያቄ ባቀረበለት ጊዜ፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ የሰጠው የተስፋ መልስ፡ *"ሰው፡ አይቶኝ አይድንምና፡ ዛሬ፡ ፊቴን ማየት አይቻልህም፤* የምታይበት ጊዜ ግን ይመጣል!" የሚል ስለነበረ፡ ያ፡ የተስፋ ቃል ተፈጽሞለት፡ ሙሴ፡ በዚያ ጥያቄው ጊዜ፡ በመለኮትነቱ ባሕርይና ግርማ ሊያየው ያልቻለውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ገዝፎ ሊያየው በቅቷል:: የዚህም፡ ምሥጢር ከሥተት፡ ከሐዋርያት አንዱ፡ ፊልጶስ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ *"አብን አሳየንና ይበቃናል!"* ብሎ በጠየቀው ጊዜ፡ በተገኘው መለኮታዊ መልስ ታውቋል:: ይህም፡ *"አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል ዘመን፡ ከእናንተ ጋር ስኖር፡ አታውቀኝምን? እኔን ያየ፡ አብን አይቷል፤ እንዴትስ አንተ፡ 'አብን አሳየን' ትላለህ?*

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ሥጋዌ።

### እግዚአብሔር፡ ለምን ሰው መኾን ፈለገ?

*"እኔ፡ በአብ እንዳለሁ፤ አብም፡ በእኔ እንዳለ፡ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል፡ ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን፡ በእኔ የሚኖረው አብ፡ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ፡ በአብ እንዳለሁ፥ አብም፡ በእኔ እንዳለ፡ እመኑኝ፤ ባይኾንስ፡ ስለራሱ፡ ስለሥራው እመኑኝ።"* ባለው፡ በወንጌላዊው ቃል፡ ትክክለኛውን ፍቺና ምስክርነት አግኝቷል።[፺፮]

እንግዴህ፡ እናንተም፡ በማስተዋል ተመልከቱ! በመጀመሪያው ውይይታችን ጊዜ እንደተገነዘባችሁት፡ "አዳም" እና "ሔዋን" በሚል ስም፡ ወንድና ሴት አድርጎ፡ በመልኩ የፈጠረው ሰው፡ በራሱ ምርጫ፡ የተቀዳጀውን የተቀደሰ ክብር፡ በርኩሰት አቃልሎና በፈጣሪው ፈቃድ ላይ ዓምፆ፡ ራሱን፡ ለዲያብሎስ የከፋት አገዛዝ፥ ለኃጢአት ጽኑ ቀንበርና ለሞት የጻዕር ፍዳ በመዳረጉ፡ ለ፭ሺ፭፻ ዓመታት ሲማቅቅ መኖሩን አውቃችኋል።

'እግዚአብሔር አብ'፥ 'እግዚአብሔር ወልድ'፥ 'እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ' ተብሎ፡ በሦስት ስም፥ በሦስት አካላትና በሦስት ግብራት የታወቀው፡ አንድ አምላክ የኾነው ፈጣሪ፡ ከሦስትነቱ አካል፡ አንዱ፡ 'እግዚአብሔር ወልድ'፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ መለኮታዊ ግብር፡ ከድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፡ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ በፍጹም ተዋሕዶ በመፀነስ፡ እንዲህ፡ በሰውነት ከተወለደ በኋላ፡ ልዩ ልዩ ፈተናዎችንና መከራዎችን ተቀብሎ፥ አዎን! ያን በመሰለ ውርደትና ሥቃይ ላይ ለሚገኘው ሰብአዊ ፍጡሩም፡ ቤዛ ኾኖ፡ ይህንኑ ፍጡሩን፡ ለዲያብሎስ ከመገዛትና ከኃጢአት ቀንበር፥ ከሞት ፍዳም አዳነው።

እግዚአብሔር ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱ ምክንያት፡ የእርሱ የኾነችውን እውነት፡ ከምድር ገጽ ሊያጠፋ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ ሲጥር የኖረውን ዲያብሎስን፡ ከነሠራዊቱ፡ ድል በማድረግና የሐሰት ሥራዎቹን፡ በእግዚአብሔር እውነት በመደምሰስ፡ ቀደም ብለው የተመለከቱትን አምላካውያት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መኾኑን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተከሰሰበትና በተፈረደበት አደባባይ ላይ፡ እንዲህ ሲል፡ በመጨረሻ የተናገረው ቃል ያጠቃልለዋል፤ *"እኔ ለእውነት ልመሰክር፡ ስለዚህ ተወልጃለሁ፡ ስለዚህም፡ ወደዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የኾነ ኹሉ ድምፄን ይሰማል።"*[፺፯]

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እናንተ የምትሰሙት፡ የማንን ድምፅ ነው? ቀድሞ፡ አዳምንና ሔዋንን በገነት ፈጥሮ፡ *"እንዳትሞቱ፡ የከፉዪቱን ዛፍ ፍሬ አትብሉ!"* ያላቸውን፥ ኋላም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶና በቅዱስ መስቀል ላይ ተሠውቶ፡ እናንተንና እኔን፥ መላ ፍጥረቱንም፡ ከክፉው ኃይል፥ ከኃጢአትና ከሞት በማዳን፡ *"ለዘለዓለም ሕያዋን ኾናችሁ ትኖሩ ዘንድ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ሥጋዬን ብሉ! የፈሰሰ ደሜንም ጠጡ!"* ያላቸውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ ብቻ ነውን? ወይስ፡ እርሱ፡ *"አትብሉ!"* ያለውን፡ "ብሉ!"፥ *"ብሉ! ጠጡ!"* ያለውን፡ "አትብሉ! አትጠጡ!" የሚለውን፡ የሐሰት አባት፡ የዲያብሎስን ድምፅ? እናንተና እኔ የሰማነውና የምንሰማው፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ ብቻ በመኾኑ፡ እጅግ ደስ ሊለን ይገባል።

## የሥጋዌ ምሥጢር የተገለጸበት ጊዜ::

**ጥያቄ:-** *ይህ የሥጋዌ ምሥጢር የተገለጸው መቼ ነው?*

**መልስ:-** ከቀደሙት: በትውፊት እየተነገረ እንደደረሰን: የአምላክ ቃል: እግዚአብሔር ወልድ: *"አድናችኋለሁ!"* ብሎ: ለአዳምና ሔዋን በሰጣቸው ተስፋ መሠረት: የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል: ለድንግል ማርያም ታይቶ: *"ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና: አትፍሪ! እነሆም: ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ፤ ስሙንም 'ኢየሱስ' ትዪዋለሽ!"* ብሎ ካበሠራት በኋላ: *"ማርያም: 'እነሆኝ: የእግዚአብሔር ባሪያ! እንደቃልህ ይኹንልኝ!"* ባለችባት ቅጽበት: እግዚአብሔር ቃል: በታኅሣሥ ፩ ቀን: በድንግል ማርያም ማሕፀን ተቀረፀ፤ ማለትም: በዚያች ቅጽበት: እግዚአብሔር ወልድ: በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ሥራ: ከድንግል ማርያም: ከፍጹም ሥጋዋና ከፍጹም ነፍሷ የነሣውን አካልና ባሕርይ: ከመለኮታዊ አካሉና ባሕርዩ ጋር አዋሕዶ: በማሕፀኗ ሰው ኾኖ ተፀነሰ::

በ፱ ወር ከ፭ ቀኑም: አዳምና ሔዋን ተፈጥረው: የመጀመሪያውን ቃል ኪዳን ከተቀበሉባት ቀን አንሥቶ ሲቆጠር: ልክ: የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ዘመን ሲፈጸም: ከዓመቱ: አንድ ዓመት፥ ከወሩ: አንድ ወር፥ ከዕለቱ: አንዲት ዕለት፥ ከሰዓቱ: አንዲት ሰዓት ሳያጓድልና ሳያሳልፍ: በጽኑ ቀጠሮው: ጳጉሜ ፮: እኩለ ሌሊት ላይ: ለመስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት: መጽሐፍ: *"እሑድ: ዕለተ ተልሕኮቱ ለአዳም"* ማለትም: *"ቀዳማዊው አዳም በተፈጠረባት በእሑድ ዕለት"* አጥቢያ: *ዳግማዊው አዳም ተወለደ::*[፶፫]

እርሱም: "ከፍጥረተ ዓለም አስቀድሞ: ከእግዚአብሔር አብ: በመለኮት አካልና ባሕርይ: ያለእናት በመወለዱ፥ በፍጥረተ ዓለሙም የመጨረሻ ዘመን: ከቅድስት ድንግል ማርያም: በሰውነት አካልና ባሕርይ: ያለአባት በመወለዱ: በእነዚህ ኹለት ልደታት: በተዋሕዶ ስለከበረ: ከኹለት አካል: አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርይ: አንድ ባሕርይ ኾኖ: ስሙ: "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተባለ:: ይህም ማለት: "በእርሱ: በኢየሱስ ክርስቶስ: የመለኮት አካልና የሰውነት አካል፥ የመለኮት ባሕርይና የሰውነት ባሕርይ: ያለመቀላቀልና ያለመጠፋፋት፥ ያለመለዋወጥና ያለትድምርት (ጭማሪ ሳይኾን): በተዋሕዶ: አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ኾነዋል!" ማለት ነው:: በዚህም: የሥጋዌ ተስፋ: ማለትም: እግዚአብሔር ወልድ: የመኾኑ ነገር፥ ትንቢቱ: ተፈጸመ፥ ምሥጢሩም ተገለጠ::

ያች: የሥጋዌ ምሥጢር የተፈጸመባትና የተገለጠባት ቅጽበት: በዘመነ ብሉይ: እያንዳንዱ ዓመት: "ዓመተ ፍዳ" እየተባለ: የ፭ሺ፭፻ ዓመታት ዘመን ኰንኖ አብቅቶ: እያንዳንዱ ዓመት: "ዓመተ ምሕረት" እየተባለ መጠራት የጀመረበት: የአዲስ ኪዳኑ ዘመነ ምሕረት የባተባት (የገባባት) የእኩለ ሌሊት እላፊ አፍታ ናት፤ እርሷም: መስከረም ፩ ቀን፥ ፩ ዓመተ ምሕረት ተባለች:: ኢትዮጵያውያን: "የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ቀን ናት" ብለው ሲያከብሩዋት የኖሩትና የሚኖሩት: ይህችን ዕለት መኾኗን አስተውሉ![፶፬]

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ሥጋዌ።

---

### የመለኮትና የትስብእት (የሰውነት) መዋሐድ።

**ጥያቄ፦** *ይህ፡ የመለኮትና የትስብእት መዋሐድ እንዴት ነው?*

**መልስ፦** "ተዋሕዶ" የምንለው፡ መለኮት (አምላክነት) እና ትስብእት (ሰውነት)፡ በአኳኋኗ በባሕርይ፡ የመዋሓዳቸው፡ ማለትም፡ አንድ የመኾናቸው ነገር የሚታወቅበት ሥርዓተ እምነት ነው፤ ይህም ውሕደት፡ በጋለ የብረት ፍሕም ይመሰላል። መለኮት፡ እንደፍሕሙ፥ ትስብእት፡ እንደብረቱ። ብረቱና ፍሕሙ ሳይለያዩ፡ ብረቱ፡ የብረትነቱን ባሕርይ ሳይለቅ፥ ፍሕሙም፡ የእሳትነት ባሕርዩን ሳይለቅ፡ ኹለቱም፡ ምንነታቸውን እንደጠበቁ፡ እርስ በርሳቸው ተጠባብቀው እንደሚገኙ ማለት ነው። ፍሕሙ፡ በብረቱ ገዝፎ እንደሚታይ፡ ብረቱም፡ በፍሕሙ ግለት፡ በሌጣ እጅ ሊዳሰስ እንደማይቻል ኹሉ፡ እንዲሁ፡ "ረቂቅ መለኮትም፡ ይህን ርቅቀቱን ሳይለቅ፡ በተዐቅቦ (ባሕርዩን እንደጠበቀ በመገኘት)፡ ግዙፍ ሥጋን ኾነ! ግዙፍ ሥጋ፡ ግዙፍነቱን ሳይለቅ፡ በተዐቅቦ፡ ረቂቅ መለኮትን ኾነ! ምሉዕ በኵለሄ (በኹሉ የመላ) የኾነው መለኮት፡ ይህን ምልዓቱን ሳይለቅ፡ በተዐቅቦ፡ ውሱን ሥጋን ኾነ! ውሱን ሥጋ፡ ውሱንነቱን ሳይለቅ፡ በተዐቅቦ፡ ምሉዕ በኵለሄ የኾነውን መለኮት ኾነ! የመለኮት የኾነው፡ ለሥጋ፥ የሥጋ የኾነው ለመለኮት ኾነ!" ማለት ነው።

**ጥያቄ፦** *አሁንም፡ ይህ፡ የተዋሕዶ ነገር፡ እንደረቀቀብን ነውና፡ በበለጠ ብታብራሩልን?*

**መልስ፦** በእየራሳችሁ እንደምታዩት፡ ነባቢት ነፍስንና ደመ ነፍስን የያዘው ሰውነት፡ በሥጋ ምክንያት፡ ግዙፍ፥ ውሱን፥ ጠባብ ነው፤ መለኮት ግን፡ በሰማይና በምድር፥ በአየርና በጥልቁ የመላ፡ ስፉሕ፥ ረቂቅ ነው። እኒህ ኹለት፡ የሰውነትና የመለኮት አካላትና ባሕርያት፡ እንዴት እንደተዋሓዱ፡ እስኪ፡ በምሳሌ ላስረዳችሁ! እንደምትመለከቱት፡ "ብሌን" የምትባለው፡ ይህች፡ የዓይናችን ማዕከላዊ ብረት፡ እጅግ ትንሽ ናት፤ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህላለች። የፀሓይ ብርሃን ግን፡ በዚህ ዓለም የመላ ነው።

እንግዴህ፡ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህለው ብሌናችን፡ ባላት የማየት ኃይሏ፡ ማለትም፡ በእርሷ አማካይነት በሚከፈተው፡ የዓይናችን መስኮት በኩል፡ ይህን ዓለም መልቶት ከሚገኘው የፀሓይ ብርሃን ጋር ተዋሕዳ፡ ሰማይ፥ ደመና፥ ደንና ገመገም (እንደሰንሰለት የተያያዘ ተራራ)፥ የሰው ሥራ የኾነው ሕንፃም ካልጋረዳት በቀር፡ የዓለሙ ብርሃን እስካለበት አድማስ ኹሉ ደርሳ፡ ትመለከታለች። የሥጋም፡ ከመለኮት ጋር መዋሓድ፡ እንደዚህ ነው። ሲዋሓድም፡ ማየት፡ ለዓይን፥ መስማት፡ ለጆሮ፥ መናገር፡ ለአንደበት እንደሚስማማ ኹሉ፡ መለኮትም ከሥጋ ጋር ተስማምቶ ተዋሕዷል። እዚህ ላይ፡ ማየት፥ መስማት፥ መናገር፡ ለመለኮት፡ ምሳሌዎች ሲኾኑ፡ ዓይን፥ ጆሮና አንደበት ደግሞ፡ ለትስብእት (ለሰውነት)፡ ምሳሌዎች ናቸው። ራሱ እየነደደ፡ ለሌሎች የሚያበራውን ጧፍ፡ ያስገኙት፡ የፈትልና የሰም ውሕደትና ስምምነት፡ ለመለኮትና ለትስብእት ተዋሕዶ፡ ሌላ ምሳሌ ኾኖ ይነገራል።

እግዚአብሔር ወልድ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ የተጠራበት ስሙ፥ ወይም፡ ማንነቱ፡ "ብቻ የሰውነት"፡ ወይም፡ "ብቻ የመለኮት" ሳይኾን፡ መለኮትና ሰውነት ተዋሕደው፡ አንድ የኾኑበት ህላዌ ነው:: ይህም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱን፡ "እኛ" ብሎ፡ በኹለትነት ሳይኾን፡ "እኔ" ብሎ፡ በአንድ ነጠላ አመልካች ስም፡ በማመልከቱ ተረጋግጦ ይታወቃል:: "ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በተዋሕዶ፡ ከኹለት አካል፡ አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርይ፡ አንድ ባሕርይ ኾኖ፡ ከድንግል ማርያም ተወለደ!" ስንል፡ የመለኮት ፈቃድና የሰውነት ፈቃድ፥ የመለኮት ግብርና የሰውነት ግብር፡ በተዋሕዶ አንድ ኾኑ! "ፍጹም ተስማሙ!" ማለት ነው:: ከዚህ የተነሣ፡ *"ቃል ሥጋ ኾነ!"* ባለው፡ በወንጌላዊው ዮሐንስ መልእክት መሠረት፡ "አምላክ ሰው ኾነ! ሰውም አምላክ ኾነ!" እንላለን:: በኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ምንታዌ"፡ ማለትም፡ ኹለትነት ጠፍቷል፤ "ተዋሕዶ"፡ ማለትም፡ አንድነት ጸንቷል::

*"ቃል"* የተባለው እግዚአብሔር ወልድ፡ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ሲፀነስ፡ የእናቱን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ማኅተመ ድንግልናዋን እንዳላለወጠው ኹሉ፥ ሲወለድም፡ ማኅተመ ድንግልናዋን አላለወጠውም:: የፊት ወዝ (ላብ)፡ ከግንባር ሲንጠፈጠፍ እንጂ፡ ክቆዳው ሲወጣ እንደማይታይ፡ የኢየሱስ ክርስቶስንም፡ በድንግልና መወለድ፡ አቅራቢያው በኾነው፥ በዚህ የተፈጥሮ ድርጊት መስሎ፡ ማስረዳት ይቻላል::

### የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኹለት ልደት::

ጥያቄ:- *ቀደም ብለህ፡ "ኹለት ልደት" ያልኸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኹለት ጊዜ መወለድ፡ እንዴት ነው?*

መልስ:- *"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም፡ እግዚአብሔር ነበረ:: ...ቃልም፡ ሥጋ ኾነ!"* ብሎ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ እንደጻፈው፡ *"ቃል"* የተባለው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ቅድመ ዓለም (ዓለም ከመፈጠሩ በፊት) ከእግዚአብሔር አብ፡ በመለኮትነት፡ ያለእናት መወለዱ፡ ፩ (አንድ) ልደት ሲኾን፡ ይህ የመጀመሪያው ልደቱ ነው፤ ኋላ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ያው *"ቃል"፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ"* ተብሎ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በሰውነት፡ ያለአባት መወለዱ፡ ፩ (አንድ) ልደት ሲኾን፡ ይህ ኹለተኛው ልደቱ ነው፤ *"ወልደ አብ፥ ወልደ ማርያም (የአብ ልጅ፥*[፺፩] *የማርያም ልጅ) በተዋሕዶ ከበረ!"* የሚባለው፡ ፪ (ኹለት) ልደት ይህ ነው::

*"በተዋሕዶ ከበረ"* ማለትም፡ "ቃል" እግዚአብሔር ወልድ፡ ራሱ፡ ቀብዕ፥ ራሱ ቀቢና ራሱ ተቀቢ ኾኖ፡ በተለየ አካሉ፡ ለተዋሓደው ሥጋ፡ ማለትም፡ ለሰውነት፡ እንደወርቅና እንደብር ተዋሕዶ፡ ክብር ኾነው ማለት ነው:: ወርቅና ብር ሲዋሓዱ፡ ወርቁ፡ ለብሩ፥ ጌጥ፡ ክብር ኾኖት ይኖራል፤ ሠሪው፡ አንጥረኛው ነው:: እንደዚሁ ኹሉ፡ ትስብእትና መለኮት ለተዋሓዱበት፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ፡ እንደአንጥረኛው ናቸው::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ሥጋዌ::

### የኢየሱስ ክርስቶስ: ኹለት ልደት::

---

*ሥጋ* (ሰውነት): እንደብር ሲኾን: "*ቃል*" እግዚአብሔር ወልድ: በተለየ አካሉ: እንደወርቅ ነው:: የወርቁንና የብሩን ውሕደት: "የአንጥረኛው እጅ: *ሠራው*: አስጌጠው!" ይባላል እንጂ: "ክብር: ጌጥ ኾነው!" አይባልም:: እንደዚሁ ኹሉ: አብ: ወልድ: *መንፈስ* ቅዱስ: *ሥጋን* (ሰውነትን): "ፈጠሩት: ከመለኮት ጋር አዋሓዱት!" ይባላል እንጂ: አብ: *መንፈስ* ቅዱስ: *ሥጋን*: "ተዋሓዱት: ክብር ኾኑት!" አይባልም:: በተለየ አካሉ: *ለሥጋ*: "ክብር: ጌጥ የኾነው": *ራሱ*: ወልድ ብቻ ነውና::

ስለዚህ: ይህን: "*በተዋሕዶ ከበረ*" የሚለውን ምሥጢር: ጠንቅቃችሁ ማወቅ አለባችሁ! ምክንያቱም: በአገራችን: "ጸጋ": "ቅብዓት": "፫ ልደት" የሚል ጠንቀኛ ባህሎችን ትተውብን የኼዱትን: በተለይ: "የሮማ ካቶሊክን": እንዲሁም: "የግሪክ ኦርቶዶክስን" የመሰሉትን አብያተ ክርስቲያናት: ከእኛ: ከተዋሕዶው ሃይማኖት የሚለያቸው: የነገረ መለኮት ትምህርታቸው: ከዚህ: ከተዋሕዶው ምሥጢር የተዛባ በመኾኑ ነው::

**ጥያቄ:-** *እነዚህ: "ጸጋ": "ቅብዓት": "፫ ልደት" ብለህ የጠቀስካቸው አባባሎች ምንድር ናቸው? ለማወቅ ያህል: ጥቂት አስፋፍተህ ብታስረዳን?*

**መልስ:-** እነዚህ ይትበሃሎች: የራሳችሁን የተዋሕዶ ሃይማኖት ምሥጢር: በማያስፈልግ የትርጓሜ ችግር እንዳያምታቱባችሁ: ስለእነርሱ: እምብዛም አትጨነቁ! በዝርዝር ለማወቅ ከፈለጋችሁ ግን: በየግላችሁ: ከመምህራንና ከመጻሕፍት በበለጠ ለመረዳት ሞክሩ! መሠረታዊ ምንነታቸውን ለማወቅ ያህል ብቻ: እዚህ ላይ: አጭር መግለጫን እሰጣችኋለሁ::

በግእዝ: "ቅቡዕ": በኢትዮጵያኛ: "የተቀባ": በዕብራይስጥ: "መሢሕ": በግሪክኛ: "ክርስቶስ" የሚለው ሉዓላዊና ትንቢታዊ ቃል: ቅድመ ዓለም: ከእግዚአብሔር አብ: በመለኮትነት: ያለእናት ተወልዶ ለኖረውና ኋላ: በመጨረሻው ዘመን: "ኢየሱስ" በሚል መጠሪያ: ከቅድስት ድንግል ማርያም: ያለአባት: በሰውነት ለተወለደው: ለእግዚአብሔር ወልድ የተሰጠ: የማንነቱ መታወቂያ፥ የሹመት ስም ነው:: በእነዚህ ኹለት ልደቶቹ ላይ ከጸናው: ከተዋሕዶ ትምህርት በኋላ: እግዚአብሔር ወልድ: ሦስተኛ ልደትን እንደተወለደ የሚያስመስል: የኑፋቄ ትምህርት ተፈጠረ!

ይህ: የኑፋቄ ትምህርት: እግዚአብሔር ወልድ: "ራሱ: ቅብዕ፥ ራሱ ቀቢና ራሱ ተቀቢ ኾኖ: በተለየ አካሉ: ለተዋሓደው ሥጋ (ሰውነት): ክብር ኾነው!" የሚለውን የተዋሕዶን መሠረታዊ አቋም የሚያቃውስ ኾኖ ስለተገኘ፥ ደግሞም: በዮርዳኖስ ወንዝ: በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ: እኛ ሰዎች: በምሥጢረ ጥምቀት: ከመንፈስ ቅዱስና ከውኃ ተወልደን: የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር እንድንቀዳጅ ያደረገበትን ጸጋ በሚመስል ኹኔታ: እርሱም: "ሥጋን: በማሕፀን ሲዋሓድ ጀምሮ: መንፈስ ቅዱስ: ክብርም፥ ቅብዕም ኾኖት: በቅብዓት፥ በጸጋ: የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ስለኾነ: ሦስት ልደት!" የሚል በመኾኑ: "፫ ልደት"፥ "ጸጋ"፥ "ቅብዓት" ተባለ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ "መቀባት"፡ በእግዚአብሔር መሾም ነው:: የሹመቶቹ ኹሉ መሠረቱና ቀዳሚው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በክርስትናው ጊዜ፡ በውኃና በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቀ በኋላ፡ ቅብዓ ሜሮንን በመቀባት የሚቀበለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾን ክብር ነው፤ ለቤተ ሕዝብና ለቤተ ምልክና፥ ለቤተ ክህነትም አባልነትና አገልግሎት፥ ለአጼነትና ለነቢይነት ጭምር፡ የሚያበቃው ጸጋ፡ ይህ ሹመት ነው:: ከዚህ ቀጥሎ፡ ከእነዚህ ሹመቶች መካከል፡ ከብሉይ ኪዳኑ ነቢይነት በቀር፡ ለአንዳቸው የታጨው ሰው፡ በመጀመሪያ፡ በቅዱሱ ኪዳንም ሕዝብ ይመረጣል፤ ከዚህ በኋላ፡ በዘመነ ብሉይ፡ በነቢይ፡ ወይም በካህን እጅ፡ የተቀደሰውን ዘይት ይቀባል:: በተቀባም ጊዜ፡ የሹመቱን ሥራ የሚያስፈጽምበት፡ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት፥ ሥልጣንና ችሎት ያድርበታል:: በዘመነ ብሉይ፡ ለነቢይነት ሹመት የሚታጨው ሰው ግን፡ በእግዚአብሔር ተመርጦ፡ በእግዚአብሔር ይቀባል:: የብሉይ ኪዳኑ ነቢይነት፡ በመጥምቁ ዮሐንስ፡ አብቅቷል:: ነቢይነት፡ በአዲስ ኪዳኑ መሢሕ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሞ፡ አብቅቷል::

በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ የሚያገለግሉት ሕዝባውያን፥ ምሉካውያንና ካህናት፡ እንዲህ እየተቀቡ፡ የአገልግሎት ሥልጣንን እንደሚቀበሉ ኹሉ፡ "ኢየሱስም፡ ቅቡዕነትን፥ ወይም መሢሕነትን፡ ወይም ክርስቶስነትን፡ በመንፈስ ቅዱስ ቅብዕነት፡ ከእግዚአብሔር፡ በዚህ መልክ ተቀብቶ፡ በሰውነቱ፡ የጸጋ ልጅነትን፥ በአምላክነቱ፡ የባሕርይ ልጅነትን አገኘ!" ለማለት፡ መናፍቃን፡ እነዚህን፡ " "ቅብዓት"፥ "ጸጋ" እና/ወይም "፫ ልደት" የሚባሉትን ቃላት፡ ሰው ለኾነው፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስም ይጠቀሙባቸዋል::

ይህ የኑፋቄ እምነትና ትምህርት ወደአገራችን የገባው፡ በአሕመድ ግራኝ ወረራ ምክንያት፡ ኢትዮጵያን እንዲረዱ፡ በዚያ ዘመን ከነበረው፡ ከአጼ ንብለ ድንግል መንግሥት ተጠይቀው፡ ከተላኩት፡ የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር አብረው በመጡት፡ የተዋሕዶ ሃይማኖት ተቃዋሚ በኾኑት፡ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ልኡካን አማካይነት እንደኾነ ይነገራል::

"ተዋሕዶ"፥ "Orthodox" እና "Coptic" ስለሚባሉት ቃላት::

ጥያቄ:- *በኢትዮጵያ ሃይማኖትና ቤተ ክርስቲያን ስም ላይ፡ "ተዋሕዶ" የሚለው ቃል የተጨመረው፡ ለምን እንደኾነ፡ እውነተኛ ምክንያቱን፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ ብትገልጽልን?*

መልስ:- *"ተዋሕዶ"፡* የሚለው ቃል፡ ቀደም ብለው በተገለጹት ሐተታዎች እንደተብራራው፡ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር፡ አንዱ በኾነው፡ በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የተመሠረተ ነው::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ሥጋዌ።

### "ተዋሕዶ"፥ "Orthodox" እና "Coptic" ስለሚባሉት ቃላት።

---

የኢትዮጵያውያንን: የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት: ቀናነት፥ እውነተኛነትና ጥራት በትክክል ለመግለጽ፥ ለማረጋገጥም፥ እንዲሁም: ከሌሎቹ: የክርስትና እምነት ተከታዮች ከኾኑት: የዓለም ሕዝቦች መካከል ተለይቶ እንዲታወቅ ለማድረግ ሲባል: በራሳቸው: በኢትዮጵያውያን የተሰጠ ልዩ መጠሪያ ነው።

ቃሉ: ግእዝ እንደመኾኑ: ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን በቀር: ሌላ የሚጠቀምበት አገር፡ ሕዝብ፡ ሃይማኖት እና/ወይም ቤተ ክርስቲያን የለም፤ ከዚህም ጋር፡ ጥንት: በዘመነ ብሉይ: በኪዳን ልቦና ተመሥርቶ: ወደኪዳን ኦሪት የተሻለፈውንና ከዚያ ሲያያዝ መጥቶ: በዘመነ ሐዲስ: በኪዳን መንፈስ ቅዱስ: ለምሥጢረ ሥጋዌ የበቃውን: የኢትዮጵያውያንን ሃይማኖት እውነተኛነትና ትክክለኛነት ያረጋግጣል።

እንግዲህ: በማናቸውም ጊዜና ቦታ: እየራሳችሁንና ሃይማኖታችሁን ለማስተዋወቅ: *"ኢትዮጵያዊ ነኝ!"* ማለቱ ብቻ በቂ መኾኑን: ተረድታችሁ: ይህንኑ: በማስተዋልና በጥንቃቄ እንድትፈጽሙት ይኹን! ነገር ግን: በይበልጥ: በዚሁ: በምሥጢረ ሥጋዌ የተለያየ አተረጓጐም ምክንያት: በዓለም ክርስቲያኖች መካከል: የውስጥ መቃቃር ተፈጥሮ: በስምና በአስተዳደር ወደመለያየቱ ውድቀት ስለተደረሰ: ይህ ኹኔታ ካስከተለው ችግር ለመዳን: እጅግ አስፈልጎ: የሃይማኖት ወገንነታችሁን እንድትገልጹ የተጠየቃችሁ እንደኾነ: *"ሃይማኖቴ: ተዋሕዶ ነው!"*፥ እጅግ ቢበዛም: *"እኔ ተዋሕዶ ክርስቲያን ነኝ!"* ማለት ትችላላችሁ።

ጥያቄ:- *ታዲያ! የኢትዮጵያ: ተዋሕዶ ሃይማኖት፥ ወይም የኢትዮጵያ: ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን: በሚለው ስያሜ ላይ: "ኦርቶዶክስ" የሚለው ባዕድ ቃል የታከለው: ለምን እንደኾነ: በዚህ: አጋጣሚ ብታስረዳን?*

መልስ:- በቅዱሱ ኪዳን ጸንታ የኖረችው: ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ: ቀደም ብላ: ከኪዳን ልቦና ወደኪዳን ኦሪት ተሸጋግራ ከቆየችበት እምነቷ: በምሥጢረ ጥምቀት: ለክርስትና እምነት: ማለትም: ለኪዳን መንፈስ ቅዱስ የበቃችው: ከክርስቶስ ልደት በኋላ: አርባ ዓመት እንኳ ሳይሞላ መኾኑ እየታወቀ: በወንጌል ያመነችውና ቤተ ክህነቷ: "ቤተ ክርስቲያን" ተብላ: እንደአዲስ የተቋቋመችው: ክርስቶስ በተወለደ: በአራተኛው ምዕት ዓመት እንደኾነ የሚያስመስል: የሓሰት ይትበሃል ሠርጎ እንዲገባ ተደርጓል።

ይህም: "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" በሚለው: መደበኛና ተገቢ በኾነው ስያሜ መኻከል: ቢያስፈልግ እንኳ: "ተዋሕዶ" የሚለውን የራስ ቃል ማከሉ የሚበቃ ሲኾን: የዚሁ: የባዕዳኑ ይትበሃል ጠንቀኛ ውጤቶች የኾኑትን: "Coptic" (ኮፕቲክ) እና "Orthodox" (ኦርቶዶክስ) የተባሉትን: የግብፅና የግሪክ የሃይማኖት መለያ የኾኑትን ቃላት: በተቀጽላነት በመጨመር: "የኢትዮጵያ Coptic ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን" ወይም "የኢትዮጵያ Orthodox ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን" የሚለው አጠራር ጸንቶ እንዲቀጥል በመደረጉ ይታወቃል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህ አጠራር፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ያላትን የቀዳሚነት ደረጃ በመሻር፡ “የግብፅ ወይም የኦርቶዶክሳውያን”፡ ማለትም፡ “የግብፅ ወይም፡ የግሪክ፡ ከኹለቱ፡ የአንደኛቸው፡ ቅኝ” መኾኗን ለማረጋገጥና ባዕድ የኾነውን ዓላማ፡ በቀላሉ ከግብ ለማድረስ እንዲያመች፡ ኾን ተብሎ በዕቅድ የተቀነባበረ መኾኑ ግልጽ ነው:: ከዚህ ድርጊት፡ የተነሣ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸንታ፡ ለዝንተዓለም በኖረችው፡ በቀዳማዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ላይ፡ የእውነተኛ ማንነቷን፡ የህልውና ዕድሜዋንና የምሥጢረ ሃይማኖቷን መሠረታዊ አቅዋም በሚመለከት፡ ጠንቁ እስካሁን ሊወገድ ያልቻለ፡ እጅግ አሳሳችና አደናጋሪ፡ አሳፋሪም የኾነ፡ ከባድ ችግር መፈጠሩን፡ በግብር ደርሶ ከሚታየው ኹኔታ፡ በማስተዋል መመልከቱ አያዳግትም::

የዚህ ችግር መንሥዔ፡ የእነዚህ ባዕዳን ቃላት፡ በስሟ መካከል መዘንቅ (መደባለቅ) ሲኾን፡ ችግሩን የባሰ ያከበደው ደግሞ፡ ይኸው ድርጊት፡ በቀላሉና በአጭሩ ሊነቀሉ የማይቻሉ፡ ኹለት ዓበይት ጠንቆችን ተክሎ ስለኼደ ነው:: እርግጥ፡ "Coptic" “ኮፕቲክ”፡ “ቅብጥ” ወይም “ግብፅ” ማለት ስለኾነ፡ በግብፅ ቋንቋነቱና የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የኾነውን፡ ማናቸውንም ነገር በሚመለከት መልክ መጠቀሙ፡ በማንም ዘንድ፡ ጉዳት የለበትም:: "Orthodox" “ኦርቶዶክስ”፡ የሚለውም ቃል፡ ግሪክኛ ኾኖ፡ “የቀናች ሃይማኖት” ማለት ስለኾነ፡ በግሪክኛነቱና በቃሉ ትርጉም ረገድ፡ በማንም ዘንድ መጠቀሚያ ቢኾን፡ ቅር አያሰኝም:: ጉዳቱና ቅሬታው የተፈጠረውና የመጣው ግን፡ እነዚሁ፡ ኹለት የባዕዳን ቃላት፡ ከዚህ፡ እጅግ በተለየና በረቀቀ መንገድ፡ ኹለት ዐበይት ጠንቆችን በማስከተላቸውና ትተው በማለፋቸው ነው፤ እነዚህ ጠንቆችም፡ የሚከተሉት ናቸው:-

የመጀመሪያው ዓቢይ ጠንቅ፡ "Orthodox" “ኦርቶዶክስ” ወይም "Coptic" “ኮፕቲክ” የሚለው፡ ይኸው ባዕድ ስያሜ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በአበው ልቦና መሥርቷትና በመካከሉ፡ በኪዳኑ አሪት አጽንቷት፥ በመጨረሻ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የፈጸማትን፥ ከዚህ የተነሣም፡ በዓለም ላይ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ ቀድማና ለብቻዋ እጅግ ጥንታዊት ኾና የኖረችውን፥ አንዲት የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን ቤተ ክህነት፡ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ባለው፡ በአራተኛው ምዕት ዓመት ግድም፡ በዚሁ ስም ተለይተው በታወቁት፡ በግሪክ፡ ወይም በኮፕት (በግብፅ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርታ እንደተቋቋመች ማስመሰሉ ነው::

ከጠንቆቹ መካከል፡ የሚከፋው ኹለተኛው ደግሞ፡ ከዚሁ፡ “ኦርቶዶክስ” ከሚለው ቃል የተነሣ፡ ኢትዮጵያ፡ በነገረ መለኮት ሃይማኖታዊ አቋሟ፡ ከካቶሊኮች ጋር ተመሳሳይ በኾነው፡ በግሪኮች ኦርቶዶክሳዊ እምነት ላይ እንደተመሠረተች ያስቆጠራት መኾኑ ነው:: የኋላ ኋላ ግን፡ ኢትዮጵያውያን፡ “ተዋሕዶ” የሚለውን የግእዝ ቃል፡ ቢቸግራቸው፡ በመጠሪያ ስሟ መካከል ተጨማሪ እንዲኾን አድርገው፡ “የኢትዮጵያ Orthodox ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን” የሚለውን አጠራር የሰጡት፡ “ሃይማኖታቸው የቆመበትን ጥንታዊ መሠረት፡ ለጊዜው፡ ከእነዚሁ ጠንቆች ለማዳን ይችል ይኾናል፤” ብለው በማሰብ መኾኑን፡ ልትገነዘቡት ይገባል::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
## ምሥጢረ ሥጋዌ::
### "ተዋሕዶ"÷ "Orthodox" እና "Coptic" ስለሚባሉት ቃላት::

---

አዎን! እኒሁ: የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን: የእግዚአብሔር ልጅ: በፍጹም ሰውነት ስለመገለጡ: ቤተ ክህነታቸው ያላትን: "የምሥጢረ ሥጋዌ ሃይማኖታዊ አቋም: በትክክል ያስረዳልናል፡ ለዚህም ችግር መፍትሔ ሊኾነን ይችላል" ብለው ያከሉት: ይህ: "ተዋሕዶ" የሚለው ቃል: እውነትም: በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተገለጸው: የትስብእትና የመለኮት የውሕደት ምሥጢር: ፍጹም የኾነውን ትርጉም: ያለምንም ሕፀፅ: በተሟላ ኹኔታ ሊያስተላልፍ የቻለ መልካም ምርጫ መኾኑ ታምኖበታል:: ይኸውም: "ተዋሕዶ" የሚለው: ይኸው ቃል: ቀደም ብዬ እንዳተትሁላችሁ: ተቀዳሚና ተከታይ ሳይኖረው: በመንፈስ ቅዱስ ግብር: ለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈጸመውን: የእግዚአብሔርን ሰው የመኾን መለኮታዊ ምሥጢር: በሚበቃ ግልጽነት የሚያስረዳ በመኾኑ ነው:: እንዲህ: ረቂቅ የኾነውን: የሃይማኖት ነገር: አጉልቶና አግዝፎ÷ ምሥጢር የኾነውንም ገልጾና ተርጉሞ የሚያስረዳ በመኾኑ: ለዚህ "ተዋሕዶ" ለሚለው የተሟላ ኢትዮጵያዊ ቃል: "ኦርቶዶክስ" የሚል: ሌላ ባዕድ የኾነ ደባል: ባላስፈለገው ነበር፤ ራሱ: ብቻውን: በቂ ኾኖ ይገኛልና::

ባዕዳን ግን: ያንኑ: ጠንቀኛ ተግባራቸውን: አሁንም ሳያለዝቡ: ይህንኑ "ተዋሕዶ" የሚለውን ቃል: ሌላ የትርጓሜ ሐተታ እንዳለው በማስመሰል: ሊያማስኑት ሲሞክሩ ይታያል:: ይኸውም: "ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጸው: የሰውነት ባሕርዩን በማጥፋት: በአንድ የመለኮት ባሕርይ ብቻ ነው" ለሚለው: ለአውጣኪስ የኑፋቄ ትምህርት የተሰጠው: "Monophysite" "ሞኖፊዚት" የሚባለው ይትበሃል: ከዚሁ ከ"ተዋሕዶ" ቃል ጋር "ተመሳሳይነት አለው" እያሉ በሚያስፋፉት የሓሰት ትርጓሜያቸው ነው::

እንግዴህ: ኢትዮጵያ: የባዕዳን የኾነውን በማይከተለው: በራሷ ባህል: በቤተ ክህነቷ÷ በቤተ ምልክናዋና በቤተ ሕዝቧ መካከል መለያየትና መከፋፈል ሳይኖርባት: "ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚለው አቋሟ: አንዲት ስለኾነች÷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም: በዚሁ: በባለሚሶ ዘርፍነቷ: የያዘችው: ይኸው ስሟ: እንዳለ: ማንነቷን: ራሱ ስለሚናገርና እርሱው ስለሚበቃት: ለኢትዮጵያም ያለቻት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በአበው ልቦና: የመሠረታት÷ በነቢያት ቃል: ያጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ የፈጸማት÷ በድንግል ማርያምም: ሕያው ኾና ህልውናዋን የቀጠለች: እርሷ: አንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ስለኾነች: ሌላ ተጨማሪ መለያ ስያሜ ከቶ አያስፈልጋትም:: ዳሩ ግን: እውነታው ይህ ኾኖ ሳለ: በዚህ ስሟ ላይ: "Orthodox" የሚለው ስያሜ በመጨመሩ: ዛሬ ያለችውን: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን: የኢትዮጵያ ሳትኾን: የግብፅ መኾኗን: በራስ ምስክርነት ለማረጋገጥ ተቻለ:: ሌሎቹም ባዕዳን: ወደኢትዮጵያ ላስገቡት ሃይማኖታቸው: እየራሳቸውን: "በኢትዮጵያ" በማለት ፋንታ: "የኢትዮጵያ" ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን÷ "የኢትዮጵያ" ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን÷ ወዘተ. እያሉ ለመጥራት ለቻሉበት ማሳሳቻ: አመቺ በር ተከፍቶላቸው: ይህንኑ[፶] ልማድ: እንዴት: እየተጠቀሙበት እንዳሉ: ራሳችሁ የምትመለከቱት ነው::

## ስለምሥጢረ ሥጋዌ ማጠቃለያ።

*ጥያቄ፡- እግዜር ይስጥልን! እስካሁን ላቀረብናቸው ጥያቄዎቻችን፡ ተገቢውን መልስ በማግኘት፡ በሚበቃ ተረድተናልና፡ የምሥጢረ ሥጋዌን ነገር፡ ብታጠቃልልን?*

መልስ፡- የምሥጢረ ሥጋዌን ሐተታ፡ ከዚህ በሚከተለው ፍሬ ቃል፡ አጠቃልልላችኋለሁ፡- "እግዚአብሔር ወልድ" ሰው በኾነ ጊዜ፡ በአንደኛው ወገን ያለው፡ የፍጹም አምላክነት፡ አካልና ባሕርይ፥ በኹለተኛው ወገን ያለውን፡ የፍጹም ሰውነት፡ አካልና ባሕርይ፥ ወይም፡ በኹለተኛው ወገን ያለው፡ የፍጹም ሰውነት፡ አካልና ባሕርይ፥ በአንደኛው ወገን ያለውን፡ የፍጹም አምላክነት፡ አካልና ባሕርይ፡ ሳያጠፋው፡ ወይም ሳይለውጠው፡ ወይም ሳይውጠው፡ በኹለቱም ወገኖች ያሉት፡ ፪ አካላትና ፪ ባሕርያት፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ጥበብ፡ በተዓቅቦ ተዋሕደው፡ ተቀዳሚ፡ ተከታይ በሌለው፡ በአንዱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንድ አካል፥ አንድ ባሕርይ ኾነዋል፤ ይህም ማለት፡ ራሱን፡ በኹለትነት ሳይኾን፡ በአንድነት፡ "እኔ" ብሎ በሚጠራው፡ በአንዱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተዋሕዶ ህላዌ ውስጥ፡ የሰውነት ፈቃድ፡ ለመለኮት ፈቃድ፡ ፈጽሞ በመገዛቱ፥ በዚህ፡ አንድ በኾነ ፈቃድ፡ መለኮት፡ የሰውነትን ሥራ፥ ሰውነትም፡ የመለኮትን ሥራ ሠሩ፡ ማለት ነው።

ተቀዳሚ፡ ተከታይ የሌለው ማለትም፡ ከእርሱ በቀር፡ ከፍጥረት በፊት እንሥቶ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ድረስ ባልተደረገ፡ ከእርሱ ጀምሮና ከእርሱ በኋላ፥ እንግዴህ ወዲህም፡ ለዘለዓለም በማይደረግ፡ ዕፁብ ድንቅ በኾነ መለኮታዊ ምሥጢር፡ የቀደመውም ኾነ፡ የሚከተለው የሌለ፡ አንድ ወልድ ዋህድ፡ በሰውነት የታየበት፡ ፍጹም የብቸኛነት ህላዌ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ፡ "አምላክ፡ በተዋሕዶ፡ ሰው ኾነ! ሰውም፡ በተዋሕዶ፡ አምላክ ኾነ!" የሚል ትርጉም ያለው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ተሰጠ። በፍጥረት መጀመሪያ፡ *"እግዚአብሔር አምላክ፡ 'እነሆ ሰው፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!' አለ።"* የሚለውም መለኮታዊው የትንቢት ቃል፡ በእውን ተፈጸመ።

"ተዋሕዶ" የምንለው፡ የሃይማኖታችን ስም፥ "እግዚአብሔር ወልድ፡ በተዋሕዶ፡ ከኹለት አካላት፡ አንድ አካል፥ ከኹለት ባሕርያት፡ አንድ ባሕርይ ኾነ!" ብለን የምናምንበትም፡ "ምሥጢረ ሥጋዌ" የሚባለው፡ የሃይማኖት ትምህርትና እውቀት፡ ይህ ነው።

ምሥጢረ ሥጋዌ፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ የቱን ያህል በሰውነታቸው ሠርፆና ጠልቆ፥ ሥር ሰድዶና ተወድዶ፡ በሕያውነት ተዋሕዷቸው የሚኖር መኾኑን፡ በገሃድ ከሚያሳዩት እውን ኹኔታዎች መካከል፡ ከትስብእቱ ጀምሮ፡ እስከ ትንሣኤውና ዕርገቱ ድረስ ያሉትን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓላት የሚያከብሩበት ሥርዓትና ድምቀት፡ አንዱ ኾኖ ይገኛል፤ ይህንም፡ ወደፊት፡ ስለበዓልና በዓላት በምናደርገው ውይይታችን ላይ በስፋት እንነጋገርበታለን።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ሥጋዌ::

### ስለምሥጢረ ሥጋዌ ማጠቃለያ::

---

ከዚህ ጋር፡ ከጾመ ነቢያት ጀምሮ፡ እስከዓቢይ ጾምና ሰሙነ ሕማማት፡ በተለይም፡ እስከዕለተ ዓርብ የስቅለቱ ስግደት ድረስ ያሉትን ጾሞቻቸውን የሚፈጽሙበት የቀኖና ጽናት፡ እንዲሁም፡ ሕማማተ መስቀሉን በማዘከር፡ በየሳምንቱ የሚፈጽሙት የዓርብ ጾማቸው፡ በየወሩ፡ በ፳፱ኛው ቀን የሚውለው የመድኃኔ ዓለም የስቅለቱ መታሰቢያና በዓለ ወልድ ተብሎ፡ በ፳፱ኛው ቀን የሚውለው የጌታ የትንሣኤው በዓል፡ ስለዚሁ ስለኢትዮጵያውያኑ ሃይማኖታዊ አቋም፡ በሚበቃ ስለሚያስረዱ፡ ሌላ ማብራሪያ ከቶ አያስፈልግም::

ከዚህ በኋላ ተከታትለው፡ በቅደም ተከተል የሚቀርቡት ሦስት ምሥጢራት፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ያስገኛቸው ናቸው፡ በእነርሱ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር፡ ለሰው የተሰጡት ጸጋዎችም፡ በእያንዳንዳቸው ሓተታ ላይ ይብራራሉ:: እንግዲህ፡ በ"ምሥጢረ ሥጋዌ" ላይ ያሏችሁ ጥያቄዎች፡ በዚህ ማጠቃለያ ከተካተተ፡ ወደሦስተኛው ምሥጢር እናልፋለን::

## ምሥጢረ ጥምቀት::

ጥያቄ:- *እስካሁን እንደተረዳነው፡ ስለሃይማኖታችን፡ በስፋትም ኾነ በጥልቀት ለማወቅ የሚያስችለንን ብሩህና ቀጥተኛ መንገድ፡ በዚህ ውይይታችን አማካይነት፡ ይኸው ተያይዘነዋል፡ ስለዚህ፡ ይህንኑ የስጀመርኸንን የእውቀት ፈለግ፡ ከግብ ለማድረስ፡ እየናፈቅን ነንና፡ ስለሚቀጥለው ምሥጢር፡ የምትሰጠንን ማብራሪያ በጉጉት እንጠብቃለን::*

መልስ:- የሚቀጥለው ርእሳችን፡ "ምሥጢረ ጥምቀት" ነው:: በዚህ ምሥጢር፡ እግዚአብሔር፡ ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ፡ በመልኩ እስከሚፍጠር የወደደው ሰው፡ ሴቷም፥ ወንዱም፡ ለሕይወታቸው ይበጃቸው የነበረውን፡ የእርሱን መለኮታዊ ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ፡ ራሳቸውን የሚጎዳ የክህደትንና የዓመፅን፥ የአመንዝራነትንም ሥራ በመፈጸም፡ የተቃዋሚው የዲያብሎስ ግብረ አበር በመኾናቸውና የክፋት ጐዳናን መርጠው በመከተላቸው ቢያሳዝኑትም፡ ያን ኹሉ በደል፡ ራሱን፡ በቤዛነት አቅርቦና ሠውቶ በመካሥ ይቅር ብሎ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ዘለዓለማዊ ጸጋውን፡ ለእነርሱ፡ መልሶ ያጎናጸፈበት ቸርነቱ፡ በስፋትና በጥልቀት ይነገርበታል::

ይህ ምሥጢር፡ እያንዳንዱን አስተዋይ ሰብአዊ ፍጡር፡ "እኔ፡ ለእግዚአብሔር፡ እንዲህ *'ጠላቱ ስኾን'*፡ እርሱ ግን፡ ይህን የመሰለውን፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነ፡ ይቅርታውንና ምሕረቱን ሊያደርግልኝ፡ እንዴት እንደገና ፈቃደኛ ኾነ?! ይህን ያስደረገ ኃይል፤ ከምን ዓይነቱ ፍቅር ሊመነጭ ቻለ?" በሚል የአንክሮ ጥያቄ እንዲመሰጥ፡ በእርግጥ ያስገድደዋል:: ይህንም፡ ወንጌላዊው፡ *"'የእግዚአብሔር ልጆች' ተብለን ልንጠራ፡ አብ፡ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን፡ እዩ!"* ሲል፡ በመልእክቱ፡ አሳምሮ አስቀምጦታል:: እግዚአብሔር፡ ይህን የመሰለውን፡ የእርሱ ልጆች ለመኾን የሚያበቃንን ታላቅ ጸጋ፡ ለሰው ልጅ የሰጠበት የቸርነት ሥራው፡ የሚነገርበት ትምህርት[፶፯] የሚገኘው፡ ከዚሁ ከ"ምሥጢረ ጥምቀት" ስለኾነ፡ "ምሥጢር" ተብሏል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ሰው፡ ነፍሱ፡ በምድራዊው ኑሮዋ፡ ገዝፋ የምትታይበትንና ለተወሰነ ዕድሜ፡ በጊዜያዊነት የምትቆይበትን፥ ማንነቷንና ምንነቷንም፡ በሃይማኖታዊ አቋሟና በምግባራዊ ድርጊቷ የምትገልጽበትን አካለ ሥጋ ለብሳ፡ ከማሕፀን እንደምትወለድ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ በሰማያዊው ዓለም፡ ለዘለዓለም፡ በሕይወት ለመኖር የሚያበቃትን መንፈሳዊ አካል ለብሳ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የምትወለድበት ረቂቅ ሥርዓት፡ በፈጣሪዋ ቸርነት ተሠርቶላታል፤ ያም ሥርዓት፡ "ምሥጢረ ጥምቀት" ነው:: እርሱም የተመሠረተው፡ *"ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው!"* በሚለው መለኮታዊ ቃል ሲኾን፡ በዓይን የማይታየውና በእጅ የማይዳሰሰው፡ ይህ፡ ረቂቅ ምሥጢር የኾነው መንፈሳዊ ሥርዓት፡ ገዝፎ እንዲታይ የተደረገው፡ በውኃ ኹኖ ተገኘ::[፶፰]

ይህን ሥርዓት፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ በምሥጢረ ሥጋዌ የተገለጸው፡ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ዕድሜው፡ ፴ ዓመት ሲኾነው፡ በመጥምቁ በዮሐንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በመጠመቅ፡ ለሥርዓተ ጥምቀት፡ በኵር ኹኖ፡ ራሱም፡ በአብነት ፈጽሞት፡ መሥርቶታል፡ ቀድሶታልም::

### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት::

ጥያቄ:- *በመሠረቱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለምን ተጠመቀ?*

መልስ:- ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት፡ የመጀመሪያው ምክንያት፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ እርሱ መኾኑን፡ ለዮሐንስና ለዓለሙ በይፋ ለማሳወቅ ነው፡ የዚህ ነገር እውነተኛነት፡ ዮሐንስ፡ ባየውና በሰማው ተረጋግጧል፡ ይህንም፡ ዮሐንስ፡ ጌታን ባጠመቀው ጊዜ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ሰማያት ተከፍተውለት፡ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ እንደርግብ ሲወርድ፥ በእርሱም ላይ ሲቀመጥ አየ!" ደግሞም፡ "በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወድደው ልጄ ይህ ነው!' የሚል ድምፅ፡ ከሰማይ ሲነገር ሰማ::"* የሚለው ቃል ያስረዳል::[፶፱]

ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ የመሠረታትን መንግሥቱን፡ ከነሥርዓቷ በማፈራረስ፡ ዲያብሎስ፡ በሰውና በፍጥረተ ዓለሙ ላይ የዘረጋውን የክፋት ግዛት፡ በዚህ አገዛዙም ጠንቅ የሰፈኑትን የኃጢአት ቀምበርና የሞት ፍዳ፡ በእግሮቹ፡ እንደገል ቀጥቅጦና እንደሰም አቅልጦ ለማስወገድ ነው::[፷]

ሦስተኛውም ምክንያት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ሰው፡ አስወስዷት የነበረውን፡ ከእግዚአብሔር የመወለድን ታላቅ ክብር፡ በማስመለስ፡ ይህችን ልጅነት ለማግኘት፡ ፈቃደኞች ለኾኑ ወንዶችና ሴቶች፡ ይህንኑ ጸጋ፡ ለዘለዓለም ለማቀዳጀት ነው::[፷፩]

ጥያቄ:- *ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዮሐንስ እጅ፡ በዮርዳኖስ ወንዝ፡ በሚጠመቅበት ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በራሱ ላይ፡ ስለምን፡ በርግብ አምሳል ወረደ?*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ጥምቀት::

### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት::

---

**መልስ:-** ቀድሞ: በጥፋት ውኃ ጊዜ: የውኃው ሙላት ጉድሉ እንደኾነ: ኣይቶ እንዲመጣ: ኖኅ: ከመርከቡ አውጥቶ ልኮት የነበረው ቁራ: ሳይመለስ ስለቀረበት: ርግብን ሰደዳት፤ እርሷም: እየበረረች ኼዳ: የውኃውን መጉደል: ተዘዋውራ አይታ: አለመጉደሉን በማየት: ይህንኑ ኹኔታ ለመግለጽ: ባዶዋን ተመለሰች: ከቀናት በኋላ: እንደገና በላካት ጊዜ ግን: ውኃው መጉደሉን በማረጋገጥ: ይህንኑ ለማመልከት: የወይራ ቀምበጥ: ባፏ ይዛ አምጥታ: አብሥራው ነበርና: አሁንም: ዓለሙን: እንደጥፋት ውኃ ማዕበል ያጥለቀለቀው: የዲያብሎስ የክፋት ግዛት: የኃጢአት ቀምበርና የሞት ፍዳ: ከሰውና ከፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ የሚወገድበት: የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት መፈጸሙን ለማብሠር: መንፈስ ቅዱስ: በርግብ አምሳል ተገለጠ::

**ጥያቄ:-** *የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት: በዮርዳኖስ ወንዝ የኾነበት: የተለየ ምክንያት ይኖረው ይኾን? ካለ: ብትገልጹልን?*

**መልስ:-** ዲያብሎስ: አዳምንና ሔዋንን: በተንኰሉ አሳስቶ: የፈጣሪያቸውን ፈቃድ እንዲተላለፉ: እነርሱም: የእርሱን አሳሳች ቃል ተከትለው ለመኖር በመስማማት: ግዝነቱን እንዲቀበሉ ካደረጋቸው በኋላ: ያሸከማቸውን የባርነት ቀንበር አጽንቶ ለማዝለቅ: በጽላተ ሙሴ ምሳሌ: "አዳምና ሔዋን: የዲያብሎስ ባሮች ናቸው!" የሚል ምልክት የታተመባቸው: ኹለት የድንጋይ ሰሌዳዎችን አዘጋጅቶ: አንዱን: በሲዖል: ኹለተኛውን: በዚህ: በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ አኑሮ እንደነበረ: በትውፊት የደረሰን አምላካዊ ቃል ይነግረናል:: ስለዚህ: ያን የዕዳ ሰነድ ደምስሶ ለማጥፋት: ኢየሱስ ክርስቶስ: በዚህ ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ:: በሲዖል ያኖረውንም የዕዳ ሰነድ: መለኮት ከተዋሐደው ሥጋዋ: በሕማማተ መስቀሉ ፍጻሜ ላይ በተለየችው እካለ ነፍሱ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ወደዚያ ወርዶ: ኹለተኛውን የዕዳ ሰነድ ደምስሶ አጠፋው፤ በዚያ የነበሩትንም: ያመኑትን ነፍሳት: ነጻ አወጣቸው::

**ጥያቄ:-** *ኢየሱስ ክርስቶስ: ጥምቀቱን: በውኃ ያደረገው ለምንድር ነው?*

**መልስ:-** *"የእግዚአብሔርም መንፈስ: በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር::"* የሚለው ቃል: ስለሥነ ፍጥረት በሚናገረው: በታላቁ መጽሐፍ መክፈቻ ላይ ተጽፎ ይነበባል፤ ስለዚህ: በጥምቀት ምሥጢር: ከእግዚአብሔር ለሚገኘው መንፈሳዊ ልደት ማስፈጸሚያ: ውኃን መርጦ መሠየሙ አያስደንቅም::

*ውኃ:* የሕይወት ምንጭ ነው፤ ማንኛውም ሥጋዊና ተንቀሳቃሽ ፍጡር: *ያለውኃ:* በሕይወት ሊኖር አይችልም:: ዕፅዋት: አዝርዕትና አትክልት: የሚለመልሙት፥ የሚያብቡትና የሚያፈሩት: *በውኃ* መኾኑን የማይረዳ የለም:: አያሌ የደዌና የሕመም ዓይነቶች የሚፈወሱት: በውኃ የኾነው: ከዚህ የተነሣ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል:: ምድር: ጸንታ: ተጠብቃና ተከብባ የምትገኘው: *በውኃ* ነው::

ቸሩ ፈጣሪ፡ የምሥጢረ ጥምቀት ጸጋ የሚሰጥበትን ሥርዓት ለመፈጸም የሚያስፈልገው ዓቢይ ነገር፡ በምስኪኑ ደኃ ዘንድ ሳይቀር፡ በቀላሉ ሊገኝ የሚችለውንና የማይታጣውን፡ *ውኃን የመሰለውን* ተራ ሀብት እንዲኾን ማድረጉ፡[፷፫] ይህንኑም ሲሳይ፡ አትረፍርፎ ማበርከቱ፡ የቸርነቱን ስፋ ልግሥና ያሳያል።

ጥያቄ:- *ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለምን፡ በ፴ ዓመቱ፡ በዮሓንስ እጅ ተጠመቀ? ዝቅ ብሎ፡ በ፰፡ ከፍ ብሎ፡ በ፵ ዓመት ያላደረገው ለምንድር ነው?*

መልስ:- አዳም፡ የ፴ ዓመት ጕልማሳ ኾኖ ተፈጥሮ ሳለ፡ ራሱን፡ ለፈጣሪው የሕይወት ፈቃድ ሳይኾን፡ ለሰይጣን የሞት ትእዛዝ በማስገዛቱ፡ ከእግዚአብሔር፡ በ፵ ቀን ያገኛትን ልጅነት፡ አስወስዷት ነበርና፡ ያችን ልጅነት ለማስመለስ ሲል ነው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቤዛ ኾኖ፡ ያን ካሣ ለመክፈል፡ በ፴ ዓመቱ የተጠመቀው።

አምላክ ሲኾን፡ ወደዮሓንስ ኼዶ መጠመቁም፡ ተጠማቂው፡ ምንም ታላቅ ባለማዕርግ ቢኾን፡ ወደአጥማቂው ተራ ካህን ኼዶ መጠመቅ የሚገባው መኾኑን፡ ለእኛ፡ በአርአያነት ለማሳየትና ስለትሕትና ምሳሌ ለመኾን ነው።

ጥያቄ:- *ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በ፴ ዓመቱ ከተጠመቀ፡ "እኛም፡ ልንጠመቅ የሚገባን፡ በዚሁ ዕድሜ ነው!" የሚሉ አሉ። ይህን ስለመሰለው አስተሳሰብ፡ ምን ትላለህ?*

መልስ:- ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም የመጣው፡ ለፍጥረቱ የሰጠውን ተስፋና በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ሊፈጽም፡ በዲያብሎስ የክፋት አገዛዝ፤ በኃጢአት ቀንበርና በሞት ፍዳ ሲማቅቅ የኖረውን የሰውን ዘር ሊያድንና ሰዎች፡ በምድር ላይ ሕይወታቸው፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓተ መንግሥት ተከትለው፡ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው፤ እንደሚችሉም ሊያስተምር መኾኑ፡ ቀደም ብሎ በየአርእስቱ፡ በተለይም፡ *በምሥጢረ ሥጋዌ* ትምህርት ውስጥ፡ በሰጧችሁ ሓተታ ተብራርቶላችኋል፤ ስለዚህ፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱ ተጠምቆ፡ ማንነቱን፡ በይፋ ከማሳወቁ ጋር፡ እኛም ተጠምቀን፡ የእግዚአብሔር ልጆች የምንኾንበትን ሥርዓት ሊመሠርት፡ እስከ፴ ዓመት ዕድሜው መቆየት እንዳስፈለገው፡ በዚህ ሓተታ፡ በሚበቃ የተገነዘባችሁት ይመስለኛል።

*ታዲያ*፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ ዓላማውና ግብሩ ይህ መኾኑ ተረጋግጦ ከታወቀ፡ ዕሩቅ ብእሲ የሚባለው ሰብአዊ ፍጡር፡ የዘለዓለም ሕይወት ከሚወረስበት፡ ከእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት፡ እስከ፴ ዓመት ዕድሜው ድረስ የሚቆይበት ምን ምክንያት ይኖራል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለመኾኑ፡ በየእፍታዋ፡ ለሞት ከተጋለጠው ከሰብአዊው ፍጡር መካከል፡ ከቶ፡ በዕድሜው፡ እስከ፴ ዓመት ለመቆየት፡ ዋስትና ያለው ሰው፡ በምድር ላይ አለን? የለም።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ጥምቀት።
### የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት።

---

ወይስ፡ ዕድሜው፡ ከ፴ ዓመት በታች የኾነ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ዕድል ተነፍጎታል ማለት ነውን? ወይስ፡ ይህ ዕድል፡ ሊነፈገው ይገባል ማለት ነውን? አይደለም።

ይህ፡ የሰይጣን ወገኖች የኾኑ፡ የክፉ ሰዎች አስተሳሰብ ሲኾን፡ እግዚአብሔር ግን፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ፡ በዚህ ረገድ ያደረገለት ቸርነት ምን እንደኾነ፡ ቀጥዬ እነግራችኋለሁ። ይኸውም፡ ማንኛውም ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ወደእርሱ መንግሥት ለመግባት ከፈለገ፡ ገና ከእናቱ ማሕፀን ከወጣው አራስ አንሥቶ፡ ወደዐፈርነቱ መቃብር ሊወርድ እስከተቃረበው ሽማግሌ ድረስ፡ ምንም ዓይነት የዕድሜ ወሰን እንዳይደረግበት መፍቀዱና ወደር ወደማይገኝላት፡ ወደዚችው መንግሥቱ ለመግባት፡ አንዲት ግዳጅን ብቻ ይፈጽም ዘንድ የሚጠይቅ ሥርዓትን መደንገጉ ነው።

### የሰብአዊው ፍጡር ጥምቀትና የሚያገኘው ኹለተኛ ልደት።

ጥያቄ፡- *ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ይችል ዘንድ፡ ፈጣሪ፡ ከታላቅ ቸርነቱ ጋር፡ ከእርሱ የጠየቀው፡ አንዲት የኾነችው ብቸኛ ግዳጅ ምንድር ናት?*

መልስ፡- "ኹለተኛዋ ልደት!" ናት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ "*እውነት፡ እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።*" የተባለችው፡ "እንደገና መወለድ!" ይህች ናት።

ጥያቄ፡- *"ሰው፡ ከተወለደ በኋላ፡ ወይም፡ ካደገ፡ ወይም፡ ከሸመገለ በኋላ፡ እንዴት፡ እንደገና ሊወለድ ይችላል? ኹለተኛ ወደእናቱ ማሕፀን ገብቶ፡ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"*

መልስ፡- ይገርማችኋል! ኒቆዲሞስ የተባለው፡ ፈሪሳዊ የአይሁድ አለቃ፡ በሌሊት፡ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ፡ ልክ፡ ይህንኑ፡ አሁን፡ እናንተ ያቀረባችሁትን የመሰለ ጥያቄ፡ ለጌታ አቅርቦለት፡ መልሱን ሰጥቶታል።

ጥያቄ፡- *እውነት!? እንዴት! ታዲያ፡ አምላክ፡ ምን የሚል መልስን ሰጠው?*

መልስ፡- አዎን! ኒቆዲሞስ፡ ይህን ጥያቄ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረበ። ያቀረበውም፡ "*መምህር ሆይ! እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከኾነ በቀር፡ አንተ የምታደርጋቸውን፡ እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና፡ መምህር ኾነህ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን፡*" የሚለውን የመግቢያ ቃል ካስቀደመ በኋላ ነበር።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይኸው ኒቆዲሞስ፡ ቀደም ብሎ ላሰማው፡ ለዚህ ንግግሩ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው መልስ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚቻለው፡ ይህን የመሰለውን እውነት፡ በሌሊት፡ በሥውር መጥቶ፡ በመናገር ብቻ ሳይኾን፡ *እንደገና ተወልዶ፡ በብርሃንና በይፋ በመመስከር* መኾኑን የሚያመለክት ግዳጅን ነው።

ጥያቄውንም፡ *"እውነት፡ እውነት እልሃለሁ! ሰው፡ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።"* ሲል፡ አምላካችን፡ "ኹለተኛው ልደት" የተባለው ምን እንደኾነ፡ ምሥጢሩን ወዲያው ገልጾለታል፡ ትርጉሙንም ፈትቶለታል።

ጥያቄ፡- *እኹንም፡ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ እንዴት እንደኾነ ለመረዳት፡ እንደኒቆዲሞስ፡ ለእኛም፡ ከብዶናልና፡ በበለጠ ብታብራራልን?*

መልስ፡- ለዚህ ጥያቄያችሁ፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለኒቆዲሞስ የተናገረው፡ እንዲህ የሚለው ቃሉ፡ በቂ ምላሽ በመኾኑ፡ እዚህ ላይ ጠቅሼላችኋለሁ።

*"ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፡ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። 'ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል!' ስላልሁህ፡ አታድንቅ! ነፋስ፡ ወደሚወድደው ይነፍሳል፡ ድምፁንም ትሰማለህ፡ ነገር ግን፡ ከወዴት እንደመጣ፡ ወዴትም እንዲኼድ አታውቅም፡ ከመንፈስ የሚወለድም ኹሉ እንዲሁ ነው።"*

ጥያቄ፡- *"ይህ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል?" ይህን ረቂቅ ድርጊት፡ በምን ዘዴ፡ በቀላሉ ታስረዳናለህ?*

መልስ፡- በዚህ ጥያቄያችሁ፡ አሁንም እንደገና፡ ልክ፡ ኒቆዲሞስን መስላችሁ ተገኝታችኋል። ለዚሁ ጥያቄያችሁ፡ መልስ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመለኮታዊ አንደበቱ፡ ለኒቆዲሞስ የተናገረውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ ያንኑ ቃሉን፡ መልስ አድርጌ፡ ይኸው፡ አቅርቤላችኋለሁ፡-

*"አንተ የእስራኤል መምህር ስትኾን፡ ይህን አታውቅምን? እውነት፡ እውነት እልሃለሁ፡ የምናውቀውን እንናገራለን፡ ያየነውንም እንመሰክራለን፡ ምስክራችንንም አትቀበሉትም። ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ፡ ካላመናችሁ፡ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ፡ እንዴት ታምናላችሁ?"*

እንግዴህ፡ ይህን የመሰለውን ምሥጢር መረዳትና መቀበል የሚቻለው፡ በሃይማኖት በታነፀ መንፈሳዊ አእምሮ መኾኑን፡ ቀደም ብዬ ገልጬላችሁ ስለነበረ፡ ታስታውሱታላችሁ። እናንተም፡ ይህን የተያያዝነውን፡ የአዕማደ ምሥጢራቱን ማብራሪያ፡ በዚያ ሃይማኖታዊ መሠረትና መንፈሳዊ አቋም ኾናችሁ እንደምትሰሙኝ፡ በዚያኑ ጊዜ አረጋግጣችሁልኛል።